መጽሐፈ ፡ ግብረ ፡ ሕማማት።



በግእዝና ፡ በአማርኛ።

ይህ ፡ መጽሐፈ ፡ ግብረ ፡ ሕማማት ፡ በብፁዕ ፡ ወቅዱስ ፡ አቡነ ፡ ጳውሎስ ፡ ፓትርያርክ ፡ ርእሰ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘኢትዮጵያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ ዘአክሱም ፡ ወዕጨጌ ፡ ዘመንበረ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ በ፲፩ኛው ፡ ዘመነ ፡ ፓትርያርክነት ፡ ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ በግእዝና ፡ በአማርኛ ፡ ታተመ።

አሳታሚ ፡– ትንሣኤ ፡ ማኅተሚያ ፡ ድርጅት፡
አ·አ· ፲፱፻፺፯ ፡ ዓ·ም

Scanned by CamScanner

ዘማኅትወ፡ሆሣዕና።	የሆሣዕና፡ዋዜማ።

(፫)፡ሠለስት፡ስምዓኒ፡እግዚኦ፡ጸሎትየ፡ሃሌ፡ሉያ፡ሃሌ፡ሉያ፡ወይብጻሕ፡ቅድሜከ፡ገዳርየ፡ሃሌ፡ሉያ፡ሃሌ፡ሉያ፡ወኢትሚጥ፡ገጸከ፡እምኔየ። በዕለተ፡ምንዳቤየ፡አጽምዕ፡እዝነከ፡ኅቤየ። ሃሌ፡ሉያ፡ሃሌ፡ሉያ፡አመ፡ዕለተ፡እጼውዓከ፡ፍጡነ፡ስምዓኒ፡ሃሌ፡ሉያ፡ሃሌ፡ሉያ፡ለዓለም፡ወለዓለመ፡ዓለም። ተፈሥሒ፡ጽዮን፡ወተሐሠዪ፡በጽሐ፡ብርሃንኪ፡ጸድቅ፡ወየዋህ፡ዘዕሤቱ፡ምስሌሁ፡ወምግባሩ፡ቅድመ፡ገጹ።

ሰላም፡በ፪፡ሃሌ፡ሉያ፡ሃሌ፡ሉያ፡ወእንዘ፡ሰሙን፡በዓለ፡ፋሲካ፡ዐርገ፡ኢየሱስ፡ኢየሩሳሌም፡ወተቀበልዎ፡ሕዝብ፡ብዙኃን። ወበልዋ፡ለወለተ፡ጽዮን፡ነዋ፡ንጉሥኪ፡ጸድቅ፡ወየዋህ፡ዘዕሤቱ፡ምስሌሁ፡ወምግባሩ፡ቅድመ፡ገጹ፡ወይከውን፡ሰላም፡በመዋዕሊሁ።

ምልጣን። ወይከውን፡ሰላም፡በመዋዕሊሁ፡ንጉሥኪ፡ጽዮን፡በጽሐ፡ናሁ፡ወይከውን፡ሰላም፡በመዋዕሊሁ።

(ይኳ)፡ሰላመ፡አብ፡ወወልድ፡ወመንፈስ፡ቅዱስ፡እንዘ፡ይባርክ፡ሕዝበ። ወእምዝ፡ይበል፡በዐቢይ፡ዜማ፡እግዚኦ፡መሐረን፡ክርስቶስ።(ሠለስተ፡ጊዜ)፡ወይሠጠዉ፡ሕዝብ፡ዘንተ። ወይበሉ፡ሰላም፡ለኪ፡ምልእተ፡ጸጋ።

ሰላም፡ለክሙ፡ሐዋርያት፡እለ፡ሥሉጣን፡በኵሉ።

ሰላም፡ለክሙ፡ነቢያት፡ወሐዋርያት። ሀበን፡ሰላመክ።

ስብሐት፡ለእግዚአብሔር፡

ስብሐት፡ለማርያም፡

ስብሐት፡ለመስቀለ፡ክርስቶስ።

ጸሎተ፡ሃይማኖት፡

ነአምን፡በአሐዱ፡አምላክ፡በል።

ተፈጸመ፡ጸታ፡ዜማሁ፡ለያሬድ፡በዓለ፡መዝሙር፡ጥዑም። ወምንባብ፡ዘሊቃውንት፡አዕይንተ፡ቤተ፡ክርስቲያን፡ቅድስት፡አዳም፡ዘይትበሀል፡በማኅትወ፡ሰንበት፡ዘሆሣዕና። ጸሎቶሙ፡ወበረከቶሙ፡የሀሉ፡ምስሌን፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን። (ይሕ)፡አቡነ፡ዘበሰማያት።

ምዕራፍ፡፪።

ዘዕለተ፡ሆሣዕና።

መዝሙር፡ዘሆሣዕና፡በ፮፡ወእንዘ፡ሰሙን፡በዐለ፡ፋሲካ፡ቀርቡ፡አርዳኢሁ፡ለአምላክ፡ጽድቅ፡ኀበ፡ደብረ፡ዘይት፡ሙራደ፡ዐቀብ፡ሀገረ፡እግዚአብሔር። ወተቀበልዎ፡ሕዝብ፡ብዙኃን፡አዕሩግ፡ወሕፃናት፡ነሢአሙ፡አዕጹቀ፡በቀልት። እንዘ፡ይብሉ፡ሆሣዕና፡በአርያም፡ተጽዒኖ፡ዲበ፡ዕዋል፡ቦአ፡ሀገረ፡ኢየሩሳሌም፡በትፍሥሕት፡ወበሐሤት፡ይሁቦሙ፡ኀይለ፡ወሥልጣነ። (ምልጣን)፡እንዘ፡ይብሉ፡ሆሣዕና፡በአርያም፡ተጽዒኖ፡ዲበ፡ዕዋል፡ቦአ፡ሀገረ፡ኢየሩሳሌም፡በትፍሥሕት፡ወበሐሤት፡ይሁቦሙ፡ኀይለ፡ወሥልጣነ።

(ዘአምላኪየ)፡በጺሐመ፡ቤተ፡ፋጌ። ጸምአት፡በጺሐሙ፡ቤተ፡ፋጌ፡እፎ፡በጺ፡ቤ፡ፋ። ነሢአሙ፡አዕጹቀ፡በቀልት፡ይብሉ፡ሆሣዕና፡በአርያም። አርባዕት፡(ንልበ)፡ነሥአ፡አብርሃም፡ዐበርተ፡ወበቀልተ፡ያደ፡ምሥዋዐ፡ጸርሐ፡ወከልሐ፡ዘመረ፡ወይቤ፡ሆሣዕና፡በአርያም።

(ምል)፡እምርት፡ዕለት፡በዓልን፡ነያ፡አብርሃም፡አብ፡ዘተመነያ፡ሰብሓ፡ወበዓለ፡ሰመያ። (እም፡አዳ)፡መዝሙር፡ሐዋዝ፡ዘምስለ፡መሰንቆ፡ንፍኑ፡ቀርን፡በዕለተ፡ሠርቅ፡በእምርት፡ዕለት፡በዓልን።

(ምል)፡ሆሣዕና፡እምርት፡እንተ፡አቡነ፡ዳዊት፡ቡርክት፡እንተ፡ትመጽእ፡መንግሥት። (አራራ)፡ንፍኑ፡ቀርን፡በዕለተ፡ሠርቅ፡በእምርት፡ዕለት፡በዓልን፡ተዝካረ፡መድኀኒን፡በኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ንዑ፡ንትፈሣሕ፡በእግዚአብሔር፡ዘረድአን። (ምል)፡በጽዮን፡ንፍኑ፡ቀርን፡በዕለተ፡ሠርቅ፡ንፍሑ፡ቀርን፡በእምርት፡ዕለት፡በዓልን። (በ፬፡ኀፀ)፡ወይቤሎሙ፡ሑሩ፡በልዎ፡ለእገሌ፡በኀቤከአ፡እገብር፡ፋሲካ፡ምስለ፡አርዳእየ። በሀየ፡እገብር፡ፋሲካ። (ምል)፡በኀቤከ፡ዮም፡በኀቤከ፡ፋሲካ፡እገብር፡በልዎ፡ለእገሌ፡ቤተከ፡ሀለወኒ፡አዐል፡ይቤለከ፡ሊቅ፡ከመዝ፡በልዎ፡ለእገሌ። (ኮከ)፡በንጹሕ።

Scanned by CamScanner

ጽርሕ፡ርሡይ፡ወሥርግው፡ይቤሎሙ፡ኢየሱስ፡ለአርዳኢሁ፡ዕቀቡ፡ሕግየ፡ወሥርዓትየ፡ወአክብሩ፡ሰንበ
ታትየ።(ምል)፡በንጹሕ፡ጽርሕ፡ወሥርግው፡ለአርዳኢሁ፡ክርስቶስ፡ይቤሎሙ፡ዕቀቡ፡ሕግየ፡ወሥር
ዓትየ።(ዕዝል)፡ዘነግህ፡ነሥአ፡አብርሃም፡አዕዩቀ፡በቀልት፡ሰብሐ፡ወዘመረ፡በዕለተ፡ሰንበት፡በእ
ኢየሱስ፡ኢየሩሳሌም፡በስብሐት።(ምል)፡አብርሃም፡ነሥአ፡አዕዩቀ፡በቀልት፡አብርሃም፡ነሥአ፡
አብርሃም፡ነሥአ፡አዕዩቀ፡በቀልት፡አብርሃም፡ነሥአ።
(ምል)፡አብርሃም፡ነሥአ፡አዕዩቀ፡በቀልት፡ሰብሐ፡ወዘመረ፡በዕለተ፡ሰንበት፡አብርሃም፡ነሥአ።
(ዘይ)፡ዘየሐዕብ፡በወይን፡ልብሶ፡ሰቀልዎ፡አይሁድ፡ዲበ፡ዕፀ፡መስቀል።(በሰ)፡ዘየሐዕብ፡በወይን፡ልብሶ፡
ሰቀልዎ፡አይሁድ፡ዲበ፡ዕፀ፡መስቀል።(ማኅ)፡በጺሐመ፡ኅበ፡ደብረ፡ዘይት፡ነሢአመ፡አዕዩቀ፡በቀልት፡
ይብሉ፡ሆሣዕና፡በአርያም።(ስብሐ)፡ንፍኁ፡ቀርነ፡በዕለተ፡ሠርቅ፡በእምርት፡ዕለት፡በዓልነ፡ንዑ፡
ንትፈሣሕ፡ኅቡረ።

(አቡ)፡በ፬፡አልጸቀ፡ጸም፡ወበጽሐ፡ፋሲካ፡ኢትግበሩ፡ሊተ፡ምክንያተ፡ለግዕዛንክሙ፡እስመ፡ኅላፊ፡
ውእቱ፡ንብረተ፡ዝንቱ፡ዓለም።ንብረቱኒ፡ፍትወቱኒ፡ኅላፊ፡ውእቱ።(ምል)፡እስመ፡ኅላፊ፡ውእቱ፡
ንብረተ፡ዝንቱ፡ዓለም፡ዓለሙኒ፡ኅላፊ፡ፍትወቱኒ፡ኅላፊ፡እስመ፡ኵሉ፡ኅላፊ፡ውእቱ።(ዓዲ)፡ዓለሙኒ፡
ኅላፊ፡ፍትወቱኒ፡ኅላፊ፡እስመ፡ኵሉ፡ኅላፊ፡ውእቱ።

መዋሥዕት፡ዘሆሣዕና።

መዝሙር፡ዘዳዊት፡ዘ፲ወ፰ወ፩፡ተፈሣሕኩ፡እስመ፡ይቤሉኒ፡ቤተ፡እግዚአብሔር፡ነሐውር።ኢየሩሳሌም፡
ዐርገ፡ተጽዒኖ፡ዲበ፡ዕዋል፡ወልደ፡አምላክ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ዘበአማን፡ንጉሥ።ወበእንተ፡ቤተ፡እግ፡
ኁሠ።ዘ፲ወ፰ወ፬፡እለ፡ተወከሉ፡በእግዚአብሔር፡ከመ፡ደብረ፡ጽዮን።ጸድቅ፡ወየዋህ፡ዘዕሤቱ፡ምስሌሁ፡
ወምግባሩ፡ቅድመ፡ገጹ፡ወልደ፡አምላክ፡ዘየኀዕብ፡በወይን፡ልብሶ፡(ምል)፡ዘየኀዕብ፡በወይን፡ልብሶ፡
ወልደ፡አምላክ፡ዘየኀጽብ፡በወይን፡ልብሶ፡ጸድቅ፡ወየዋህ፡ዘዕሤቱ፡ምስሌሁ፡ወምግባሩ፡ቅድመ፡ገጹ።
ዘ፲ወ፰ወ፭፡እማዕምቅ፡ጸዋዕኩከ፡እግዚኦ።ዘዲበ፡ኪሩቤል፡ይነብር፡ዲበ፡ዕዋል፡ነበረ፡ምስለ፡አርዳኢሁ፡
ሆሣዕና፡ዘየደ፡በዕለተ፡ሰንበት።ወውእቱ፡ያድኅኖ፡ለእስራኤል፡እምኵሉ፡ኀጢአቱ።(ምል)፡ዘዲበ፡
ኪሩቤል፡ይነብር፡ዲበ፡ዕዋል፡ነበረ፡ምስለ፡አርዳኢሁ፡ሆሣዕና፡ዘየደ፡በዕለተ፡ሰንበት፡ዘ፲ወ፬፡እግዚኦ፡
ኢይትዔበየኒ፡ልብየ።ይቤሎ፡ያዕቆብ፡ለወልዱ፡ይሁዳ፡ሀሎ፡ንጉሥ፡ዘይወዕእ፡እምኔከ፡ዘየኀዕብ፡በወይን፡
ልብሶ።እምይእዜ፡ወእስከ፡ለዓለም፡ዘ፲ወ፯፡እግዚአብሔር፡ይባርከነ፡ወይሣሃለነ።ቦ፡እለ፡ኀጸፉ፡አልባ
ሲሆሙ፡ውስተ፡ፍኖት፡እንዘ፡ይብሉ፡በሩካ፡ውእቱ፡ንጉሡ፡እስራኤል።ወይፈርሀዎ፡ኵሎሙ፡አጽናፈ፡
ምድር፡ምልዐ፡ቦ፡እለ፡ነጸፉ፡አልባሲሆሙ፡ውስተ፡ፍኖት፡እንዘ፡ይብሉ፡በሩካ፡ውእቱ፡ንጉሡ፡እስራኤል።
(ዕዝል)፡ይትባረክ፡እግዚአብሔር፡አምላክ፡እስራኤል፡ከሃሊ፡በቃሉ፡ወሠናይ፡በምግባሩ፡ዘየኀዕብ፡
በወይን፡ልብሶ፡ንጉሠኪ፡ጽዮን።(ምል)፡ከሃሊ፡በቃሉ፡ወሠናይ፡በምግባሩ፡ዘየኀዕብ፡በወይን፡ልብሶ፡
ንጉሠኪ፡ጽዮን።(አራራይ)፡ይባርከዎ፡ኵሉ፡ግብረ፡እግዚእ፡ለእግዚአብሔር።ስቡሕኒ፡ውእቱ፡
ወልዐ-ልኒ፡ውእ፡ለዓ።በእምርት፡ዕለት፡በዓልነ፡ንፍኁ፡ቀርነ፡በጽዮን።ንባርኮ፡ለአብ፡ወወልድ፡
ወመንፈስ፡ቅዱስ፡ስቡሕኒ፡ውእ፡ወል፡ውእ፡ለዓ።በእምርት፡ዕለት፡በዓልነ፡ንፍኁ፡ቀርነ፡በጽዮን።
(ምል)፡በእምርት፡ዕለት፡በዓልነ፡ንፍኁ፡ቀርነ፡በጽዮን።

(እስ)፡ወእንዘ፡ሰሙን፡በዓለ፡ፋሲካ፡ዐርጉ፡አርዳኢሁ፡ምስሌሁ፡ወይቤሎሙ፡ሑሩ፡በልዎ፡ለእገሌ፡
ይቤለከ፡ሊቅ፡በኀቤከአ፡እገብር፡ፋሲካ፡በንጹሕ፡ጽርሕ፡ወበርሡይ፡ምስለ፡አርዳእየ፡በህየ፡እገብር፡
ፋሲካ።(እስ)፡ወይቤሎሙ፡ዕዝራ፡ለሕዝብ፡ዓኡ፡ግበሩ፡በዓለ፡በትፍሥሕት፡ወበልዋ፡ለወለተ፡ጽዮን፡
ነዋ፡ንጉሠኪ፡በጽሐ።(ምል)፡ወበልዋ፡ለወለተ፡ጽዮን፡ነዋ፡ንጉሠኪ፡በጽሐ።(እስ)፡ወትቤ፡ጽዮን፡
አርኅዊ፡ሊተ፡አናቅጸ፡ይባኡ፡ሕዝብ፡ብዙኃን፡ወያእትቱ፡እብነ፡እምፍኖት፡ቤትየሰ፡ቤተ፡ጸሎት፡
ይሰመይ።

(እስ)፡ነሥአ፡አብርሃም፡ዐበርተ፡ወበቀልተ፡በዘየዐውድ፡ምሥዋዐ፡ሰብሐ፡ወዘመረ፡በዕለተ፡ሰንበት፡
ሆሣዕና፡በአርያም፡ለወልደ፡ዳዊት።

Scanned by CamScanner

ክፍል፡፩።

በስመ፡አብ፡ወወልድ፡ወመንፈስ፡ቅዱስ፡አሐዱ፡አምላክ።

፩፤ ንዌጥን ፡ በረድኤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ በጽሑፍ፡ዘአንበርዎ ፡ አበዊነ ፡ መምህራን ፡ ዘቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ቅድስት ፡ እለ ፡ አዳም ፡ ዘየኅብር ፡ ድርሳናተ ፡ ወወንጌላተ ፡ ወትን ቢታተ ፡ በዘይደሉ ፡ አንብቦቱ ፡ በሰሙነ ፡ ሕማማት፡እምዕለተ፡እሑድ፡ዘሆሣዕና፡ወዘ ይተልዎ፡እምሰዓታተ፡ሌሊት፡ወመዐልት።

፪፤ ይረድእ፡እግዚአብሔር፡በእንተ፡ቀዊም፡በት እዛዝቲሃ፡አሜን።
ዝንቱ፡ዘይደሉ፡አንብቦቱ፡በሌሊተ፡እሑድ።

ምዕ፡፫፡፱-፴፯።

፫፤ (ዓዲ፡ጥቅስ)፡እምትንቢተ፡ኢሳይያስ፡ምዕ፤ ፴፡፱። ዕርግ፡ዲበ፡ደብር፡ልዑል፡ዘይዜንዋ፡ ለጽዮን፡ወክላህ፡በኃይልከ፡አንሥዕ፡ቃለከ፡ በኃይል ፡ ወዜንዋ ፡ ለኢየሩሳሌም ፡ ወንግር ፡ ለአኅጉረ፡ይሁዳ።

፬፤ ናሁ ፡ ይመጽእ ፡ ንጉሥክሙ ፡ ዘዕሤቱ ፡ ምስሌሁ፡ወምግባሩ፡ቅድሜሁ፡ከመ፡ኖላዊ፡ ዘይርዒ ፡ መርዔተ ፡ አባግዒሁ ፡ በመዝራዕቱ ፡ ልዑል፡ያስተጋብእ።

፭፤ ሰላም፡ለጽዮን፡ኅሪት፡እንተ፡ሣረራ፡እግዚአ ብሔር፡ቅዱስ፡በስብሐት፡ወክብር።

፮፤ ተንሥኢ ፡ አሠርግዊ ፡ አናቅጸኪ ፡ እስመ ፡ ይመጽእ፡ወልደ፡እግዚአብሔር።

፯፤ ወውእቱ፡ያድኅነኪ፡በጽድቅ፡ወበንጽሕ።

፰፤ ናሁ ፡ ሱሉሙ ፡ ደቂቅኪ ፡ ይመጽኡ ፡ ኀቤሁ ፡ በፍሥሐ፡እንዘ፡ይጸርሑ፡ወይብሉ፡ሆሣዕና፡ ለወልደ፡ዳዊት።

፱፤ ወሶበ፡ቀርቡ፡ውስተ፡ቤተ፡ፋጌ፡ኀበ፡ደብረ፡ ዘይት ፡ ፈነወ ፡ እግዚእ ፡ ኢየሱስ ፡ ክልኤተ ፡ እምአርዳኢሁ።

፲፤ ወይቤሎሙ ፡ ሑሩ ፡ ኀበ ፡ ዛቲ ፡ ሀገር ፡ እንተ ፡ ቅድሜክሙ ፡ ትረክቡ ፡ አድገ ፡ ወዕዋለ ፡ እሱራነ፡ፍትሕዎሙ፡ወአምጽእዎሙ፡ሊተ።

ክፍል፡፩።

በአንድ ፡ አምላክ ፡ በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ፡ቅዱስ፡ስም።

፩፤ የአዳም፡ዘሮች፡የሆኑ፡የቅድስት፡ቤተ፡ክርስ ቲያን ፡ መምህራን ፡ አባቶቻችን ፡ ጽፈው ፡ ያኖሩትን ፡ ከድርሳናት ፡ ከወንጌሎችና ፡ ከነቢያት ፡ መጻሕፍት ፡ የሚተባበር ፡ በሕማማት ፡ ሰሞን ፡ ከሆሣዕና ፡ እሑድ ፡ ጀምሮ፡በሌሊቱና፡በመዓልቱ፡ሰዓቶች፡በተ ከታታይ ፡ መነበብ ፡ የሚገባውን ፡ ለመጻፍ ፡ በእግዚአብሔር፡አጋዥነት፡እንጀምራለን።

፪፤ በሥርዓታም ፡ ጸንቶ ፡ ስለመኖር ፡ እግዚአ ብሔር፡በእውነት፡ይረዳል፤ይርዳን።ይኸም፡ በእሑድ፡ሌሊት፡መነበብ፡የሚገባው፡ነው።

ምዕ፡፳፡፱-፵፪።

፫፤ ዳግመኛ፡ከኢሳይያስ፡ትንቢት፡ምዕ፤፷፡፤፱። ለጽዮን ፡ ወሬን ፡ የምትነግራት ፡ ሰው ፡ ወደ ፡ ረኸም፡ተራራ፡ውጣ፤አሰምተህ፡አስተምር፤ ቃልህንም፡ከፍ፡ከፍ፡አድርግ፤ለኢየሩሳሌም፡ ንገራት፤ለይሁዳ፡ከተሞችም፡ተናገር።

፬፤ እነሆ ፡ ንጉሣችሁ ፡ ይመጣል ። ዋጋው ፡ ከእርሱ፡ጋራ፡ነው፤ሥራውም፡በፊቱ፡ነው፤ የበጎቹን ፡ መንጋ ፡ እንደሚያሰማራ ፡ እረኛ ፡ ከፍ፡ባለ፡ሥልጣኑ፡ይሰበስባል።

፭፤ ቅዱስ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለፈጠራት ፡ ለተመ ረጠች ፡ ጽዮን ፡ ሰላም ፤ ምስጋናና ፡ ክብር ፡ ይገባታል።

፮፤ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ ይመጣልና ፡ ጽዮን ፡ ሆይ፡ተነሥተሽ፡አደባባይሽን፡አስጊጪ።

፯፤ እርሱም ፡ በዕውነትና ፡ በንጽሕና ፡ ይጠብ ቅሻል።

፰፤ እነሆ ፡ ልጆችሽ ፡ ሁሉ ፡ ደስ ፡ እያላቸው ፡ ወደእርሱ ፡ ይመጣሉ ፤ ለዳዊት ፡ ልጅ ፡ መድኃኒት፡መባል፡ይገባል፡እያሉ፡ይጮሃሉ።

፱፤ በደብረ ፡ ዘይት ፡ አጠገብ ፡ ወዳለው ፡ ወደ ፡ ቤተ፡ ፋጌ ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፡ ጌታ ፡ ኢየሱስ ፡ ከደቀ፡መዛሙርቱ፡ሁለቱን፡ላከ።

፲፤ በፊታችሁ፡ወዳለች፡ወደዚያች፡ከተማ፡ሂዱ፤ አህያና ፡ ውርንጫ ፡ ታስረው ፡ ታገኛላችሁ ፤ ፈትታችሁ፡አምጡልኝ፡አላቸው።

Scanned by CamScanner

ዘዕለተ፡ሆሣዕና።

፲፯፤ ወለእመ፡ቦ፡ዘይቤለክሙ፡አሐዱ፡ለምንት፡ትፈትሕዎሙ፡በልዎ፡አንትሙ፡እስመ፡እግዚእ፡ይፈቅዶሙ፡ወወፅኡ፡አርድእት፡በከመ፡ይቤሎሙ፡ወረከቡ፡አድኅ፡ወፅዋለ፡እሱራነ።ወፈትሕዎሙ፡ወወሰድዎሙ፡ሎቱ።

፲፰፤ ከመ፡ይትፈጸም፡ዘይቤ፡እግዚአብሔር፡እምኅበ፡ነቢይ፡በልዋ፡ለወለተ፡ጽዮን፡ነዋ፡ይመጽእ፡ኀቤኪ፡ንጉሥኪ፡ተጽዒኖ፡ዲበ፡ዕዋል፡ወዲበ፡እድግት።

፲፱፤ ወሶበ፡ቀርበ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡ኀበ፡አንቀጸ፡ሀገር፡ነሥኡ፡ዐበርተ፡በእደዊሆሙ፡ወአዕጹቀ፡ዘይት፡በየማኖሙ፡ወነጸፉ፡ውስተ፡ፍኖት፡ዘሖረ፡በኀቤሃ፡መድኅን፡ወከልሑ፡ሕዝብ፡ወይብሉ፡ሆሣዕና፡ለወልደ፡ዳዊት፡"ሆሣዕና፡በአርያም"፡ዝንቱ፡ውእቱ፡ንጉሠ፡እስራኤል።

፳፤ አ፡ለዛቲ፡ነከራ፡ዐባይ፡ዘይነብር፡ዲበ፡ኪሩቤል፡ወሱራፌል፡ይጼዐን፡ዲበ፡አድግ፡ወዕዋል።በከመ፡ሥርዐት፡ውእቱ፡ህልው፡ዲበ፡ምድር፡ወኀደገ፡ሰማያተ፡ወይነብር፡ውስተ፡ሕፅነ፡አቡሁ።

፳፩፤ ወውእቱ፡ህልው፡ውስተ፡ኢየሩሳሌም፡ሀገሩ።

፳፪፤ ወደቂቀ፡ዕብራውያን፡ነጸፉ፡አልባሲሆሙ፡ቅድሜሁ።

፳፫፤ ወኪሩቤል፡ኀቡረ፡ይከድኑ፡ገጸሙ፡በክነ፡ፊሆሙ፡እልክቱ፡ኮኑ፡ይሴብሑ፡በድልው፡አፋሆሙ፡ዘእንበለ፡አርምሞ።

፳፬፤ ቡሩክ፡እግዚአብሔር፡በሳሌም፡ደብረ፡መቅደሱ፤ወእልክቱኒ፡ኮኑ፡ይሴብሑ፡እንዘ፡ይብሉ፡ሆሣዕና፡ለወልደ፡ዳዊት፡ቡሩክ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ዘመጽአ፡ወአድኀነ።

፳፭፤ (ዓዲ፡ጥቅስ፡ዮሐ፡ምዕ፤፲፪፤፲፪)፡ወአመ፡ሳኒታ፡ሕዝብ፡ዘመጽኡ፡ኀበ፡በዓል፡ሶበ፡ሰምዑ፡ከመ፡ይመጽእ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ኀበ፡ኢየሩሳሌም፡ነሥኡ፡ዐበርተ፡እምበቀልት፡ወወፅኡ፡ለቀበላሁ፡እንዘ፡ይብሉ፡ሆሣዕና፡ለወልደ፡ዳዊት፡ዘጸውዖ፡ለአልዓዛር፡ወአንሥኦ፡እምነ፡ምውታን፡መጽአ፡ዮም፡ኀበ፡ኢየሩሳሌም፡ከመ፡ይፈጽም፡መጻሕፍት።

የሆሣዕና፡ዕለት።

፲፯፤ ከሰዎች፡አንዱ፡ለምን፡ትፈቷቸዋላችሁ፡የሚላችሁ፡ቢኖር፡እናንተ፡ጌታ፡ይሻቸዋል፡በሉት፤ደቀ፡መዛሙርቱም፡እንዳላቸው፡ወጡ፤የታሠሩ፡አህያና፡ውርንጫ፡አግኝተው፡ፈትተው፡ወሰዱለት።

፲፰፤ እግዚአብሔር፡በነቢይ፡ለጽዮን፡ልጅ፡ንጉሥሽ፡በውርንጫና፡በአህያይቱ፡ተቀምጦ፡ወዳንቺ፡ይመጣል፡በልዋት፡ያለው፡ይፈጸም፡ዘንድ።

፲፱፤ ጌታ፡ኢየሱስም፡ወደ፡ከተማው፡በር፡በደረሰ፡ጊዜ፡በእጃቸው፡ሰሌንና፡የወይራ፡ዝንጣፊ፡ወስደው፡መድኃኒታችን፡ወደሚሄድባት፡መንገድ፡ገለገሉ፤ሕዝቡም፡ለዳዊት፡ልጅ፡መድኃኒት፡መባል፡ይገባዋል፡"መድኃኒት፡በአርያም"፡እያሉ፡ጮኹ፤እርሱም፡የእስራኤል፡ንጉሥ፡ነው።

፳፤ ለዚች፡ታላቅ፡ሥራ፡አንክሮ፡ይገባል።በኪሩቤልና፡በሱራፌል፡ላይ፡አድሮ፡የሚኖር፡በሰውነት፡ሥርዓት፡በአህያና፡በውርንጫ፡ላይ፡ተቀመጠ፤እርሱም፡ልዑል፡ባሕርዩን፡ሠውሮ፡በምድር፡ተገለጠ፤በአባቱም፡ዕሪና፡ይቀመጣል።

፳፩፤ እርሱም፡በሀገሩ፡በኢየሩሳሌምም፡ይኖራል።

፳፪፤ የዕብራውያን፡ልጆችም፡በፊቱ፡ልብሳቸውን፡አነጠፉ።

፳፫፤ ኪሩቤልም፡ፊታቸውን፡በክንፋቸው፡ሸፍነው፡በተዘጋጀ፡አንደበታቸው፡ያለ፡ማቋረጥ፡ያመሰግናሉ።

፳፬፤ እግዚአብሔር፡በመመስገኛው፡በሳሌም፡ቤተ፡መቅደሱ፡የተመሰገነ፡ነው።እነርሱም፡ሰው፡ሆኖ፡ላዳነን፡ለጌታ፡ለኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ለዳዊት፡ልጅ፡መድኃኒት፡መባል፤ቡሩክ፡መባል፡ይገባዋል፡እያሉ፡የሚያመሰግኑ፡ሆኑ።

፳፭፤ (ዳግመኛም፡ጥቅስ፡ዮሐ፡ምዕ፤፲፪፡፲፪)፡በማግሥቱም፡ወደበዓሉ፡የመጡ፡ሕዝቦች፡ጌታ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ወደ፡ኢየሩሳሌም፡እንደሚመጣ፡በሰሙ፡ጊዜ፡የሰሌን፡ዛፍ፡ዝንጣፊ፡ይዘው፡በእግዚአብሔር፡ስም፡የሚመጣ፡ሆሣዕና፡መባል፡ለዳዊት፡ልጅ፡ይገባዋል፤አልዓዛርን፡ጠርቶ፡ከሙታን፡ለይቶ፡ያስነሣው፡የመጻሕፍትን፡ቃል፡ይፈጽም፡ዘንድ፡ዛሬ፡ወደ፡ኢየሩሳሌም፡መጣ፡እያሉ፡ወጥተው፡ተቀበሉት።

Scanned by CamScanner

ዘዕለተ፡ሆሣዕና።

ክፍል፡፪።

ድርሳን፡ዘቅዱስ፡ወክቡር፡ስምዖን፡ዐምዳዊ፡ዘይትነበብ፡በሌሊተ፡ሰንበተ፡ክርስቲያን፡ቅድስት፡ዘኮነ፡ባቲ፡በዓለ፡ሆሣዕና።

፩፤ አ፡እግዚአየ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ሀበኒ፡ከመ፡እጹር፡አዕጹቀ፡ዘይት፡ወፀበርተ፡በቀልት፡እጽራሕ፡ጎቤከ፡ምስለ፡ሕፃናት፡እንዘ፡አብል፡ሆሣዕና፡በአርያም፡ለከ።

፪፤ አ፡ወልደ፡ዳዊት!! አስተዋሕደኒ፡ምስሌከ፡አማኑኤል።

፫፤ ወረስየን፡ንኩን፡አባላቲከ፡ወአሥርቅ፡ውስተ፡ጎሊናን፡ጸዳለ፡ስብሐቲከ፡ወረስየን፡ከመ፡ንኩን፡እምደቂቀ፡ርስትከ።አንተ፡ውእቱ፡ኖላዊነ፡ወመጋቢነ፡ወመራሒነ።

፬፤ ወአንተ፡ንጉሥነ፡ወንሕነ፡ደቂቀ፡ርስትከ።

፭፤ ቡርክት፡ምጽአትከ፡ጎቤነ፡አ፡ንጉሥነ፡ወአምላክነ፡አድኅንነ፡እመንግሥተ፡ጽልመት፡ወአብጽሐነ፡ጎበ፡መንግሥት፡ዘምልዕት፡ብርሃነ።

፮፤ ወአድኅንነ፡እምተከይዶ፡ለመልአከ፡ጽልመት፡ወጸሐፍ፡ላዕሌነ፡ኪዳነከ፡ወሕገከ፡አምላካዊ፡ከመ፡ንረስ፡በስምከ፡ሕይወት፡ማሕየዊተ።

፯፤ አ፡እግዚአየ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ዘቦእከ፡ውስተ፡ምኵራብ፡ወሰደድኮሙ፡ለእለ፡ይሠይጡ፡አርጋበ፡ወትቤሎሙ፡ቤትየሰ፡ቤተ፡ጸሎት፡ይሰመይ፡አንትሙሰ፡ረሰይ ክምዎ፡በአተ፡ፈያት፡ወሰረቅት።

፰፤ ስድድ፡እምልብየ፡ወነፍስየ፡ዙሎ፡መንፈሰ፡እከይ፡ወኅልዮ፡ምኑን።

፱፤ ወረስዮ፡ለልቡናየ፡ይኩን፡ቤተ፡ጸሎት፡ወአንቅሆሙ፡ለልብየ፡ወለኅሊናየ፡ጎበ፡ስብሐት፡ወባርኮት፡ለስምከ።

ቃል፡ዘተብህለ፡እምኅበ፡አረጋዊ፡መንፈላዊ፡ዘይትነበብ፡በዝንቱ፡ጊዜ።

፩፤ ወዓዲ፡ጸጋሁ፡ለአብ፡ለእመ፡ኅሠሠዋ፡በፈቲው፡ይረክብዋ፡በኀሊሥ፡ኅሣሥያን።

የሆሣዕና፡ዕለት።

ክፍል፡፪።

ንጹሕ፡ክቡር፡የሚሆን፡ዐምዳዊው፡ስምዖን፡የደረሰው፡የሆሣዕና፡በዓል፡በተደረገባት፡በከበረች፡የክርስቲያኖች፡ሰንበት፡ሌሊት፡የሚነበብ።

፩፤ ጌታዬ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ሆይ፡የዘይት፡ዝንጣፊና፡የሰሌን፡ዘንባባ፡ተሸክሜ፡ከአርያም፡የተገኘ፡መድኃኒት፡መባል፡ለአንተ፡ይገባል፡እያልኩ፡ከሕፃናት፡ጋራ፡እጮኽ፡ዘንድ፡አድለኝ።

፪፤ የዳዊት፡ልጅ፡ሆይ፡አማኑኤል፡እግዚአብሔር፡ከእኛ፡ጋር፡ነው፡ማለት፡እንደሆነ፡ከአንተ፡ጋር፡አንድ፡አድርገኝ።

፫፤ ወገኖችህ፡እንሆን፡ዘንድ፡አድርገን፤በልቡናችን፡የጌትነትህን፡ብርሃን፡አብራ፡ከወገንህ፡ልጆች፡ውስጥ፡አድርገን።አንተ፡ጠባቂያችን፡መጋቢያችን፡መሪያችን፡ነህ።

፬፤ አንተም፡ንጉሣችን፡እኛም፡የወገንህ፡ልጆችነን።

፭፤ ንጉሣችንና፡አምላካችን፡ወደ፡እኛ፡መምጣትህ፡የተባረከች፡ናት፤ከጨለማውም፡ግዛት፡አድነህ፡ብርሃንንና፡ክብርን፡ወደ፡ተመላች፡መንግሥትም፡አድርሰን።

፮፤ በጨለማው፡ገዥ፡ከመረገጥ፡አድነን፡ቃል፡ኪዳንህንና፡አምላካዊ፡ሕግህን፡በላያችን፡አጽና፤በስምህ፡የሚያድን፡ሕይወትህን፡እንወርስ፡ዘንድ።

፯፤ ጌታዬ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ሆይ፡ወደ፡ቤተ፡መቅደስ፡ገብተህ፡ርግቦች፡የሚሸጡትን፡ቤቴ፡የጸሎት፡ቤት፡ይባላል፤እናንተ፡ግን፡የሌባና፡የወንበዴ፡ዋሻ፡አደረጋችሁት፡በማለት፡ያሳደድኻቸው።

፰፤ ከልቤና፡ከሰውነቴ፡የክፋት፡መንፈስን፡ሁሉና፡የተናቀ፡ነገር፡ማሰብን፡አስወግድ።

፱፤ ልቡናዬንም፡የጸሎት፡ቤት፡አድርገው፡ልቤንና፡ሐሳቤንም፤ስምህን፡ለማክበርና፡ለማመስገን፡አንቃቸው።

በዚሁ፡ጊዜ፡የሚነበብ፡ከአረጋዊ፡መንፈላዊ፡የተነገረ፡ቃል።

፩፤ ዳግመኛም፡የአብ፡ጸጋውን፡ወደው፡ቢፈልጓት፡ፈላጊዎች፡ያገኙዋታል።

Scanned by CamScanner

ዘዕለተ፡ሆሣዕና።	የሆሣዕና፡ዕለት።
፪፤ ቃል ፡ ዘይሰማዕ ፡ በአዕዛኑ ፡ ሥጋ ፡ ውስተ ፡ መካነ፡ አእምሮ፡ ወአንከሮ፡ አስምዐ፡ ድምፃ፡ በመዋዕለ ፡ ትፍሥሕት ፡ ዘውሉድ ፡ እንዘ ፡ ይብል፡ምንተ፡ትፈቅድ፡አ፡ወልድየ።	፪፤ በማስተዋል ፡ በአድናቆት ፡ ቦታ ፡ በሥጋዊ ፡ ጆሮ፡የሚሰማ፡ቃል፡በልጆች፡ተድላ፡ደስታ፡ ወራት ፡ ልጄ ፡ ሆይ ፡ ምን ፡ ትሻለህ ፡ ብሎ ፡ ድምፁን፡አሰማ።
፫፤ ወአውሥአ ፡ ውእቱ ፡ በቃለ ፡ ተራኅርኖ ፡ ወበንባበ ፡ ሕፃናት ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ ኪያከ ፡ አጎሥሥ ፡ አ ፡ አቡየ ፡ ወአኮ ፡ ንዋየከ ፡ ወኢ ፡ ዝሉሎ።	፫፤ እርሱም ፡ በርኅራኄ ፡ ቃልና ፡ በሕፃናት ፡ አንጋገር፡አባቴ፡ሆይ፡አንተን፡ነው፡የምሻ፡ ገንዘብህን ፡ አይደለም ፤ ሌላውንም ፡ ሁሉ ፡ አልሻም፡ብሎ፡መለሰ።
፬፤ ወበግብአቱ፡እምህየ፡ይቤ፡በልቡ፡ተአክለኒ፡ ዛቲ ፡ ህየንተ ፡ ዝሉን ፡ ጸሎታትየ ፡ ወስእለ ታትየ፡በዝንቱ፡ዓለም።	፬፤ ሲመለስም ፡ በልቡ ፡ ስለ ፡ ጸሎቱም ፡ ስለ ፡ ልመናዬም ፡ ሁሉ ፡ ፈንታ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ይህች፡ትበቃኛለች፡አለ።
፭፤ እሉኬ፡እለ፡ሰማዕክዎሙ፡እምውእቱ፡እኁ፡ ዘተገብሩ፡ሎቱ።	፭፤ ከዚያ፡ወንድም፡የሰማኋቸው፡እኒህ፡የተደረ ጉለት፡ናቸው።
፮፤ ወይቤለኒ ፡ ዛቲኬ ፡ ይእቲ ፡ መንፈስ ፡ እንተ ፡ ብህላ ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ከመ ፡ ይእቲ ፡ ትጼውዖ፡ለአብ፡እንዘ፡ትብል፡አባ፡ወአቡየ።	፮፤ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ የተናገራት ፡ መንፈስ ፡ አብን፡አባ፡አባቴ፡ብላ፡የምትጠራው፡ይህቺ፡ ናት፡ብሎ፡ይቺ፡እንደ፡ሆነች፡ነገረኝ።
፯፤ እሀ ፡ ለልሳን ፡ ሐዲስ ፡ ዘይከድና ፡ ለጥቅበተ ፡ ሥጋ፡ወይሁባ።	፯፤ ለአዲስ፡አንደበት፡የሥጋ፡ጽሬትን፡የሚያለ ብሳትና፡የሚሰጣትን፡አዬ፡ወዲያ፡(እሀ!)።
፰፤ መኑ፡ዘአብሐከ፡ወወሀበከ፡ሥልጣነ፡ከመ፡ ትክሥት ፡ ዘኢይትከሠት ፡ ወረሰይኮሙ ፡ ይደመሙ፡ለዓለማት።	፰፤ የማይገለጠውን ፡ ገልጠህ ፡ ለዓለማውያን ፡ መደነቂያ ፡ ታደርጋቸው ፡ ዘንድ ፡ ማን ፡ ሥልጣን፡ሰጠህ?
፱፤ ናሁ ፡ መንፈስ ፡ አመረኒ ፡ በጎቡአ ፡ ከመ ፡ አርምሞ፡ውሳንያቲሆሙ፡ለእሉ።	፱፤ የእሊህ ፡ ውሳኔያቸው ፡ አርምሞ ፡ ገምታ ፡ እንደሆነ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እነሆ ፡ በምሥጢር፡አመለከተኝ።
፲፤ ጎድግ፡አ፡እጉየ፡ጎሠመ፡ገጹ፡ለዘየሐበርት፡ ለከ ፡ ባሕርያተ ፡ ወከላእ ፡ ንጸሬከ ፡ እምኔሁ ፡ ከመ፡ ኢይሕጽጸ ፡ ቅድመ ፡ አዕይንቲከ ፡ ባሕርያት፡እለ፡ይትወሀባ፡ለከ፡በእዴሁ።	፲፤ ወንድሜ ፡ ሆይ ፡ የመዐርጋተ ፡ ገድልን ፡ ባሕርይ፡ ለሚተነትንልህ ፡ የፊቱን ፡ ቋጠሮ ፡ ተው፤በእጁ፡የሚሰጠህ፡ማዕርጋተ፡ጸጋ፡በዓ ይኖችህ ፡ ፊት ፡ እንዳይጎድሉ ፡ ዓይንህን ፡ ከእርሱ፡ከልክል።
፲፩፤ ወተዘከር፡በዝንቱ፡አድኅኒ፡ዘጾሮ፡ለእግዚአ፡ ቅድሳት።	፲፩፤ በዚህም ፡ የቅድስና ፡ ባለቤትን ፡ የተሸከ መውን፡አህያ፡አስብ።
ስንክሳር።	ስንክሳር።
በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አሐዱ ፡ አምላክ ፡ አመ ፡ ዕሥራ ፡ ወሰኑዩ ፡ ለመጋቢት።	በአንድ ፡ አምላክ ፡ በአብ ፡ በወልድ ፡ በመ ንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም ፡ በመጋቢት ፡ ሃያ ፡ ሁለት ፡ ቀን።
፩፤ በዛቲ ፡ ዕለት ፡ ቦአ ፡ እግዚእ ፡ ኢየሱስ ፡ ኢየሩ ሳሌም ፡ ወየደ ፡ ሆሣዕና ፡ ከመ ፡ ይፈጽም ፡ ትንቢተ ፡ ነቢያት ፡ ዘተነበዩ ፡ በእንቲአሁ ፡ ለለ፡አሐዱ፡አሐዱ፡በዘመኖሙ።	፩፤ በዚች፡ዕለት ጌታችን፡ኢየሱስ፡ወደ፡ኢየሩ ሳሌም፡ገብቶ፡እያንዳንዳቸው፡ነቢያት፡በዘ መናቸው፡ስለእርሱ፡የተናገሩትን፡ይፈጽም፡ ዘንድ፡ሆሣዕናን፡ዘረ።

Scanned by CamScanner

ዘዕለተ፡ሆሣዕና።	የሆሣዕና፡ዕለት።
፭፮፤ ደቂቀ፡ዕብራውያን፡ነሥኡ፡ዐበርተ፡ምስለ፡ዘይት፡ወሰብሑ፡ምስሌሆሙ፡እንዘ፡ይብሉ፡ሆሣዕና፡ለወልደ፡ዳዊት።	፭፮፤ የዕብራውያንም፡ልጆች፡ሰሌንና፡የዘይት፡(ወይራ)፡ዝንጣፊ፡ይዘው፡ለዳዊት ልጅ፡ሆሣዕና፡መባል፡ይገባዋል፡እያሉ፡ከሳቸው፡ጋራ፡አመሰገኑ።
፭፯፤ ዝ፡ውእቱ፡እንጋ፡መሲሕ፡ዘተናገረ፡በእንቲአሁ፡ነቢይ፡ከመ፡ውእቱ፡ይወፅእ፡እምቤተ፡ልሔም፡መኰንን፡ዐቢይ፡ውእቱ፡ይርዕየን፡በበትሩ፡ልዑል፡ወውእቱ፡ይሁብ፡ጎይለ፡ወጽንዐ፡ለሕዝቡ፡እስራኤል።	፭፯፤ ይህ፡ማነው?ስለ፡እርሱ፡ነቢይ፡የተናገረለት፡በከፍተኛ፡ሥልጣኑ፡የሚጠብቀን፡ገሸር፡መኰንን፡ከቤተ፡ልሔም፡ይወጣል፤እርሱም፡ለወገኑ፡ለእስራኤል፡ኃይልና፡ብርታት፡ይሰጣል፡የተባለለት፡መሲሕ፡ይሆን?እንጃ፡አለ።
፭፰፤ ናሁ፡ይጸርሑ፡ቅድሜሁ፡እንዘ፡ይብሉ፡ሆሣዕና፡ለወልደ፡ዳዊት።	፭፰፤ እነሆ፡ለዳዊት፡ልጅ፡ሆሣዕና፡ተብሎ፡መመስገን፡ይገባዋል።እያሉ፡በፊቱ፡ጮኹ።
፭፱፤ ዝንቱ፡እንጋ፡ወልደ፡እግዚአብሔር፡ውእቱ፡ዘመጽአ፡ከመ፡ያድኅን።	፭፱፤ ይህም፡እንጃ፡ወገኖቹን፡ያድን፡ዘንድ፡የመጣ፡የእግዚአብሔር፡ልጅ፡ይሆናል፡አሉ።
፷፤ ወካዕበ፡ሶበ፡ቀርበ፡ኀቢሁ፡ዕውር፡ጸርሐ፡እንዘ፡ይብል፡ተሣሃለኒ፡እግዚእየ፡ኢየሱስ፡ወልደ፡ዳዊት።	፷፤ ዳግመኛም፡ዓይነ፡ሥውር፡ወደእርሱ፡በቀረበ፡ጊዜ፡የዳዊት፡ልጅ፡ጌታዬ፡ኢየሱስ፡ይቅር፡በለኝ፡ብሎ፡ጮኸ።
፷፩፤ ወሰፍሐ፡እዴሁ፡ወነሥአ፡ጽቡረ፡እምድር፡ወቀብዖ፡አዕይንቲሁ፡ወበጊዜሃ፡ርእየ።	፷፩፤ እጁንም፡ዘርግቶ፡ከመሬት፡አፈር፡አንሥቶ፡ጭቃ፡አድርጎ፡ዓይኑን፡ቀባው፡ወዲያውም፡አየ።
፷፪፤ ለምንት፡ክሕድኮ፡አ፡እስራኤል፡ዘኢአእኳቲ፡ናሁ፡ደቂቅከ፡ይሴብሑ፡ቅድሜሁ፡እንዘ፡ይብሉ፡ሆሣዕና፡ለወልደ፡ዳዊት።	፷፪፤ የማታመሰግን፡እስራኤል፡ሆይ፡ለምን፡ካድከው? እነሆ፡ልጆችህ፡ለዳዊት፡ልጅ፡ሆሣዕና፡መባል፡ይገባዋል፡እያሉ፡በፊቱ፡ያመሰግናሉ።
፷፫፤ ወዘኬዎስ፡ሊቀ፡መጸብሓን፡ዘሐጺር፡ቆመ፡ሶበ፡ርእየ፡ብዙኃነ፡እንዘ፡ይተልዉ፡ኀበ፡መድኀኒነ።	፷፫፤ ቁመቱ፡አጭር፡የሆነ፡የግብር፡ሰብሳቢዎች፡አለቃ፡ዘኬዎስ፡መድኃኒታችንን፡ብዙ፡ሰው፡ሲከተለው፡ባየ፡ጊዜ።
፷፬፤ ወበእንተ፡ብዝኀ፡አሕዛብ፡ኢክህለ፡ከመ፡ይርአዮ፡ወአፍጢኖ፡ዘኬዎስ፡ዐርገ፡ዲበ፡ሰግላ፡እስመ፡ውእቱ፡ኮነ፡ይፈቱ፡ከመ፡ይርአዮ፡ለእግዚአብሔር፡ወአርዳኢሁ፡ኀቡረ።	፷፬፤ ስለ፡ሕዝብ፡ብዛትም፡ሊያየው፡አልቻለም። ፈጥኖም፡ከሾላ፡ዛፍ፡ላይ፡ወጣ፡እርሱ፡ጌታን፡ከደቀ፡መዛሙርቱ፡ጋራ፡በአንድነት፡ያየው፡ዘንድ፡ይመኝ፡ነበርና።
፷፭፤ ወሶበ፡ርእዮ፡እግዚአብሔር፡ጸውዖ፡እንዘ፡ይብል፡ዘኬዎስ፡አፍጥን፡ወነዐ፡ረድ፡ኀቤየ፡ዮም፡አነ፡እከውን፡ውስተ፡ቤትከ።	፷፭፤ እግዚአብሔርም፡በአየው፡ጊዜ፡ዘኬዎስ፡ፈጥነህ፡ውረድ፤ወደ፡እኔም፡ና፤እኔ፡ዛሬ፡በቤትህ፡እሆናለሁና፡ብሎ፡ጠራው።
፷፮፤ ወአፍጠነ፡ዘኬዎስ፡ወወረደ፡ኀቤሁ፡ወነሥአ፡ሥርየተ፡ኃጣውኢሁ፡እምኀበ፡ምሕረቱ፡ዐቢይ።	፷፮፤ ዘኬዎስም፡ወደ፡እርሱ፡ፈጥኖ፡ወረደ፤ፍጹም፡ከሆነ፡ምሕረቱም፡የኃጢአቱን፡ሥርየት፡ተቀበለ።
፷፯፤ ወበእንተዝ፡ንሰብሕ፡ምስለ፡ሕፃናተ፡ዕብራውያን፡እንዘ፡ንብል፡ሆሣዕና፡በአርያም፡ለወልደ፡ዳዊት፡ዝንቱ፡ውእቱ፡ንጉሠ፡እስራኤል።	፷፯፤ ስለዚህም፡ከዕብራውያን፡ልጆች፡ጋራ፡ለዳዊት፡ልጅ፡በአርያም፡መድኃኒት፡መባል፡ይገባዋል፡እያልን፡እናመስግን፤ይኸውም፡የእስራኤል፡ንጉሥ፡ነው።

Scanned by CamScanner

ዘዕለተ፡ሆሣዕና።	የሆሣዕና፡ዕለት።
፱፡ ይቤ፡ያዕቆብ፡በእንተ፡ወልዱ፡ዘተመሰለ፡ በክርስቶስ፡ የአስር፡በዕፀ፡ዘይት፡አድጎ፡ ወበሐረገ፡ወይን፡ዕዋለ።	፱፡ በክርስቶስ፡ ስለተመሰለ፡ስለ፡ልጁ፡ይሁዳ፡ ያዕቆብ፡አህያይቱን፡በዘይቱ፡ዕንጨት፡ውር ንጫውን፡በወይን፡ሐረግ፡ያስራል፡አለ።
፲፡ ወካዕበ፡ይቤ፡ዘካርያስ፡ኢትፍርሂ፡ወለተ፡ ጽዮን፡ነዋ፡ንጉሥኪ፡ጻድቅ፡ወመድኀን፡ ወየዋህ፡ይመጽእ፡ወይጼዐን፡ዲበ፡ዕዋል፡ ወዲበ፡እድግት።	፲፡ ዳግመኛም፡ዘካርያስ፡የጽዮን፡ልጅ፡አይዞሽ፡ አትፍሪ፤ እውነተኛ፡ የሚሆን፡ጻድቅ፡ የሚያድን፡የዋህ፡ንጉሥሽ፡ይመጣል፤በውር ንጫይቱና፡በአህያይቱ፡ይቀመጣል፡አለ።
፲፩፡ ወኢሳይያስኒ፡ይቤ፡ይመጽእ፡ንጉሥኪ፡ ጻድቅ፡ወየዋህ፡ዘዕሴቱ፡ምስሌሁ፡ወምግባሩ፡ ቅድመ፡ገጹ፡እንዘ፡ይጼዐን፡ዲበ፡ዕዋለ፡ አድግ።	፲፩፡ ኢሳይያስም፡ጻድቅና፡የዋህ፡የሆነ፡ንጉሥሽ፡ በአህያ፡ ውርንጫ፡ ተቀምጦ፡ይመጣል፡ ዋጋው፡ከርሱ፡ጋራ፡ሥራውም፡በፊቱ፡ነው፡ አለ።
፲፪፡ ወአብርሃምኒ፡ሰመያ፡ለዛቲ፡በዓል፡በዓለ፡ እግዚአብሔር፡ ፍሥሓ፡እስመ፡ዖደ፡ምስዋዐ፡ ነሢኦ፡ፀበርተ፡ተመርት፡ዘበቀልት።	፲፪፡ አብርሃምም፡ ይቺን፡በዓል፡ደስታን፡ የተመላች፡የእግዚአብሔር፡ በዓል፡ናት፡ ብሎ፡ጠራት፤የሰሌን፡ዝንጣፊና፡ዘንባባን፡ ይዞ፡መሠዊያውን፡ዙሮአልና።
፲፫፡ ወዳዊትኒ፡ይቤ፡እምአፈ፡ደቂቅ፡ወሕፃናት፡ አስተዳለውከ፡ስብሐተ።	፲፫፡ ዳዊትም፡ከልጆችና፡ከሕፃናት፡አንደበት፡ ምስጋናን፡አዘጋጀህ፡አለ።
፲፬፡ ወሰሎሞንኒ፡ይቤ፡ልሳናቲሆሙ፡ለሕፃናት፡ ረሰየት፡ርቱዐ።	፲፬፡ ሰሎሞንም፡ የሕፃናት፡ አንደበታቸው፡ የሚገባ፡ምስጋናን፡አደረገች፡አለ።
፲፭፡ ወካዕበ፡ይቤ፡ዘካርያስ፡ይትዋነዩ፡በመርሕባ፡ ለኢየሩሳሌም፡ አዕሩግ፡ወሕፃናት፡ ወሰሉ፡ምርጕዛሙ፡ውስተ፡እደዊሆሙ።	፲፭፡ ዳግመኛም፡ዘካርያስ፡በኢየሩሳሌም፡ አደባባይ፡ ሽማግሌችና፡ሕፃናት፡ ይጫወታሉ፤ ምርኩዛቸውም፡በእጆቻቸው፡ ነው፡አለ።
፲፮፡ ወቦ፡ዘይቤ፡አርሕቢ፡መታክለኪ፡ወአን ጦልዓኒ፡ደባትረኪ።	፲፮፡ የድንኳንሽንም፡መትከያ፡አስፍተሽ፡ድንኳ ንሽን፡ዘርጊ፡ያለም፡አለ።
፲፯፡ ለፈጸሞ፡ዝንቱ፡ነገር፡ቦአ፡እግዚእነ፡ ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ ኢየሩሳሌም፡ተጽዒኖ፡ ዲበ፡እድግት፡ወዲበ፡ዕዋላ።	፲፯፡ ይህንንም፡የትንቢት፡ነገር፡ለመፈጸም፡ጌታ ችን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ በአህያና፡በውር ንጫዋ፡ላይ፡ተቀምጦ፡ወደ፡ኢየሩሳሌም፡ገባ።
፲፰፡ በከመ፡ጽሑፍ፡በወንጌል፡ወቀሪቦ፡ኢየሩ ሳሌም፡መንገለ፡ቤተ፡ፋጌ፡ወቢታንያ፡ኀበ፡ ደብር፡ዘስሙ፡ኤሌዎን፡ፈነወ፡ክልኤተ፡እም አርዳኢሁ፡ወይቤሎሙ፡ሑሩ፡ሀገረ፡ዘቅድ ሜክሙ፡ወበዊአክሙ፡ትረክቡ፡ዕዋለ፡ እሱረ፡ዘኢተጽዕኖ፡ሰብእ፡ፍትሕዎ፡ወአም ጽእዎ፡ሊተ።	፲፰፡ በወንጌል፡እንደተጻፈ፡ኢየሩሳሌም፡ገብቶ፡ ስሙ፡ኤሌዎን፡ከሚባለው፡ተራራ፡አጠገብ፡ ወደ፡ቤተ፡ፋጌና፡ወደ፡ቢታንያ፡በደረሰ፡ጊዜ፡ ከደቀመዛሙርቱ፡ ሁለቱን፡በፊታችሁ፡ ወዳለችው፡መንደር፡ሂዱ፤ገብታችሁም፡ሰው፡ ያልተቀመጠበት፡የታሰረ፡ውርንጫ፡ታገኛ ላችሁ፤ፈታችሁ፡አምጡልኝ፡ብሎ፡ላካቸው።
፲፱፡ ወእመቦ፡ዘይቤለክሙ፡ለምንት፡ትፈትሕዎ፡ በሉ፡እግዚኡ፡ይፈቅዶ።	፲፱፡ ለምን፡ትፈቱታላችሁ፡የሚላችሁ፡ቢኖር፡ ጌታው፡ይሻዋል፡በሉ።
፳፡ ወሐዊሮሙ፡እለ፡ተፈነዉ፡ረከቡ፡በከመ፡ ይቤሎሙ፡ወፈትሑ፡ዕዋለ።	፳፡ የተላኩትም፡ሂደው፡እንዳላቸው፡አገኙ፤ውር ንጫውንም፡ፈቱ።
፳፩፡ ወእንዘ፡ይፈትሑ፡ዕዋለ፡ይቤልዎሙ፡አጋዕ ዝቲሁ፡ለምንት፡ትፈትሕዎ፡ይቤልዎሙ፡ እግዚኡ፡ይፈቅዶ።	፳፩፡ ውርንጫውንም፡ሲፈቱ፡ባለቤቶቹ፡ለምን፡ ትፈቱታላችሁ፡አሏቸው፤ጌታው፡ይሻዋል፡ አሏቸው።

Scanned by CamScanner

ዘዕለተ፡ሰሚዕና።	የሰሚዕና፡ዕለት።
፲፩፤ ወነሥኡ፡ወወሰድዎ፡ኀበ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡ ወረሐኑ ፡ አልባሲሆሙ ፡ ላዕሌሁ ፡ ወአጽ ዐንዎ።	፲፩፤ ይዘውም፡ወደ፡ጌታችን፡ኢየሱስ፡ወሰዱትና፡ በውርንጫው ፡ ላይ ፡ ልብሳቸውን ፡ ጐዝጕዘው፡በዚያ፡ላይ፡አስቀመጡት።
፲፪፤ ወብዙኃን ፡ እለ ፡ ነጸፉ ፡ አልባሲሆሙ ፡ ወቈጽለ፡መቲሮሙ፡ውስተ፡ፍናት።	፲፪፤ ብዙዎችም ፡ ልብሳቸውን ፡ በመንገድ ፡ ላይ ፡ ያነጥፉ፡ነበር፤ሌሎችም፡ቅጠል፡እየዘነጠፉ፡ ይጐዘጕዙ፡ነበር።
፲፫፤ እለኒ ፡ ይመርሑ ፡ ወእለኒ ፡ ይተልዉ ፡ ይኬልሑ፡ ወይብሉ ፡ ሆሣዕና ፡ በአርያም ፡ ቡሩክ ፡ ዘይመጽእ ፡ በስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወቡርክት ፡ እንተ ፡ ትመጽእ ፡ መንግሥት ፡ በስመ፡እግዚአብሔር፡እንተ፡አቡነ፡ዳዊት፡ ሆሣዕና፡በአርያም።	፲፫፤ በፊት ፡ የሚሄዱ ፡ በኋላም ፡ የሚከተሉ ፡ መድኃኒት፡በአርያም፡በእግዚአብሔር፡ስም፡ የሚመጣ ፡ የተባረከ ፡ ነው ፡ እያሉ ፡ ይጮኹ ፡ ነበር ። በእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ የምትመጣ ፡ ያባታችን ፡ የዳዊት ፡ መንግሥትም ፡ የተባ ረከች፡ ናት ፤ መድኃኒት ፡ በአርያም ፡ ይሉ ፡ ነበር።
፲፬፤ ወቦአ ፡ እግዚእ ፡ ኢየሱስ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ውስተ፡ቤተ፡መቅደስ፡ወርእዮ፡ኵሎ፡ሶበ፡ መስየ ፡ ሖረ ፡ ቢታንያ ፡ ምስለ ፡ ዐሠርቱ ፡ ወክልኤቱ፡ሐዋርያት።	፲፬፤ ጌታ ፡ ኢየሱስም ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ሄዶ ፡ ወደ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ገባ ፤ ሁሉንም ፡ አየና ፡ በመሸ ፡ ጊዜ ፡ ከዐሥራ ፡ ሁለቱ ፡ ሐዋርያት ፡ ጋር፡ወደ፡ቢታንያ፡ሄደ።
፲፭፤ ወበሳኒታ ፡ ወሚአ ፡ እምቢታንያ ፡ ርኀበ ፡ ወርእየ፡ በለሰ ፡ እምርኁቅ ፡ ወባቲ ፡ ቈጽል ፡ ወሖረ ፡ ይርአይ ፡ እመቦ ፡ ዘይረክብ ፡ ፍሬ ፡ በውስቴታ።	፲፭፤ በነጋውም ፡ ከቢታንያ ፡ በወጣ ፡ ጊዜ ፡ ተራበ ፤ በለስንም ፡ ከሩቅ ፡ አየ ፤ ቅጠል ፡ ነበራት ፡ በውስ ጥዋም ፡ የሚያገኘው ፡ ፍሬ ፡ እንዳለ ፡ ሊያይ ፡ ሄደ።
፲፮፤ ወበጺሖ፡ኀቤሃ ፡ አልቦ ፡ ዘረከበ ፡ ዘእንበለ ፡ ቈጽል ፡ ባሕቲታ ፡ እስመ ፡ ኢኮነ ፡ ጊዜሁ ፡ ለበለስ።	፲፮፤ ወደ ፡ እርስዋም ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ ከቅጠል ፡ በቀር፡ያገኘው፡የለም፤ጊዜው፡የበለስ፡አልነ በረምና።
፲፯፤ ወአውሥአ ፡ ወይቤላ ፡ ለዓለም ፡ አልቦ ፡ ዘይበልዕ ፡ ፍሬ ፡ እምኔኪ ፡ እስከ ፡ ለዓለም ፤ ወሰምዕዎ፡አርዳኢሁ።	፲፯፤ ጌታም ፡ መልሶ ፡ ለዘላለም ፡ ካንቺ ፡ ፍሬ ፡ የሚበላ፡አይኑር፡አላት፤ደቀ፡መዛሙርቱም፡ ሰሙ።
፲፰፤ ወበጽሐ፡ኢየሩሳሌም፡ወቦአ፡ቤተ፡መቅደስ፡ ወአኀዘ ፡ ይስድዶሙ ፡ ለእለ ፡ ይሠይጡ ፡ ወይሣየጡ፡በምኵራብ።	፲፰፤ ኢየሩሳሌም ፡ በደረሰም ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ፡ገብቶ፡በምኵራብ፡የሚሸጡትንና፡ የሚገዙትን፡ያባረራቸው፡ጀመር።
፲፱፤ ወገፍትዐ፡ማእዳቲሆሙ፡ለመወልጣን፡ወመ ናብርቲሆሙ፡ለእለ፡ይሠይጡ፡ርግበ።	፲፱፤ የለዋጭዎችንም፡መደርደሪያቸውን፤ርግብ፡ የሚሸጡትንም፡ወንበሮቻቸውን፡ገለበጠ።
፳፤ ወከልኦ ፡ ከመ ፡ አልቦ ፡ ዘያኀልፍ ፡ እንተ ፡ ምኵራብ፡ንዋየ።	፳፤ በምኵራብም ፡ በኩል ፡ ገንዘብን ፡ የሚያስተ ላልፍ፡እንዳይኖር፡ከለከለ።
፳፩፤ ወመሀሮሙ ፡ ወይቤሎሙ ፡ አኮኑ ፡ ዘይብል ፡ ጽሑፍ ፡ ቤትየሰ ፡ ቤተ ፡ ጸሎት ፡ ይሰመይ ፡ ለኵሉ፡አሕዛብ።ወአንትሙሰ፡ረሰይክምዎ፡ በእተ፡ፈያት፡ወሰረቅት።	፳፩፤ እንዲህ ፡ ብሎም ፡ አስተማራቸው ፤ ቤቴ ፡ ለአሕዛብ ፡ ሁሉ ፡ የጸሎት ፡ ቤት ፡ ይሁን ፡ የሚል፡ ተጽፎ ፡ የለምን? እናንተ ፡ ግን ፡ የሌቦችና፡የቀማኞች፡ዋሻ፡አደረጋችሁት።
፳፪፤ ወዮሐንስኒ፡ይቤ፡እምድኅረ፡አንሥኡ፡ለአል ዓዛር ፡ ወበሳኒታ ፡ ብዙኃን ፡ ሰብእ ፡ እለ ፡ መጽኡ፡ለበዓል፡ሶበ፡ሰምዑ፡ከመ፡ይመጽእ፡	፳፪፤ ዮሐንስም ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤ አልዓዛርን ፡ በማግሥቱ ፡ ካስነሣው ፡ በኋላ ፡ ለበዓል ፡ መጥተው ፡ የነበሩ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ጌታችን ፡

Scanned by CamScanner

ዘዕለተ፡ሆሣዕና።	የሆሣዕና፡ዕለት።
እግዚእ፡ኢየሱስ፡ነሥኡ፡ዐበርተ፡ተመርት፡ዘበቀልት፡እምኢየሩሳሌም፡ወተቀበልዎ፡ሕዝብ፡ብዙኃን፡ወሚአሙ፡እንዘ፡ይብሉ፡ሆሣዕና፡በአርያም፡ቡሩክ፡ዘይመጽእ፡በስመ፡እግዚአብሔር፡ወንጉሦሙ፡ለእስራኤል።	ኢየሱስ፡ወደ፡ኢየሩሳሌም፡እንደሚመጣ፡በሰሙ፡ጊዜ፡የሰሌን፡ዛፍ፡ዝንጣፊ፡ይዘው፡በእግዚአብሔር፡ስም፡የሚመጣ፡ቡሩክ፡ነው፡"መድኃኒት፡በአርያም" ፡የእስራኤል፡ንጉሣቸው፡እያሉ፡ወጥተው፡ብዙ፡ሕዝቦች፡ተቀበሉት።
፳፯፤ ወረከበ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡ዕዋለ፡አድግ፡ወተጽዕነ፡ላዕሌሁ፡በከመ፡ጽሑፍ፡ዘይብል፡ኢትፍርሂ፡ወለተ፡ጽዮን፡ነዋ፡ንጉሥኪ፡በጽሐ፡እንዘ፡ይጼዓን፡ዲበ፡ዕዋለ፡አድግ።	፳፯፤ የጽዮን፡ልጅ፡ሆይ፡አትፍሪ፡እነሆ፡ንጉሥሽ፡በአህያ፡ግልገል፡ተቀምጦ፡ይመጣል፡ተብሎ፡እንደ፡ተጻፈ፡ጌታችን፡ኢየሱስ፡የአህያ፡ግልገል፡አግኝቶ፡በእርሱ፡ላይ፡ተቀመጠ።
፳፰፤ ወዘንተሰ፡ኢያእመሩ፡አርዳኢሁ፡እምትካት፡ዘእንበለ፡አመ፡ተሰብሐ እግዚእ፡ኢየሱስ።	፳፰፤ ጌታችን፡ኢየሱስ፡ከተመሰገነበት፡ጊዜ፡በቀር፡አስቀድሞ፡ደቀ፡መዛሙርቱ፡ይህን፡ነገር፡አላወቁም፡ነበር።
፳፱፤ አሜሃ፡ተዘከሩ፡አርዳኢሁ፡ከመ፡ጽሑፍ፡በእንቲአሁ፡ዝንቱ፡ከመዝ፡ገብሩ፡ሎቱ።	፳፱፤ ያን፡ጊዜ፡ግን፡ይህ፡ስለርሱ፡እንደተጻፈ፡አሰቡ፤እንዲሁም፡አደረጉለት።
፴፤ ወሰማዕተ፡ኮንዎ፡እሙንቱ፡ሕዝብ፡እለ፡ሀለዉ፡ሀየ፡ኀቤሁ፡ምስሌሁ፡ከመ፡ውእቱ፡ጸውዖ፡ለአልዓዛር፡እመቃብር፡ወአንሥኦ፡እምነ፡ምውታን።	፴፤ ከዚያም፡አብረውት፡የነበሩ፡ሕዝብ፡አልዓዛርን፡ከመቃብር፡እንደጠራው፡ከሙታንም፡ለይቶ፡እንዳስነሳው፡መሰከሩለት።
፴፩፤ በእንተ፡ዝንቱ፡ተቀበልዎ፡እሙንቱ፡ሰብእ፡ሰሚዖሙ፡ዘገብረ፡ተአምራተ፡ወዘንተሂ፡መንክረ።	፴፩፤ ስለዚህም፡እነዚህ፡ሰዎች፡ያደረገውን፡ተአምራት፡ይህንንም፡ድንቅ፡ሥራ፡ሰምተው፡ተቀበሉት።
፴፪፤ ወይቤሉ፡ፈሪሳውያን፡በበይናቲሆሙ፡ትሬእዩ፡እንከ፡ከመ፡አልቦ፡ዘንበቍዕ፡ናሁ፡ኵሉ፡ዓለም፡ተለዎ፡ድኅሬሁ።	፴፪፤ ፈሪሳውያንም፡እርስ፡በርሳቸው፡ምንም፡የምናደርገው፡እንዴለ፡ታያላችሁን? እነሆ፡ዓለም፡ሁሉ፡በኋላው፡ተከትሎታል፡አሉ።
፴፫፤ እስመ፡ማቴዎስ፡ወማርቆስ፡ኢዘከሩ፡ግብራ፡ለተመርት፡አላ፡ይቤሉ፡ወካልኣን፡መተሩ፡አዕጹቀ፡እምውስተ፡ዕፀው፡ወነጸፉ፡ውስተ፡ፍናት።	፴፫፤ ማቴዎስና፡ማርቆስ፡የዘንባባን፡ነገር፡አላስታወሱም፤ሌሎች፡ከዛፍ፡ላይ፡ቅርንጫፍ፡ዘንጥፈው፡በመንገድ፡ላይ፡ጐዘጕዙ፡አሉ፡እንጂ።
፴፬፤ ወሎቃስኒ፡ኢዘከረ፡አዕጹቀ፡ወኢተመርተ፡አላ፡ይቤ፡እንዘ፡የሐውሩ፡ይነጽፉ፡አልባሲሆሙ፡ውስተ፡ፍናት።	፴፬፤ ሉቃስም፡ዝንጣፊውንም፡ሆነ፡ዘንባባውን፡አላወሳም፤ ሲሄዱም፡ልብሳቸውን፡በመንገድ፡ላይ፡ያነጥፉ፡ነበር፡አለ፡እንጂ።
፴፭፤ ዮሐንስሰ፡ይቤ፡ባሕቲቶ፡ነሥኡ፡ዐበርተ፡ተመርት፡ዘበቀልት፡እምኢየሩሳሌም።	፴፭፤ ዮሐንስ፡ግን፡ብቻውን፡የሰሌን፡ዛፍ፡ዝንጣፊ፡ከኢየሩሳሌም፡ያዙ፡አለ።
፴፮፤ እስመ፡በቀልትሰ፡ኢሀለው፡ውስተ፡ኢየሩሳሌም፡አላ፡አመ፡ሕፃን፡ውእቱ፡እግዚእነ፡አመ፡ወረደ፡ምድረ፡ግብጽ፡ምስለ፡እሙ፡ቅድስት፡ማርያም፡በጽሑ፡ምድረ፡እስሙናይን፡ወረከቡ፡በሀየ፡ተመርተ።	፴፮፤ ሰሌን፡በኢየሩሳሌም፡የለም፡ነበርና፡ጌታችን፡በሕፃንነቱ፡ከእናቱ፡ከክብርት፡ድንግል፡ማርያም፡ጋር፡ወደ፡ግብጽ፡ምድር፡በወረደ፡ጊዜ፡እስሙናይን፡ከተባለ፡አገር፡ደረሱ፤በዚያም፡ሰሌን፡አገኙ።
፴፯፤ ወአዘዛ፡እግዚእነ፡ከመ፡ትትመላኅ፡እምሥ	፴፯፤ ጌታችንም፡ከሥርዋ፡ተነቅላ፡በደብረ፡ዘይት፡

Scanned by CamScanner

ዘዕለተ፡ሆሣዕና።	የሆሣዕና፡ዕለት።
ረዊሃ፡ወትተከል፡መልዕልተ፡ደብረ፡ዘይት።	ተራራ፡ላይ፡ትተከል፡ዘንድ፡አዘዛት።
፴፰፤ አሜሃ፡ሰረረት፡ውስተ፡አየር፡ወተተከለት፡ሀየ።	፴፰፤ ያን፡ጊዜም፡ወደ፡አየር፡ወጥታ፡በረረች፤ በደብረ፡ዘይትም፡ላይ፡ተተከለች።
፴፱፤ ወእምኔሃ፡ነሥኡ፡አቍጽለ፡ወተቀበልዎ፡ ለእግዚእነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡እስመ፡ አርአየ፡ዐይተ፡ሆሣዕና።	፴፱፤ ከእርስዋም፡ዘንባባ፡ወስደው፡ጌታችን፡ ኢየሱስ፡ክርስቶስን፡ተቀበሉት፤ ሥርዓተ፡ ሆሣዕናን፡እየዞረ፡አሳይቷልና።
፵፤ ወአሜሃ፡አኀዘሙ፡ቅንአት፡ለሕዝበ፡ አይሁድ፡ወኀሠሡ፡በዘይቀትልዎ፡ለእግ ዚእነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ።	፵፤ ያን፡ጊዜም፡አይሁድን፡ቅናት፡ያዛቸው፤ ጌታችን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስን፡የሚገድሉበ ትንም፡ምክንያት፡ፈለጉ።
፵፩፤ ሣህሉ፡ወምሕረቱ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ ዓለም፡አሜን።	፵፩፤ ይቅርታው፡ቸርነቱ፡ከኛ፡ጋራ፡ለዘላለሙ፡ ይኑር፡አሜን።
ሰላም፡ለዕርገትከ፡ወለበአትከ፡ማእከላ። በተጽዕኖ፡እድግት፡ምስለ፡ዕዋላ። ኢየሩ ሳሌም፡አሜሃ፡ኢያእመረት፡መዋዕለ፡ ሣህላ። ሀገርኒ፡ተሀውከት፡ኵላ። መኑ፡ ውእቱ፡ኪያከ፡ብሂላ።	ከውርንጫዋ፡ጋራ፡በአህያይቱ፡ላይ፡በመ ቀመጥ፡ለመውጣትህና፡ወደ፡ማኸሏ፡ለመግባ ትህ፡ሰላምታ፡ይገባል። ኢየሩሳሌም፡ያን፡ጊዜ፡ የይቅርታዋን፡ወራት፡አላወቀችም፤ ሀገሪቱም፡ በመላዋ፡አንተን፡ማነው፡አሱ?ብላ፡ተሸበረች።
ትእዛዝ።	ትእዛዝ።
ምንተኑ፡አዐስየኪ፡በል፤እስከ፡ተፍጸሜቱ፡ ወመቅድመ፡ተአምሪሃ፡ለድንግል፡በከመ፡ ተጽሕፈ፡ቀዳሚ፡በማኅትወ፡ዝንቱ፡ዕለት።	ምንተኑ፡አዐስየኪ፡እስከ፡መጨረሻው፡በል፡ የድንግልን፡የተአምርዋን፡መቅድም፡ አስቀድሞ፡በዚሁ፡ቀን፡ዋዜማ፡እንደ፡ ተሠራ፡ፈጽም።
ተአምሪሃ፡ለእግዝእትነ፡ቅድስት፡ድንግል፡ በከልኤ፡ማርያም፡ወላዲተ፡አምላክ።ዘከመ፡ ተናገረ፡መንፈስ፡ቅዱስ፡በእንተ፡ክብራ፡ለእ ግዝእትነ፡ቅድስት፡ድንግል፡በከልኤ፡ ማርያም፡ጸሎታ፡ወበረከታ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።	ልመናዋ፡፡ክብርዋ፡ከእኛ፡ጋራ፡ለዘላለሙ፡ ይደርብንና፡በሁለት፡ወገን፡ድንግል፡ ስለሆነች፡ስለ፡እመቤታችን፡ስለ፡ቅድስት፡ ድንግል፡ማርያም ስለ፡ክብርዋ፡መንፈስ፡ ቅዱስ፡የተናገረላት፡ተአምር፡ይህ፡ ነው።
፩፤ ወእምዝ፡እምድኅረ፡አስተርአየ፡ዝንቱ፡ ተአምር፡ላእለ እግዝእትነ፡ወላእለ፡አርድእት፡ ተናገረ፡መንፈስ፡ቅዱስ። ወይቤ፡አእምሩኬ፡ ከመ፡በዕለተ፡እሑድ፡አብሠራ፡ገብርኤል፡ መልአክ፡ለማርያም፡ቅድስት፡ከመ፡የኀድር፡ ክርስቶስ፡ቃለ፡እግዚአብሔር፡ላዕሌሃ።	፩፤ አሁንም፡ይኸ፡ምልክት፡በእመቤታችንና፡ በሐዋርያት፡ላይ፡ከተገለጠ፡በኋላ፡መንፈስ፡ ቅዱስ፡ተናገረ፤ የእግዚአብሔር፡አካላዊ፡ ቃል፡ክርስቶስ፡ከእርስዋ፡እንደሚወለድ፡ በእሑድ፡ቀን፡ቅድስት፡ማርያምን፡ ገብርኤል፡እንዳበሠራት፡እወቁ፡አለ።
፪፤ ወበዕለተ፡እሑድ፡ወዕኡ፡አዕሩግ፡ወሕፃናት፡ ከመ፡ይትቀበልዎ፡ለእግዚእነ፡ኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡እንዘ፡ይብሉ፡ሆሣዕና፡በአርያም፡ ቡሩክ፡ዘይመጽእ፡በስመ፡እግዚአብሔር።	፪፤ በእሑድ፡ቀንም፡ጌታችን፡ኢየሱስ፡ክርስ ቶስን፡ከአርያም፡የተገኘ፡መድኃኒት፡በእግዚ አብሔር፡ስም፡የሚመጣ፡ቡሩክ፡ነው፡እያሉ፡ ሽማግሌዎችና፡ሕፃናት፡ሊቀበሉት፡ወጡ።
፫፤ ወበዕለተ፡እሑድ፡ተንሥአ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡እሙታን።	፫፤ በዚሁ፡በእሑድ፡ቀን፡ጌታችን፡ኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ከሙታን፡ተለይቶ፡ተነሣ።

Scanned by CamScanner

ዘዕለተ፡ሆሣዕና።

፩፤ ወበዕለተ፡እሑድ፡መጽአ፡በእንተ፡ዕበያ፡ወክብራ፡ለፀዓተ፡ነፍሳ፡ለማርያም፡እምዝ፡ዓለም።

፪፤ ወሶበ፡ኮነ፡ዕለተ፡እሑድ፡ትቤሎሙ፡እግዝእትነ፡ማርያም፡ለአርድእት፡እስመ፡እግዚእነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ይመጽእ፡ኀቤየ፡ምስለ፡ኵሎሙ፡መላእክቲሁ።

፫፤ ወእንዘ፡ትትናገር፡ምስሌሆሙ፡ናሁ፡መጽአ፡እግዚእነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ወመላእክቲሁ፡ምስሌሁ፡እንዘ፡ይነብር፡ዲበ፡መንበረ፡ስብሐቲሁ።

፬፤ ወአስተርአዩ፡ቅድሜሁ፡መላእክት፡እለ፡አልቦሙ፡ጎልቍ።

፭፤ ወዓዲ፡አስተርአየ፡ብርሃን፡ዐቢይ፡ላዕለ፡ቅድስት፡ወክብርት፡ፈድፋደ፡በምጽአቱ፡ለወልደ፡አምላክ።

፮፤ ወሰገዱ፡ላቲ፡ኵሎሙ፡ኃይለ፡ሰማያት፡ወመጽአ፡ቃል፡ኀበ፡ቅድስት፡ዘይብል፡አ፡ማርያም፡አውሥአት፡ወትቤ፡ነየ።

፯፤ ዳግመ፡ይቤላ፡ተፈሥሒ፡ወተሐሠዪ፡ወትትሐሠይ፡ነፍስኪ፡በኀቤየ፡በዐቢይ፡ክብር።

፰፤ ርእዩኪ፡ፍቁራንየ፡ደቂቀ፡ወንጌል፡ዘከመ፡ይነግር፡ክብራ፡መንፈስ፡ቅዱስ፡ለእግዝእትነ፡ማርያም፡ድንግል፡ወላዲተ፡አምላክ።

፱፤ ጸሎታ፡ወበረከታ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ለተአምርኪ፡ማርያም፡ክብር፡ይደሉ።
ለወልድኪ፡ከመ፡ወንጌሉ።እስመ፡ምክሐ፡ጸድቃን፡ውእቱ፡ወተስፋ፡ኀጥኣን፡ኵሉ።ዘያሰትሰ፡ወያስተሐቅር፡እምቃሉ።እምነ፡ልብኪ፡ኢይፃእ፡በቀሉ።ሃሌ፡ሉያ፡በብዝኃ፡ጎሩትኪ፡በል፤ወላዲተ፡አምላክ፡ማርያም፡በል፤ስብሐት፡ለኪ፡በል።

መቅድመ፡ተአምሪሁ፡በከመ፡ተጽሕፈ፡ቀዳሚ፡በማኅተወ፡ዝንቱ፡ዕለት፡በል።

ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ጥዑመ፡ስም፡በል።

ተአምር፡ወመንክር፡ዘገብረ፡እግዚእነ፡ወአምላክነ፡ወመድኀኒነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡

የሆሣዕና፡ዕለት።

፩፤ አሁንም፡ከዚህ፡ዓለም፡የእመቤታችን፡የማርያም፡ነፍሷ፡ከሥጋዋ፡በምትለይ፡ጊዜ፡ስለ፡ክብርዋና፡ስለ፡ልዕልናዋ፡በእሑድ፡ቀን፡መጣ።

፪፤ የእሑድ፡ዕለት፡በሆነ፡ጊዜም፡እመቤታችን፡ማርያም፡ከመላእክቱ፡ሁሉ፡ጋር፡ጌታችን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ወደ፡እኔ፡ይመጣል፡ብላ፡ለሐዋርያት፡ነገረቻቸው።

፫፤ ከእርሳቸው፡ጋራ፡ስትነጋገርም፡እነሆ፡ጌታችን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ከመላእክቱ፡ጋራ፡ሁኖ፡በጌትነቱ፡ዙፋን፡ላይ፡ተቀምጦ፡መጣ።

፬፤ በፊቱም፡ስፍር፡ቍጥር፡የሌላቸው፡መላእክት፡ታዩ።

፭፤ እንደገናም፡ክብርት፡ቅድስት፡በምትሆን፡በእመቤታችን፡ላይ፡የአምላክ፡ልጅ፡በመምጣቱ፡እጅግ፡ታላቅ፡ብርሃን፡ተገለጠ።

፮፤ የሰማይም፡ሠራዊት፡ሁሉ፡ሰገዱላት፤ወደ፡ቅድስት፡እመቤታችንም፡ማርያም፡ሆይ! የሚል፡ቃል፡መጣ፤እርስዋም፡እነሆኝ፡አለሁ፡ብላ፡መለሰች።

፯፤ ዳግመኛም፡ፈጽሞ፡ደስ፡ይበልሽ፤ነፍስሽም፡በእኔ፡ዘንድ፡በታላቅ፡ክብር፡ደስ፡ትሰኝ፡አላት።

፰፤ የወንጌል፡ልጆች፡ወዳጆቼ፡ሆይ፡አምላክን፡የወለደች፡የእመቤታችን፡የድንግል፡ማርያምን፡ክብርዋን፡መንፈስ፡ቅዱስ፡እንደሚናገር፡እወቁ።

፱፤ ልመናዋ፡ክብርዋ፡በእኛ፡ላይ፡ለዘላለሙ፡ይደርብን፡አሜን።

ማርያም፡ሆይ፡የልጅሽ፡ወንጌል፡እንደከበረ፡ለተአምርሽ፡ክብር፡ይገባል።እርሱም፡የጻድቃን፡መመኪያ፡የኀጥኣን፡ሁሉ፡ተስፋ፡ነውና።ከቃሉ፡የተነሣ፡የሚያቃልልና፡የሚንቅ፡ቢኖር፡ግን፡ከልብሽ፡የሱ፡በቀል፡አይውጣ፤ሃሌ፡ሉያ፡በቸርነትሽ፡ብዛት፡የሚለውን፡በል።ወላዲተ፡አምላክ፡ማርያም፡በል።ስብሐት፡ለኪ፡በል።
በዚሁ፡ዕለት፡ዋዜማ፡እንደተጻፈ፡የተአምሩን፡መቅድም፡በል።

ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ጥዑመ፡ስም፡በል።

ጌታችን፡አምላካችንና፡መድኃኒታችን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ሐዋርያት፡ውርንጫ፡እንዳ

Scanned by CamScanner

ዘዕለተ፡ሆሣዕና።	የሆሣዕና፡ዕለት።
ዘከመ ፡ አምጽኡ ፡ ለሙ ፡ ሐዋርያት ፡ ዕዋለ ፡ ወተጽዕነ ፡ ቦቱ ፡ ወቦአ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ። ሣህሉ፡ወምሕረቱ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።	መጡለትና ፡ በላዩ ፡ ተቀምጦ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ እንደገባ ፡ ያደረገው ፡ ድንቅ ፡ ተአምር፡ይህ ፡ነው ። ይቅርታውና ፡ቸርነቱ ፡ ከእኛ፡ጋራ፡ለዘላለሙ፡ይኑር፡አሜን።
፩፤ ወተመይጡ ፡ ሐዋርያት ፡ ኀበ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እንዘ ፡ ምስሌሆሙ ፡ ውእቱ፡ዕዋል።	፩፤ ሐዋርያትም ፡ ውርንጫውን ፡ ይዘው ፡ ወደ ፡ ጌታችን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ተመለሱ።
፪፤ ወሶበ፡ርእዩ፡ዙሎሙ፡አርዳኢሁ፡እለ፡ነበሩ፡ምስሌሁ፡ነሥኡ፡አልባሲሆሙ፡ወወደይዎ፡ላዕለ ፡ ዕዋል ፡ ወተጽዕነ ፡ ዲቤሁ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ወቦአ ፡ ደብረ ፡ ዘይት ፡ ወእምህየ፡ሖረ፡መንገለ፡ኢየሩሳሌም።	፪፤ ከእርሱ ፡ ጋራ ፡ የነበሩ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ በአዩ፡ጊዜ ፡ ልብሳቸውን ፡ ወስደው ፡ በውርንጫው፡ላይ፡ጎዘጎዙ፤ጌታችን ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስም፡በላዩ፡ተቀምጦ፡ወደ፡ደብረ፡ዘይት፡ገባ፤ከዚያም፡ወደ፡ኢየሩሳሌም፡ሄደ።
፫፤ ወበይእቲ ፡ ጊዜ ፡ ርእዩ ፡ አርድእት ፡ ጎዋጎወ ፡ ሰማይ፡ርጎወ።	፫፤ በዚያችም ፡ ሰዓት ፡ ሐዋርያት ፡ የሰማይ ፡ በር ፡ ተከፍቶ፡አዩ።
፬፤ ወዓዲ፡ርእይዋ፡ለገዳም፡እንተ፡ሀለወት፡ሀየ፡ጻዕደወት ፡ ወበርሀት ፡ ወርእይዎ ፡ ለፀሐይ ፡ እንዘ፡ይሰግድ፡ቅድሜሁ፡ለዕዋል፡ዘተጽዕኖ፡እግዚእነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ።	፬፤ ዳግመኛም ፡ በዚያ ፡ ያለች ፡ ገዳም ፡ ብርሀት ፡ ጽድልት፡ሁና፡አዩዋት፤ፀሐይንም፡ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በተቀመጠበት ፡ ውርንጫ፡ፊት፡ሲሰግድ፡አዩት።
፭፤ ወመላእክትሂ ፡ ወረዱ ፡ እምሰማይ ፡ ምድረ ፡ ወየድዎ፡ለዕዋል።	፭፤ መላዕክትም ፡ ከሰማይ ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ ወርደው፡ውርንጫውን፡ከበቡት።
፮፤ ወእምብርሃነ ፡እግዚእነ ፡ኢየሱስ ፡ክርስቶስ ፡ በርሀት ፡ ኵላ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ እስከ ፡ ኀለዩ ፡ ሰብአ፡ ሀገር ፡ ከመ ፡ ውዕየት ፡ ኢየሩሳሌም።	፮፤ ከጌታችን ፡ ከኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ብርሃን ፡ የተነሣ ፡ የሀገሩ ፡ ሰዎች ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ተቃጠለች ፡ ብለው ፡ እስከ ፡ አሰቡ ፡ ድረስ ፡ መላዋ፡ኢየሩሳሌም፡በራች።
፯፤ ወወፅኡ፡እምአብድንቲሆሙ፡ከመ፡ይርአዩ፡መንክረ፡ዘዐደሞሙ።	፯፤ ደስ፡የሚያሰኝ፡ድንቅ፡ተአምርን፡ያዩ፡ዘንድ፡ከበድን፡ልቡናቸው፡ተለይተው፡ወጡ።
፰፤ ወአንስትሂ ፡ ወፅአ ፡ ምስለ ፡ ደቂቆን ፡ ወሕፃናቲሆን ፡ ወረከብዎ ፡ ለእግዚእነ ፡ እንዘ ፡ ይጼዓን፡ዕዋለ።	፰፤ ሴቶችም ፡ ከልጆቻቸውና ፡ ከሕፃናቶቻቸው ፡ ጋራ ፡ ወጡ፤ጌታችንንም ፡ በውርንጫ ፡ ላይ ፡ ተቀምጦ፡አገኙት።
፱፤ ወደቂቅሰ፡ወሕፃናት፡ርእዩ፡ብርሃነ፡በላዕለ፡እግዚእነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ።	፱፤ ልጆችና፡ሕፃናት፡ግን፡በጌታችን፡በኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ላይ፡ያለውን፡ብርሃን፡አዩ።
፲፤ ወርእይዎሙ፡ለመላእክት፡እንዘ፡የዐውድዎ፡ለዕዋል ፡ ወሶቤሃ ፡ ወረደ ፡ ላዕሌሆሙ ፡ መንፈሰ፡ጽድቅ፡ዘትንቢት።	፲፤ መላእክትንም፡ውርንጫውን፡ከበውት፡አዩአቸው፤ያን፡ጊዜም፡ዕውነተኛ፡ትንቢት፡የሚያናግር፡የእውነት፡መንፈስ፡በላያቸው፡ወረደ።
፲፩፤ ወሐሩ፡ፍጡነ፡ኀበ፡ዕፀወ፡ሆሣዕና፡ወዘይት፡ወመተሩ፡አዕጹቀ፡እምኔሆሙ።	፲፩፤ ፈጥነውም፡ወደ፡ወይራና፡ወደ፡ዘንባባ፡ዛፍ፡ሂደው፡ቅርንጫፉን፡ቆረጡ።
፲፪፤ ወጸሩ ፡ በእደዊሆሙ ፡ ወይቤሉ ፡ በልዑል ፡ ቃል፡ሆሣዕና ፡በአርያም ፡ሆሣዕና ፡ለወልደ ፡ዳዊት፡ሆሣዕና ፡ቡሩክ ፡ዘይመጽእ ፡ዘሀሎ ፡ውስተ ፡ አርያም ፡ዘመጽአ ፡ኀቤነ ፡ይእዜ ፡በፍኖ ፡ትስብእት። ወካዕበ ፡ይመጽእ ፡በስመ ፡እግዚአብሔር።	፲፪፤ በእጆቻቸውም ፡ ዝንጣፊውን ፡ ይዘው ፡ በታላቅ፡ ቃልም ፡ መድኃኒት ፡ በአርያም ፡ ለዳዊት፡ልጅ፡መድኃኒት፡መባል፡ይገባዋል። ሰው፡ሆኖ፡ወደ፡እኛ፡ዛሬ፡የመጣ፡መድኃኒት፡ቡሩክ ፡ነው ፡እያሉ ፡አመሰገኑ ። ዳግመኛም ፡ በእግዚአብሔር፡ስም፡ይመጣል።
፲፫፤ ወተደመረ ፡ ስብሐተ ፡ ሕፃናት ፡ ምስለ ፡ ስብሐተ ፡ መላእክት ፡ ወደምፀት ፡ ኵላ ፡ ሀገረ	፲፫፤ የሕፃናቱም ፡ምስጋና ፡ከመላእክት ፡ምስጋና ፡ጋራ ፡ አንድ ፡ ሆነ ፤ የመላዋ ፡ የኢየሩሳሌም ፡

Scanned by CamScanner

ዘዕለተ፡ሆሣዕና።

ኢየሩሳሌም ፡ ወርዕዱ ፡ እለ ፡ የኀድሩ ፡ ውስቴታ።

፲፬፤ ወወፅኡ፡ረበናተ፡አይሁድ፡ከመ፡ይጠይቁ፡ ግብረ ፡ ይእቲ ፡ ድንፅ ፡ ወጽራሕ ፡ ወርእዩ ፡ ስብሐተ፡ዐቢየ፡ወቅዱሰ።

፲፭፤ ወይቤልዎሙ፡ለሕፃናት፡መኑ፡መሀረክሙ፡ ዘንተ ፡ ስብሐተ ፡ ዘትሴብሑ ፡ ቦቱ ፡ ወልዶ ፡ ለዮሴፍ።(ለሙቱ፡ስብሐት።)

፲፮፤ እስመ፡ዝንቱ፡ስብሐት፡ኢይደሉ፡ዘእንበለ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ባሕቲቱ ፡ ወመኑ ፡ ውእቱ ፡ ዝንቱ፡ንጉሥ፡ዘይመጽእ።

፲፯፤ ወይቤልዎሙ፡ሕፃናት፡ለረበናተ፡አይሁድ፡ ዕውራነ ፡ አዕይንት ፡ ወአልባብ ፡ ኢትሬእይ ዎሙኑ ፡ ለእሉ ፡ መላእክት ፡ ዘከመ ፡ ይሰግዱ ፡ ለወልደ ፡ ማርያም ፡ ድንግል ፡ ወኢትሬእ ይዎኑ፡ለፀሐይ፡ዘከመ፡ኮነ፡ከመ፡ምድር።

፲፰፤ ኢያንበብክሙኑ ፡ ትንቢተ ፡ ዳዊት ፡ ነቢይ ፡ ዘይቤ ፡ እምአፈ ፡ ደቂቅ ፡ ወሕፃናት ፡ አስተዳሎከ፡ስብሐተ።

ወይቤልዎሙ ፡ ረበናት ፡ መኑ ፡ መሀረክሙ ፡ ትጹሩ ፡ ቅድሜሁ ፡ አዕጹቀ ፡ ዘይት ፡ ወበቀልት።

፲፱፤ አውሥኡ፡ሕፃናት፡ወይቤሉ፡እስመ፡ዳዊት፡ ነቢይ፡መሀረነ፡ወተነበየ፡ለነ፡በእንተ፡እሉ፡ አዕጹቅ።

፳፤ አእምሩ ፡ አ ፡ ዕውራን ፡ እስመ ፡ ዝንቱ ፡ ዘይመጽእ ፡ ተጽዒኖ ፡ ዲበ ፡ ዕዋል ፡ መሲሐ ፡ እግዚአብሔር ፡ ውእቱ።

ወውእቱ ፡ ወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቀዳማዊ ፡ መጽአ፡ይእዜኒ፡ለመድኃኒትነ።

፳፩፤ ወውእቱ ፡ ወልዳ ፡ ለእግዝእትነ ፡ ቅድስት ፡ ድንግል፡በክልኤ፡ማርያም፡በሥጋ።

፳፪፤ ወኢያንበብክሙኑ ፡ ትንቢተ ፡ ዘካርያስ ፡ ነቢይ፡ ዘይቤ ፡ ተፈሥሒ ፡ ወለተ ፡ ጽዮን ፡ ወተሐሠዪ ፡ ወለተ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ነዋ ፡ ይመጽእ ፡ ንጉሥኪ ፡ የዋህ ፡ ወትሑት ፡ ተጽዒኖ፡ዲበ፡ዕዋለ፡አድግ።ዘካ፡፱፡፱።

፳፫፤ ጎድጉ ፡ እምኔከሙ ፡ ዘንተ ፡ ቅንአተ ፡ ወመዓተ።

፳፬፤ አእምሩ ፡ ከመ ፡ ዝንቱ ፡ ውእቱ ፡ ፈራቂሁ ፡ ለዓለም ፡ ወምትሩ ፡ እምእላንቱ ፡ አዕጹቀ ፡

የሆሣዕና፡ዕለት።

ከተማ ፡ የምስጋና ፡ ድምፅ ፡ አሰማች ፡ በውስጧ፡የሚኖሩትም፡ተንቀጠቀጡ።

፲፬፤ የአይሁድ፡መምህራንም፡የዚያችን፡ምስጋና፡ ድምፅ፡ይረዱ፡ዘንድ፡ወጡ፡የከበረ፡ታላቅ፡ ምሥጋናንም፡ሰሙ።

፲፭፤ ሕፃናቱንም፡(ክብር፡ይግባውና)፡የዮሴፍን፡ ልጅ፡የምታመሰግኑበትን፡ይህን፡ምስጋና፡ ማን፡አስተማራችሁ፡አሉዋቸው።

፲፮፤ ይህ፡ምሥጋና፡ከእግዚአብሔር፡ብቻ፡በቀር፡ ለሌላ፡አይገባምና፡የሚመጣ፡ንጉሥ፡የምትሉትስ፡ይህ፡ማን፡ነው?አሉዋቸው።

፲፯፤ ሕፃናትም ፡ የአይሁድን ፡ መምህራን ፡ ዓይና ችሁና፡ልባችሁ፡የታወረ፡ለድንግል፡ማርያም፡ ልጅ፡ሲሰግዱ፡እነዚህን፡መላእክት፡አታዩአቸ ውምን? ፀሐዩንስ ፡ ከእግሩ ፡ በታች ፡ እንደ ፡ ምድር፡ሁኖ፡አታዩትምን?አሏቸው።

፲፰፤ ከሕፃናት፡አንደበት፡ምሥጋናን፡አዘጋጀህ፡ የሚል፡የነቢዩ፡የዳዊትን፡ትንቢት፡አላነበባ ችሁምን?

መምህራኑም ፡ የወይራና ፡ የዘንባባ ፡ ቅርንጫፍ፡ ትይዙ ፡ ዘንድ ፡ ማን ፡ አስተማራችሁ፡አሉአቸው።

፲፱፤ ሕፃናትም፡ነቢይ፡ዳዊት፡ስለ፡እነዚህ፡ቅርንጫፎች፡አስተምሮናል፤ትንቢትም፡ተናግሮ ልናል፡ብለው፡መለሱ።

፳፤ እናንት ፡ ዕውሮች ፡ ሆይ ፡ ይህ ፡ በውርንጭላ ፡ ላይ፡ተቀምጦ፡የሚመጣው፡የእግዚአብሔር፡ መሲሕ ፡ ነውና ፡ ዕወቁ ፤ እርሱም ፡ ቅድመ ፡ ዓለም ፡ የነበረ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ፡እኛን፡ ለማዳን፡ዛሬ፡መጣ፡አሉዋቸው።

፳፩፤ እርሱም ፡ በሥጋ ፡ በሁለት ፡ ወገን ፡ ድንግል ፡ የሆነች፡የእመቤታችን ፡ የቅድስት ፡ ድንግል ፡ ማርያም፡ልጅ፡ነው።

፳፪፤ የጽዮን ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፡ ደስ ፡ ይበልሽ ፡ የኢየሩሳሌም ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፡ ፈጽሞ ፡ ደስ ፡ ይበልሽ፡ እነሆ ፡ የዋህና ፡ ትሑት ፡ የሆነ ፡ ንጉሥሽ ፡ በአህያ ፡ ውርንጭላ ፡ ላይ ፡ ተቀምጦ ፡ ይመጣል፡ ያለውን ፡ የዘካርያስን ፡ ትንቢት ፡ አላነበባችሁምን?አሉአቸው።ዘካ፡፱፡፱።

፳፫፤ ይኸን፡ቅናታችሁንና፡ቁጣችሁን፡ከእናንተ፡ አርቁ።

፳፬፤ ይኸም ፡ የዓለም ፡ ፈጣሪ ፡ እንደሆነ ፡ እወቁ፤ ከእነዚህም ፡ ከታላላቅ ፡ ዛፎች ፡ ዝንጣፊ ፡

Scanned by CamScanner

ዘዕለተ፡ሆሣዕና።	የሆሣዕና፡ዕለት።
ዕፀው ፡ ልዑላን ፡ ወሰብሕዎ ፡ ምስሌነ ፡ ወምስለ፡ መላእክት ፡ ወደምሩ ፡ ቃላቲከሙ ፡ በቃላቲነ።	ቆርጣችሁ ፡ ከእኛና ፡ ከመላእክት ፡ ጋር ፡ አመስግኑ ፤ ቃላችሁንም ፡ ከቃላችን ፡ ጋራ ፡ አንድ፡አድርጉ።
፷፭፤ ወሶበ ፡ አእመሩ ፡ ረበናተ ፡ አይሁድ ፡ ከመ ፡ ሕፃናት ፡ ኢይሰምዕዎሙ ፡ ወኢይፈርሁ ፡ ተግሣጾሙ ፡ ወኢያኅደግዎሙ ፡ ሰብሖቶ ፡ ለእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ወፈርሁ ፡ ዐቢየ ፡ ፍርሀተ።	፷፭፤ የአይሁድም ፡ መምህራን ፡ ሕፃናቱ ፡ እንዳልሰሙአቸው ፡ እና ፡ ተግሣጽአቸውንም ፡ እንዳልፈሩ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስንም ፡ ማመስገናቸውን ፡ እንዳላስተዉአቸው ፡ ባወቁ ፡ ጊዜ ፡ ታላቅ ፡ ፍርሀትም ፡ ፈሩ።
፷፮፤ ወይቤሉ ፡ በበይናቲሆሙ ፡ ንዑ ፡ ንሑር ፡ ኅበ ፡ ዝንቱ ፡ ብእሲ ፡ ወናጠይቆ ፡ ከመ ፡ ለዝንቱ ፡ ብእሲ ፡ ኢይደልዎ ፡ ስብሐት ፡ ዘእንበለ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ባሕቲቱ ፡ የአገዘሙ ፡ ለሕፃናት ፡ ያርምሙ።	፷፮፤ እርስ ፡ በርሳቸውም ፡ ምሥጋና ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ብቻ ፡ በቀር ፡ ለዚህ ፡ ሰው ፡ እንደማይገባው ፡ ሕፃናቱንም ፡ ዝም ፡ ይሉ ፡ ዘንድ ፡ እንዲአዝዛቸው ፡ እናስረዳው ፡ ዘንድ ፡ ወደዚህ ፡ ሰው ፡ ኑ ፡ እንሂድ ፡ ተባባሉ።
፷፯፤ ወይቤሎሙ ፡ እግዚእ ፡ ኢየሱስ ፡ ለእመ ፡ አርመሙ ፡ እሉ ፡ ሕፃናት ፡ ስብሐትየ ፡ አዘዝክዎሙ ፡ ለአዕባን ፡ ይሰብሕዎ ፡ ለወልደ ፡ ዕጓለ፡እመሕያው።	፷፯፤ ጌታ ፡ ኢየሱስም ፡ ምሥጋናዬን ፡ ሕፃናቱ ፡ ዝም ፡ ቢሉ ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ክርስቶስን ፡ ያመሰግኑት ፡ ዘንድ ፡ እነዚህን ፡ ደንጊያዎች ፡ አዝዛቸዋለሁ ፡ አላቸው።
፷፰፤ ኢያንበብክሙኑ ፡ ትንቢተ ፡ ዳዊት ፡ ነቢይ ፡ በእንተ ፡ ዛቲ ፡ ዕለት።	፷፰፤ ስለዚች ፡ ቀን ፡ ዳዊት ፡ የተናገረውን ፡ ትንቢት ፡ አላነበባችሁምን?
፷፱፤ ወሶበ ፡ ይቤ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ዘንተ ፡ ነገረ ፡ መጽኡ ፡ አዕባን ፡ እንዘ ፡ ይቀንጹ ፡ እምላዕለ ፡ ደብረ ፡ ዘይት።	፷፱፤ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስም ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ ሲናገር ፡ ከደብረ ፡ ዘይት ፡ ላይ ፡ ደንጊያዎች ፡ እየዘለሉ ፡ መጡ።
፸፤ ወበጽሑ ፡ ውስተ ፡ ቄላተ ፡ ዮሳፍጥ ፡ እንዘ ፡ ይጸርሑ ፡ በቃለ ፡ ሰብእ ፡ ወይብሉ ፡ ሆሣዕና ፡ በአርያም ፡ ለአምላክነ ፡ ሆሣዕና ፡ ቡሩክ ፡ ለመድኀኒትነ ፡ ዘይመጽእ ፡ በስመ ፡ እግዚአብሔር።	፸፤ በሰው ፡ አንደበትም ፡ እየጮኹ ፡ በአርያም ፡ መድኀኒት ፡ መባል ፡ ለፈጣሪያችን ፡ ይገባል ፡ በእግዚአብሔርነቱ ፡ ስም ፡ ለማዳን ፡ የሚመጣ ፡ መድኃኒት ፡ የተመሰገነ ፡ ነው ፡ እያሉ ፡ ከዮሳፍጥ ፡ ቄላ ፡ ደረሱ።
፸፩፤ ወተደመረ ፡ ቃለ ፡ አእባን ፡ በስብሐተ ፡ መላእክት ፡ ወበቃለ ፡ ሕፃናት።	፸፩፤ የደንጊያዎቹም ፡ የምሥጋና ፡ ቃል ፡ ከመላእክትና ፡ ከሕፃናት ፡ ምሥጋና ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ሆነ።
፸፪፤ ወአኀዘሙ ፡ ለአይሁድ ፡ ፍርሀት ፡ ወረዓድ ፡ ዐቢይ ፡ ወፈርሀዎሙ ፡ ለሕፃናት ፡ እልፍ ፡ ወሠለስቱ።	፸፪፤ አይሁድንም ፡ ታላቅ ፡ ፍርሃትና ፡ መንቀጥቀጥ ፡ ያዛቸው ፡ አሥር ፡ ሺ ፡ ሦስት ፡ የሚሆኑ ፡ ሕፃናትን ፡ ፈሩአቸው።
፸፫፤ ወሖረ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ወቦአ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ።	፸፫፤ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስም ፡ ሂዶ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ገባ።
፸፬፤ ሣህሉ ፡ ወምሕረቱ ፡ የሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን።	፸፬፤ ይቅርታውና ፡ ምሕረቱ ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ለዘላለሙ ፡ ይኑር ፡ አሜን።
አመ ፡ ትመጽእ ፡ በል ፤ ሃሌ ፡ ሉያ ፡ በብዝኀ ፡ ኀጉትከ ፡ አ.የሱስ ፡ በል። እምኵሉ ፡ ይሄይስ ፡ በል።	አመ ፡ ትመጽእ ፡ በል ፡ ሃሌ ፡ ሉያ ፡ በብዝኀ ፡ ኀጉትከ ፡ በል ። እምኵሉ ፡ ይኄይስ ፡ በል።
ስብሐት ፡ ለከ ፡ ኢየሱስ ፡ በል።	ኢየሱስ ፡ ሆይ ፡ ምሥጋና ፡ ይገባሃል።

Scanned by CamScanner

ዘዕለተ፡ሰሚዕና።

ክፍል፡፫።

(ይ፡ዲ)፡ተንሥኡ፡ለጸሎት።
(ይ፡ሕ)፡እግዚኦ፡ተሣሃለነ፡(ይ፡ካ)፡ሰላም፡ለኵልክሙ።
(ይ፡ሕ)፡ምስለ፡መንፈስከ።

፩፤ (ይ፡ካ)፡እግዚአብሔር፡እግዚኦ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡አምላክነ፡ዘትቤሎሙ፡ለአርዳኢከ፡ቅዱሳን፡ወለሐዋርያቲከ፡ንጹሐን።

፪፤ እስመ፡ብዙኃን፡ነቢያት፡ወጻድቃን፡ፈተዉ፡ይርአዩ፡አንትሙ፡ዘትሬእዩ፡ወኢርእዩ።

፫፤ ወፈተዉ፡ይስምዑ፡አንትሙ፡ዘትሰምዑ፡ወኢሰምዑ።

፬፤ ወለክሙሰ፡ብፁዓት፡አዕይንቲክሙ፡እለ፡ርእያ፡ወአዕዛኒክሙ፡እለ፡ሰምዓ።

፭፤ ወከማሆሙ፡ለነኒ፡ረስየነ፡ድልዋነ፡ንስማዕ፡ወንግበር፡ቃለ፡ወንጌልከ፡ቅዱስ፡በጸሎቶሙ፡ለቅዱሳን።

(ይ፡ዲ)፡ጸልዩ፡በእንተ፡ወንጌል፡ቅዱስ፤

(ይ፡ሕ)፡አለብወነ፡ንስማዕ፡ወንግበር፡ቃለ፡ወንጌልከ፡ቅዱስ።

፮፤ (ይ፡ካ)፡ተዘከር፡ካዕበ፡እግዚኦ፡እለ፡አውሥኡነ፡ከመ፡ንዘክሮሙ፡ጊዜ፡ጸሎትነ፡ወአስተብቍዖትነ፡እንተ፡ነኀሥሥ፡እምኀቤከ።

፯፤ አ፡እግዚአብሔር፡አምላክነ፡ለእለ፡ቀደሙነ፡ነዊመ፡አእርፎሙ፡ወለዱያንሂ፡ፍጡነ፡ፈውሶሙ።

፰፤ እስመ፡አንተ፡ውእቱ፡ሕይወተ፡ኵልነ፡ወተስፋ፡ኵልነ፡ወባላሔ፡ኵልነ፡ወመንሥኤ፡ኵልነ።

፱፤ ወለከ፡ንፌኑ፡አኰቴተ፡እስከ፡አርያም፡ለዓለመ፡ዓለም፡(ይ፡ዲ)፡መዝ፤ ፻፲፯፤ ፭፮፤ ቡሩክ፡ዘይመጽእ፡በስመ፡እግዚአብሔር፡ባረክናክሙ፡እምቤተ፡እግዚአብሔር።እግዚአብሔር፡እግዚኦ፡አስተርአየ፡ለነ።ሕዝብኒ፡ይሰጠዉ፡ዘንተ።(ይ፡ዲ)፡ቁሙ፡ወአጽምዑ፡ከመ፡ንኩን፡ድልዋነ፡ለመንግሥተ፡ሰማያት።

(ይ፡ካ)፡ወንጌል፡ቅዱስ፡ዘዜነወ፡ሉቃስ፡ቃለ፡ወልደ፡እግዚአብሔር።

(ይ፡ሕ)፡ስብሐት፡ለከ፡ክርስቶስ፡እግዚእየ፡ወአምላኪየ፡ኵሎ፡ጊዜ።

(ይ፡ካ)፡ባርክ፡እግዚኦ፡ነገረ፡ዘእምወንጌለ፡ሉቃስ፡ረድኡ፡ወሐዋርያሁ፡ለእግዚእነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ወልደ፡እግዚአብሔር።ሕያው፡ዘለዓለ፡ንፌኑ፡ስብሐተ፡ወአኰቴተ፡

የሠላዕና፡ዕለት።

ክፍል፡፫።

ዲ፡ለጸሎት፡ተነሡ፡ይበል።
ሕዝቡ፡አቤቱ፡ይቅር፡በለን፡ይበል።ካህኑ፡ሰላም፡ለሁላችሁ፡ይሁን፡ይበል።
ሕዝብ፡እንደቃልህ፡ይሁንልን፡ይበሉ።

፩፤ ካህኑ፡አቤቱ፡አምላካችን፡እግዚአብሔር፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ሆይ፡ቅዱሳን፡የሚሆኑ፡ደቀ፡መዛሙርትህንና፡ንጹሓን፡ሐዋርያትን፡እንዲህ፡ያልሃቸው።

፪፤ እናንተ፡የምታዩትን፡ያዩ፡ዘንድ፡ብዙ፡ነቢያትና፡ጻድቃን፡ወደዱ፡አላዩም።

፫፤ እናንተ፡የምትሰሙትን፡ይሰሙ፡ዘንድ፡ወደዱ፡አልሰሙም።

፬፤ ያዩ፡ዓይኖቻችሁና፡የሰሙ፡ጆሮቻችሁ፡ግን፡የተመሰገኑ፡ናቸው።

፭፤ እኛንም፡እንደነሱ፡የበቃን፡አድርገን፡በቅዱሳን፡ጸሎት፡የከበረ፡የወንጌልን፡ቃል፡ሰምተን፡እንሠራ፡ዘንድ።

ዲያቆኑ፡የከበረ፡የወንጌልን፡ቃል፡ለመስማት፡ያበቃን፡ዘንድ፡ጸልዩ፡ይበል።
ሕዝቡ፡የከበረ፡የወንጌልህን፡ቃል፡ሰምተን፡እነድንሠራው፡አድርገን።

፮፤ ይ፡ካ፡ዳግመኛም፡አቤቱ፡ካንተ፡ዘንድ፡የምሻውን፡በምንለምንበትና፡በምንጸልይበት፡ጊዜ፡እናስባቸው፡ዘንድ፡አስቡን፡ያሉንን፡አስብ።

፯፤ አቤቱ፡አምላካችን፡እግዚአብሔር፡ሆይ፡ከእኛ፡አስቀድመው፡የሞቱትን፡አሳርፋቸው፡የታመሙትን፡ፈዋህ፡አድናቸው።

፰፤ የሁላችን፡ሕይወት፡የሁላችን፡ተስፋ፡የሁላችንም፡አዳኝ፡የሁላችንም፡አሥነሽ፡አንተ፡ነህና።

፱፤ ለአንተም፡ምሥጋናን፡እስከ፡አርያም፡ድረስ፡ለዘላለሙ፡እናቀርባለን።ዲያቆኑ፡መዝ፤ ፻፲፯፤ ፭፮፤ በእግዚአብሔር፡ስም፡የሚመጣ፡ቡሩክ፡ነው።ከእግዚአብሔር፡ቤት፡አከበርናችሁ።ጌታ፡እግዚአብሔር፡ተገለጠልን፤ ሕዝቡም፡ይሆን፡ይቀበሉ።ዲያቆኑ፡ቁማችሁ፡አድምጡ፡ለመንግሥተ፡ሰማያት፡የበቃን፡የተዘጋጀን፡እንሆን፡ዘንድ፡ይበል።

ካህኑ፡ሉቃስ፡የጻፈው፡የከበረ፡የእግዚአብሔር፡ልጅ፡ቃል፡ወንጌል፡ይበል።

ሕዝቡ፡ጌታዬና፡ፈጣሪዬ፡ክርስቶስ፡ሆይ፡ሁልጊዜ፡ለአንተ፡ምሥጋና፡ይገባል፡ይበሉ።

ካህን፡አቤቱ፡የሕያው፡እግዚአብሔር፡ልጅ፡የጌታችን፡የኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ሐዋርያውና፡ደቀ፡መዝሙሩ፡ከሚሆን፡ከሉቃስ፡ወንጌል፡የተገኘውን፡ቃል፡ባርክ፡ምሥጋናን፡

Scanned by CamScanner

ዘዕለተ፡ሰሣዕና።	የሰሣዕና፡ዕለት።
ክብረ፡ወስግደተ፡እምድር፡እስከ፡አርያም፡ለዓለመ፡ዓለም።	ክብርን፡ስግደትን፡ከምድር፡እስከ፡አርያም፡ለእርሱ፡እናቀርባለን፡ለዘላለሙ።
ወንጌል፡ዘሉቃስ።	የሉቃስ፡ወንጌል።
ምዕ፲፱፡፵፩-፵፱።	ምዕ፲፱፡፵፩-፵፱።
፵፩ወእምዝ ፡ አልጺቆሙ ፡ ኢያሪሐ ፡ ሀሎ ፡ አሐዱ ፡ ዕውር ፡ ይነብር ፡ ውስተ ፡ ፍኖት ፡ ወይስእል።	፵፩ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ኢያሪሆ ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፡ አንድ፡ ዕውር ፡ በጎዳና ፡ ተቀምጦ ፡ ይለምን ፡ ነበር።
፵፪ወሰሚዖ ፡ ድምፀ ፡ ሰብእ ፡ ዘየኀልፍ ፡ ይቤ ፡ ምንትኑ ፡ ዝ ፡ ዘእሰምዕ።	፵፪የሚተላለፈውን ፡ የሰው ፡ ድምጽ ፡ ሰምቶ ፡ ይህ ፡ የምሰማው ፡ ምንድን ፡ ነው ፡ አለ።
፵፫ወይቤልዎ ፡ ኢየሱስ ፡ ናዝራዊ ፡ የኀልፍ።	፵፫የናዝሬቱ ፡ ኢየሱስ ፡ ያልፋል ፡ አሉት።
፵፬ወዐውየወ ፡ ወይቤ ፡ ኢየሱስ ፡ ወልደ ፡ ዳዊት ፡ ተሣሃለኒ።	፵፬ድምፁን ፡ ከፍ ፡ አድርጎ ፡ የዳዊት ፡ ልጅ ፡ ኢየሱስ ፡ ሆይ ፡ እዘንልኝ ፡ አለ።
፵፭ወገሠጽዎ ፡ እለ ፡ ይመርሕዎ ፡ ከመ ፡ ያርምም ፡ ወዐውየወ ፡ ፈድፋደ ፡ ወይቤ ፡ ወልደ ፡ ዳዊት ፡ ተሣሃለኒ።	፵፭የሚመሩትም ፡ ዝም ፡ ይል ፡ ዘንድ ፡ ገሠጹት ፤ እሱ ፡ ግን ፡ በጣም ፡ ጮኸ ፡ ብሎ ፡ የዳዊት ፡ ልጅ ፡ ማረኝ ፡ አለ።
፵፮ወቆመ ፡ እግዚእ ፡ ኢየሱስ ፡ ወአዘዘ ፡ ያምጽእዎ ፡ ኀቤሁ።	፵፮ጌታችን ፡ ኢየሱስም ፡ ቁሞ ፡ ወደሱ ፡ ያመጡት ፡ ዘንድ ፡ አዘዘ።
፵፯ወበጺሖ ፡ ኀቤሁ ፡ ይቤሎ ፡ ምንተ ፡ ትፈቅድ ፡ እግበር ፡ ለከ ። ወይቤሎ ፡ እግዚኦ ፡ ከመ ፡ ይርአያ ፡ አዕይንትየ።	፵፯ወደርሱም ፡ በቀረበ ፡ ጊዜ ፡ ምን ፡ ላደርግልህ ፡ ትወዳለህ ፡ አለው ፤ አቤቱ ፡ ዓይኖቼ ፡ እንዲያዩ ፡ ነው ፡ አለው።
፵፰ወይቤሎ ፡ እግዚእ ፡ ኢየሱስ ፡ ርኢ ፡ ሃይማኖትከ ፡ አሕየወተከ።	፵፰ጌታችን ፡ ኢየሱስም ፡ እይ ፤ ሃይማኖትህ ፡ አዳነችህ ፡ አለው።
፵፱ወርእየ ፡ ሶቤሃ ፡ ወተለዎ ፡ ወአእኰቶ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወርእዮሙ ፡ ኵሉ ፡ ሕዝብ ፡ ሰብሕዎ ፡ ለእግዚአብሔር።	፵፱ወዲያውም ፡ አየና ፡ ተከተለው ፤ እግዚአብሔርን ፡ አመሰገነው ፤ ሕዝቡም ፡ ሁሉ ፡ አይተው ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመሰገኑት።
ምዕ፲፱፡፩-፲።	ምዕ፲፱፡፩-፲።
፩ወቦአ ፡ ኢያሪሆ ፡ እግዚእ ፡ ኢየሱስ ፡ ወአንሶሰወ።	፩ጌታችን ፡ ኢየሱስም ፡ ወደ ፡ ኢያሪሆ ፡ ገብቶ ፡ ተመላለሰ።
፪ወናሁ ፡ ረከበ ፡ ብእሴ ፡ ዘስሙ ፡ ዘኬዎስ ፡ መልአከሙ ፡ ለመጸብሓን ፡ ወባዕል ፡ ውእቱ።	፪እነሆም ፡ የቀራጮች ፡ አለቃ ፡ ስሙ ፡ ዘኬዎስ ፡ የተባለውን ፡ ሰው ፡ አገኘ ፤ እሱም ፡ ባለጸጋ ፡ ነበር።
፫ወየኀሥሥ ፡ ይርአዮ ፡ ለእግዚእ ፡ ኢየሱስ ፡ መኑ ፡ ውእቱ ። ወኢያበውሖ ፡ ሰብእ ፡ እስመ ፡ ኀጺር ፡ ውእቱ ፡ በቆሙ።	፫ጌታ ፡ ኢየሱስንም ፡ ያየው ፡ ዘንድና ፡ ማን ፡ እንደሆነ ፡ ያውቅ ፡ ዘንድ ፡ ይሻ ፡ ነበር ። የሰው ፡ ብዛትም ፡ ይከለክለው ፡ ነበር ፤ ቁመቱ ፡ አጭር ፡ ነበረና።
፬ወሮጸ ፡ ቅድሜሁ ፡ ወዐርገ ፡ ዲበ ፡ ሰግላ ፡ ከመ ፡ ይርአዮ ፡ እስመ ፡ እንተ ፡ ይእቲ ፡ ፍኖት ፡ ሀለዎ ፡ ይኅልፍ።	፬ወደፊትም ፡ ሩጦ ፡ ያየው ፡ ዘንድ ፡ ከሾላ ፡ ዛፍ ፡ ላይ ፡ ወጣ ፤ በዚያች ፡ መንገድ ፡ ያልፍ ፡ ዘንድ ፡ አለውና።
፭ወበጺሖ ፡ ህየ ፡ ነጸሮ ፡ እግዚእ ፡ ኢየሱስ ፡ ወይቤሎ ፡ ዘኬዎስ ፡ አፍጥን ፡ ረድ ፡ እስመ ፡ ዮም ፡ ሀለወኒ ፡ አዐል ፡ ቤተከ።	፭ጌታችን ፡ ኢየሱስም ፡ ከዚያ ፡ እንደ ፡ ደረሰ ፡ አየውና ፡ ዘኬዎስ ፡ ፈጥነህ ፡ ውረድ ፤ ዛሬ ፡ ከቤትህ ፡ እውል ፡ ዘንድ ፡ አለኝና ፡ አለው።

Scanned by CamScanner

ዘዕለተ፡ሆሣዕና።	የሆሣዕና፡ዕለት።
፮፤ ወአፍጠነ ፡ ወሪደ ፡ ወአግሐሥ ፡ ጎበ ፡ ቤቱ ፡ እንዘ፡ይትፌሣሕ።	፮፤ ፈጥኖም ፡ ወረደና ፡ ደስ ፡ እያለው ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ይዞት ፡ ገባ።
፯፤ ወርእዮ፡ሙሉሙ፡አንጐርጕሩ፡ወይቤሉ፡ ጎበ፡ብእሲ፡ኀጥእ፡በዐ፡የዐል።	፯፤ ሁሉም ፡ አይተው ፡ ከኃጢአተኛ ፡ ሰው ፡ ቤት ፡ ሊውል ፡ ገባ ፡ ብለው ፡ አንጐራጐሩ።
፰፤ ወቆመ፡ዘኬዎስ፡ወይቤሎ፡ለእግዚእነ፡ናሁ፡ መንፈቀ፡ንዋይየ፡እሁብ፡ለነዳያን፡ወእመሂ፡ በ ፡ ዘገፋዕክዎ ፡ እፈድዮ ፡ ህየንተ ፡ አሐዱ ፡ ትርብዕተ።	፰፤ ዘኬዎስም ፡ ቆመና ፡ ጌታችንን ፡ እንዲህ ፡ አለው፤ ጌታዬ ፡ አሁን ፡ የገንዘቤን ፡ እኩሌታ ፡ ለነዳያን ፡ እሰጣለሁ ፤ የበደልኩትም ፡ ቢኖር ፡ በአንድ ፡ አራት ፡ ዕጥፍ ፡ እከፍላለሁ።
፱፤ ወይቤሎ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡ዮምሰ፡ሕይወት፡ ኮነ ፡ ለዝንቱ ፡ ቤት ፡ እስመ ፡ አንተሂ ፡ ወልደ ፡ አብርሃም፡አንተ።	፱፤ ጌታችን ፡ ኢየሱስም ፡ ዛሬስ ፡ ለዚህ ፡ ቤት ፡ ሕይወት ፡ ሆነ ፤ አንተም ፡ የአብርሃም ፡ ልጅ ፡ ነህና ፡ አለው።
፲፤ እስመ ፡ መጽአ ፡ ወልደ ፡ ዕጓለ ፡ እመሕያው ፡ ይኅሥሥ፡ወያድኅን፡ዘተኀጕለ።	፲፤ የሰው ፡ ልጅ ፡ የጠፋውን ፡ ሊፈልግና ፡ ሊያድን ፡ መጥቷልና።
ይቀልል ፡ ኀልፈተ ፡ ሰማይ ፡ ወምድር ፡ እምትደቅ ፡ አሐቲ ፡ ቃል ፡ እምኦሪት ፡ ወእምነ ቢያት ፡ ይቤ ፡ እግዚእ ፡ ለአርዳኢሁ ፡ ።	ከአሪት ፡ ከነቢያት ፡ አንዲቱ ፡ ቃል ፡ ከምሳ ፡ ወድቅ ፡ ይልቅ ፡ የሰማይና ፡ የምድር ፡ ማለፍ ፡ ይቀላል ፡ አለ ጌታ ፡ ለደቀ ፡ መዛሙርቱ።
(ይሕ) ፡ ነአምን ፡ በቃለ ፡ ወንጌልከ ፡ ቅዱስ።	ሕዝቡ ፡ በከበረ ፡ በወንጌልህ ፡ ቃል ፡ እናምናለን ፡ ይበሉ።

(፫)፡ይገንዩ።

ስምዓኒ፡እግዚኦ፡ጸሎትየ፡ሃሌ፡ሉያ፡ወይብጻሕ፡ቅድሜከ፡ገዐርየ፡ሃሌ፡ሉያ፡ሃሌ፡ሃሌ፡ሉያ፡ወኢትሚጥ፡ገጸከ፡ እምኔየ፡በዕለተ፡ምንዳቤየ፡አጽምዕ፡ዕዝነከ፡ኀቤየ፡ሃሌ፡ሉያ፡አመ፡ዕለተ፡ዕጼውዓከ፡ፍጡነ፡ስምዐኒ፡ሃ፡ሃ፡ ለዓለም፡ወለዓለመ፡ዓለም። ቡሩክ፡ዘይመጽእ፡በስመ፡እግዚአብሔር፡ወቡሩክ፡ንጉሥ፡እስራኤል፡ንፍኁ፡ቀርነ፡ በጽዮን፡ወስብኩ፡በደብረ፡መቅደስየ።

ዕዝል፡(ሰላም)።

ተበሃሉ፡ሕዝብ፡በበይናቲሆሙ፡እንዘ፡ይብሉ፡ዓይ፡ውእቱ፡ዝንቱ፡ንጉሥ፡ስብሐት፡እስመ፡ውእቱ፡እግዚእ፡ ለሰንበት፡ቦአ፡ሀገረ፡ኢየሩሳሌም፡በፍሥሐ፡ወበሰላም።

(ምል)በፍሥሐ፡ወበሰላም፡ቦአ፡ሀገረ፡ኢየሩሳሌም።

(ይካ)፡ሰላመ፡አብ፡ወወልድ፡ወመንፈስ፡ቅዱስ። ወእምዝ፡ይበል፡በዐቢይ፡ዜማ፡ዕዝል፡ዘውእቱ፡ማሕዘኒ፡ እግዚኦ፡መሐረነ፡ክርስቶስ፡ሠለስተ፡ጊዜ፡ወይበሉ፡ክርስቶስ፡ጋዳ። ቅዱስ። እስከ፡ተፍጻሜቱ። ወእምዝ፡ይበል፡ በንዑስ፡ዜማ፡ዕዝል፡እግዚኦ፡መሐረነ፡ክርስቶስ፡ሠለስተ፡ጊዜ። ስብሐት፡ለእግዚአብሔር፡ኪያነ፡ዘፈጠረ፡ከመ፡ ናምልኮ። ስብሐት፡ለማርያም፡እመ፡አምላክ፡እግዝእትነ፡ወመድኀኒትነ።

ስብሐት፡ለመስቀለ፡ክርስቶስ፡ዕፀ፡መድኀኒት፡ኃይልነ፡ወፀወንነ። ወይበሉ፡ጸሎተ፡ሃይማኖት፡ነአምን፡በአሐዱ፡ አምላክ፡እስከ፡ተፍጻሜቱ፡ወዓዲ፡አቡነ፡ዘበሰማያት።

ወበዝየ ፡ ያንብቡ ፡ ምዕዳን ፡ በዕለተ ፡ ሆሣዕና ፡ በሰንበት፡ዘነግሀ።	እሑድ ፡ በነግህ ፡ በሆሣዕና ፡ ቀን ፡ ምክሩን፡ በዚህ፡ያንብቡ።
ምዕራፍ፡፫።	ምዕራፍ፡፫።
ክፍል፡፭።	ክፍል፡፭።
ኦሪት፡ዘልደት።	ኦሪት፡ዘፍጥረት።
ም፤፵፱፤፭።	ም፤፵፱፤፭።
፭፤ ወሶበ ፡ ቀርበ ፡ መዋዕሊሁ ፡ ለያዕቆብ ፡ ከመ ፡ ይፍልስ፡ጸውዖሙ፡ለኩሎሙ፡ደቂቁ።	፭፤ ያዕቆብም ፡ የሚሞትበት ፡ ቀን ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ ልጆቹን ፡ ጠርቶ ፡ በኋላ ፡ ዘመን ፡ የሚሆነውን ፡

Scanned by CamScanner

ዘዕለተ፡ሰሚዕና።

ወይቤሎሙ፡ተጋብኡ፡ደቂቅየ፡ዐውድየ፡ከመ፡እንግርክሙ፡ዘይከውን፡በደኀሪ፡መዋዕል።

፪፡ ወተጋብኡ፡ደቂቁ፡ወይቤሎሙ፡ያዕቆብ፡ስምዐ፡እምእስራኤል፡አቡክሙ።

፫–፰፡ ይሁዳ፡ይሴብሑክ፡አኀዊክ፡እደ፝ክ፡ዲበ፡ላዕለ፡ዘባኖሙ፡ለጸላዕትክ፡ይሰግዱ፡ለክ፡ደቂቀ፡አቡክ።

፱–፲፪፡ ይሁዳ ፡ዕንለ ፡ አንበሳ ፡ ዕርግ ፡ እም ሕዝአትክ ፡ ወልድየ ፡ ሰክብክ ፡ ወኖ ምክ ፡ ከመ ፡ ዕንለ ፡ አንበሳ ፡ አልቦ ፡ ዘያነ ቅሀክ።

፲፫–፲፯፡ ኢይጠፍእ ፡ ምልክና ፡ እምይሁዳ ፡ ወምስፍና፡ እምአባሉ ፡ እስክ ፡ አመ ፡ ይረክብ፡ዘጽኑሕ፡ሎቱ።

፲፰–፲፱፡ ወውእቱ፡ተስፋሆሙ፡ለአሕዛብ።

፳–፳፩፡ የአሥር፡በዐጸደ፡ወይን፡ዕዋሎ፡ወበዕፀ፡ዘይት፡አድጎ።

፳፪–፳፱፡ ወየሐዕብ ፡ በወይን ፡ ልብሶ ፡ አልባሲሁ ፡ ወበደመ፡አስካል፡ሰንዱኖ።

፴–፴፫፡ ፍሡሓት ፡ አዕይንቲሁ ፡ እምወይን ፡ ወጸዓዳ፡አስናኒሁ፡ከመ፡ሐሊብ።

፴፬–፴፱፡ ወባረከክ ፡ በበረከተ ፡ ሰማይ ፡ እም ላዕሉ ፡ ወበረከተ ፡ ምድር ፡ እንተ ፡ ባቲ ፡ ኵሉ።

ዘዘካርያስ ፡ ነቢይ ፡ በረከቱ ፡ ትኩን ፡ ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ምዕ፡፳፡፪–፳፡

፪፡ ከመዝ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘኵሎ ፡ ይመልክ ፡ ቀናዕኩ ፡ ላዕለ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ወላዕለ ፡ ወለተ ፡ ጽዮን ፡ ዐቢየ ፡ ቅንአተ ፡ ወተማዕኩ፡መዐተ፡ዐቢየ።

፫፡ ከመዝ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘኵሎ ፡ ይመልክ፡እትመየጣ፡ለጽዮን፡ወአኃድር፡ማዕከለ፡ኢየሩሳሌም።

ወትሰመይ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ሀገረ ፡ ጽድቅ ፡ ወደብረ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘኵሎ ፡ ይመልክ፡ወደብረ፡መቅደስ።

፬፡ ከመዝ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘኵሎ ፡ ይመልክ ፡ ዓዲ ፡ ይነብሩ ፡ አእሩግ ፡ ወሊቃ ውንት ፡ ውስተ ፡ መርኀባ ፡ ለኢየሩሳሌም ፡ ወለኵሎሙ ፡ ምርጉዛሙ ፡ ውስተ ፡ እደዊሆሙ።

የሰሚዕና፡ዕለት።

እነግራችሁ ፡ ዘንድ ፡ ልጆቼ ፡ በዙሪያዬ ፡ ወደ፡እኔ፡ተሰብሰቡ፡አላቸው።

፪፡ ልጆቹም ፡ ተሰበሰቡ ፡ ያዕቆብም ፡ እኔን ፡ አባ ታችሁን ፡ ስሙኝ ፡ አላቸው።

፫–፰፡ ይሁዳ ፡ ወንድሞችህ ፡ ያመሰግኑሃል ፡ እጅህ፡ በጠላቶችህ ፡ ጀርባ ፡ ላይ ፡ ነው ፡ የአባትህ፡ልጆችም፡ይሰግዱልሃል።

፱–፲፪፡ የአንበሳ ፡ ግልገል ፡ ይሁዳ ፡ ከመደብህ ፡ ውጣ፡ልጄ ፡ እንደ ፡ አንበሳ ፡ ተኛህ ። አንቀላፋህም ። እንደ አንበሳ ፡ ደቦልም ፡ የሚቀሰቅስህ፡የለም፡አለው።

፲፫–፲፯፡ መንግሥት ፡ ከይሁዳ ፡ አይጠፋም ፡ ምስፍናም ፡ ከወገኑ ፡ ለእርሱ ፡ የተጠበቀለት፡እስከሚገኝ፡ድረስ።

፲፰–፲፱፡ እርሱም፡የአሕዛብ፡አለኝታቸው፡ነው።

፳–፳፩፡ በወይን ፡ ሐረግ ፡ ውርንጫውን ፡ በወይራ ፡ እንጨትም፡አህያውን ፡ያስራል።

፳፪–፳፱፡ ልብሶቹን ፡ በወይን ፡ ያጥባል ፡ ድርብ ፡ በፍታውንም፡በወይኑ፡ዘለላ፡ደም።

፴–፴፫፡ ከወይን ፡ ይልቅ ፡ ዐይኖቹ ፡ ደስ ፡ ያሰኛሉ ፡ ጥርሶቹም፡እንደ፡ወተት፡ነጭ፡ናቸው።

፴፬–፴፱፡ ከላይ ፡ በሚገኝ ፡ በሰማይ ፡ በረከት ፡ አከበረህ፡ ሁሉ ፡ ከእርስዋ ፡ በሚገኝ ፡ በምድር፡በረከት፡ባረከህ።

ነቢዩ ፡ ዘካርያስ፡ የተናገረው ፡ ትንቢት ፡ ይህ፡ነው፡በረከቱ፡ከእኛ ፡ጋራ ፡ለዘላለሙ፡ትኑር፡አሜን።

ምዕ፡፳፡፪–፳፡

፪፡ ሁሉን ፡ የሚገዛ ፡ እግዚአብሔር ፡እንዲህ ፡ በኢየሩሳሌምና ፡ በጽዮን ፡ ልጅ ፡ ላይ ፡ ታላቅ፡ቅንአትን፡ቀናሁ፤ታላቅ፡ቁጣንም፡ተቈጣሁ።

፫፡ ሁሉን ፡ የሚገዛ ፡ እግዚአብሔር ፡እንዲህ ፡ አለ፤ ለጽዮን ፡ እመለስላታለሁ ፤ በኢየሩሳሌምም ፡ መካከል ፡ አድራለሁ ፤ ኢየሩሳሌም፡የእውነት፡አገር፡ተባላ፡ትጠራለች፡ ሁሉን ፡ የሚገዛ ፡ የእግዚአብሔር ፡መዲና ፡ የምሥጋናውም፡መቅደስ፡ትባላለች።

፬፡ ሁሉን ፡ የሚገዛ ፡ እግዚአብሔር ፡ እን ዲህ ፡ አለ ፤ ዳግመኛ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ አደባባይ ፡ ሊታውን፡ና፡ሽማግሎቹ ፡ይኖሩባታል ፤ የሁሉም ፡ ምርኩዛቸው ፡ በእጃቸው፡ነው።

Scanned by CamScanner

ዘዕለተ፡ሆሣዕና።	የሆሣዕና፡ዕለት።
፩፤ ይመልእ ፡ መርጎበ ፡ ሀገር ፡ ደቀ ፡ ወአዋ ልደ ፡ ዘይትዋነዩ ፡ ውስተ ፡ መርጎባ ፡ ለኢየሩ ሳሌም።	፩፤ የአገሩም ፡ አደባባይ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ አደባባይ፡ የሚጫወቱ ፡ ሴቶች ፡ ልጆችንና፡ ወንዶች፡ልጆችን፡ይመላል።
፪፤ ከመዝ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘኵሎ ፡ ይመልክ፡ለእመ፡ተስእኖሙ፡ለሕዝብየ፡እለ፡ ተርፉ፡ዝ፡ኵሉ፡በቅድሜሆሙ፡በቅድሜየኒ፡ ይሰአነኒኑ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘኵሎ ፡ ይመልክ።	፪፤ ሁሉን ፡ የሚገዛ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ፡ አለ ፤ ከሞት ፡ ለቀሩ ፡ ለወገኖቼ ፡ ይኸ ፡ ሁሉ ፡ በፊታቸው ፡ ቢሳናቸው ፡ ሁሉን፡ የሚገዛ ፡ እግዚአብሔር ፡ በኔ ፡ ዘንድ ፡ ይሳነ ኛልን?አለ።
፫፤ ከመዝ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘኵሎ ፡ ይመልክ፡ናሁ ፡ አነ ፡ አድኅኖሙ ፡ ለሕዝብየ ፡ እምብሔረ፡ጽባሕ፡ወእምብሔረ፡ዐረብ።	፫፤ ሁሉን፡የሚገዛ፡እግዚአብሔር፡እንዲህ፡አለ፡ ወገኖቼን ፡ ከምሥራቅ ፡ አገርና ፡ ከምዕራብ፡ አገር፡እነሆ፡አድናቸዋለሁ።
፬፤ ወእወስዶሙ ፡ ወአኅድሮሙ ፡ ማዕከለ ፡ ኢየሩ ሳሌም ፡ ወበህየ ፡ ይከውኑኒ ፡ ሕዝብየ ፡ ወአነሂ ፡ እከውኖሙ ፡ አምላኮሙ ፡ በጽድቅ ፡ ወበርትዕ።	፬፤ ወስጇም ፡ በኢየሩሳሌም ፡ መካከል ፡ አኖራቸ ዋለሁ ፤ በዚያም ፡ ቦታ ፡ ወገኖቼ ፡ ይሆናሉ፡ እኔም ፡ በሚገባና ፡ በእውነት ፡ ፈጣሪያቸው፡ እሆናለሁ።
ዘዘካርያስ ፡ ነቢይ ፡ በረከቱ ፡ ትኩን ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን።	ነቢዩ ፡ ዘካርያስ ፡ የተናገረው ፡ ትንቢት ፡ ይህ፡ ነው። በረከቱ ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ ለዘላለሙ ፡ ትኑር፡ አሜን።
ምዕ፱፡ቍ–፲፭።	ምዕ፱፡ቍ–፲፭።
፭፤ ወአነሥእ ፡ ቤትየ ፡ ወአቀውም ፡ ከመ ፡ ኢትሑሩ ፡ ወኢትግብኡ ፡ ውስተ ፡ አሕዛብ ፡ ወኢየኀልፍ ፡ እንከ ፡ ቀስት ፡ ላዕሌክሙ ፡ ዘያደ ነግፀክሙ ፡ እስመ ፡ ይእዜ ፡ ርኢኩ ፡ በአዕይ ንትየ።	፭፤ ወደ ፡ አሕዛብ ፡ አገር ፡ ተመልሳችሁ ፡ እንዳትሄዱ ፡ ቤቴን ፡ አነሣዋለሁ ፤ አጸና ዋለሁም ፤ዛሬ፡በዐይኖቼ፡ጠብቂያችኋለሁና፡ የሚያስደነግጣችሁ፡ጦር፡ጠላት፡በእናንተ፡ አያልፍም።
፮፤ ተፈሥሒ፡ፈድፋደ፡ወለተ፡ጽዮን፡ወስብኪ፡ ወለተ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ናሁ ፡ ይመጽእ ፡ ንጉሥኪ፡ ጻድቅ ፡ ወመድኀን ፡ ወየዋህ ፡ ውእቱ፡ወይዜማን፡ዲበ፡አድግ፡ወዲበ፡ዕዋለ፡ አድግ።	፮፤ የጽዮን ፡ ልጅ ፡ እጅግ ፡ ደስ ፡ ይበልሽ ፤ የኢየሩ ሳሌም ፡ ልጅ ፡ እልል ፡ በይ ፤ እውነተኛና፡ አዳኝ፡ ትሑትም ፡ ሆኖ ፡ ንጉሥሽ ፡ እነሆ፡ ይመጣል ፤ በውርንጫይቱና፡ በአህያይቱ፡ ላይ፡ተቀምጦ፡ይመጣል።
፯፤ ወያጠፍእ ፡ ሠረገላ ፡ እምኤፍሬም ፡ ወአ ፍራሰ ፡ እምኢየሩሳሌም ፡ ወየኃልቅ ፡ እንከ ፡ ቅስት ፡ ወቀትል ፡ ወይከውን ፡ እንከ ፡ ብዙኀ ፡ ሰላም ፡ በመዋዕሊሁ ፡ እምአሕዛብ፡ወሥልጣኑ፡እምባሕር፡እስከ፡ ባሕር ፡ ወእምአፍላግ ፡ እስከ፡ አጽናፈ ፡ ምድር።	፯፤ ከኤፍሬም ፡ ሠረገላን ፡ ከኢየሩሳሌምም ፡ ፈረሶችን፡ያጠፋል፤ሰልፍና፡ጸብ፡ከርከርም፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ይጠፋል ፤ ከአሕዛብ ፡ የተነሣ ፡ በዘመኑ ፡ ብዙ ፡ ሰላም ፡ ይሆናል ፡ ሥልጣኑም ፡ ከባሕር ፡ እስከ ፡ ባሕር ፡ ከፈሳሹም፡ እስከ ፡ ምድር ፡ ዳርቻ ፡ ድረስ ፡ ይሆናል፤
፲፩፤ ወእንተ ፡ በደመ ፡ ሥርዐት ፡ ፈነውኩ ፡ ሙቁሐነኪ፡እምአዘቅት፡ዘአልቦ፡ማይ።	፲፩፤ ሥርዓት፡ባለው፡ደም፡የታሰሩ፡እስረኞችሽን፡ ውኃ፡ከሌለበት፡ጕድጓድ፡አሰናበትኋቸው።
፲፪፤ ወይነብሩ ፡ ውስተ ፡ አጽዋን ፡ ሙቁሓን ፡ ተዓይን፡ ወሀየንተ ፡ አሐቲ ፡ ዕለት ፡ ካዕበተ ፡ እፈድየከ።	፲፪፤ የታሰሩትም ፡ ሰዎች ፡ በአምባው ፡ ይኖራሉ፡ ስለ፡ አንዲቱም ፡ ቀን ፡ ፈንታ ፡ ሁለት ፡ እጥፍ፡ አድርጌ፡እከፍልሻለሁ።
፲፫፤ እስመ ፡ መሰኩከ ፡ መንገለ ፡ ይሁዳ ፡ ወከመ ፡ ቀስት ፡ መላእክየ ፡ ለኤፍሬም ፡ ወአነሥአሙ ፡	፲፫፤ ይሁዳ ፡ ወደኔ ፡ አቅርቤሃለሁና ፡ ኤፍሬምንም፡ እንደ ፡ ቀስት ፡ አጥብቄ ፡ ይገፍዋለሁና ፡ ጽዮን፡

Scanned by CamScanner

ዘዕለተ፡ሆሣዕና።	የሆሣዕና፡ዕለት።
ለደቂቅኪ፡ጽዮን፡ላዕለ፡ደቂቀ፡አረሚ፡ወእ ሬስየኪ፡ከመ፡ኩናተ፡መስተቃትል።	ልጆችሽን፡በአረማውያን፡ልጆች፡ላይ፡አስነሣ ችዋለሁ፤እንደ፡አርበኛ፡ጦርም፡አደርግሻለሁ።
፲፬፤ ወእግዚአብሔር ፡ ያስተርኢ ፡ ላዕ ሌሆሙ ፡ ወትወፅእ ፡ ማእበልት ፡ ከመ ፡ መብረቅ።	፲፬፤ እግዚአብሔርም ፡ በእነሱ ፡ ላይ ፡ ይገለጣል ፤ ፈጣን ፡ ሰይፍም ፡ እንደ ፡ መብረቅ ፡ ፈጥና ፡ ትወጣለች።
፲፭፤ ወእግዚአብሔር ፡ ዘሠለሞ ፡ ይመልክ ፡ ይነፍሕ ፡ በቀርን ፡ ወየሐውር ፡ መዐቱ ፡ ከመ ፡ አውሎ ፡ ቴማን።	፲፭፤ ሁሉን ፡ የሚገዛ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ነጋሪቱን ፡ ይመታል ፤ ቁጣውም ፡ እንደ ፡ ቴማን ፡ ጥቅል ፡ ነፋስ ፡ ይሄዳል።
ዘኢሳይያስ ፡ ነቢይ ፡ በረከቱ ፡ ትኩን ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን።	ነቢዩ ፡ ኢሳይያስ ፡ የተናገረው ፡ ትንቢት ፡ ይህ ፡ ነው። በረከቱ ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ለዘላለሙ ፡ ትኑር ፡ አሜን።
ምዕ ፡ ፶፱ ፡ ፩—፲፮።	ምዕ ፡ ፶፱ ፡ ፩—፲፮።
፩፤ ወይእዜኒ ፡ ከመዝ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘፈጠረኒ ፡ በውስተ ፡ ከርሠ ፡ እምየ ፡ ከመ ፡ እኩን ፡ ገብሮ ፡ ከመ ፡ አስተጋብኦ ፡ ለያዕቆብ ፡ ኀቤሁ ፡ ወለእስራኤልኒ ፡ ይቤ ፡ እትጋባእ ፡ ምስሌሆሙ ፡ ወእሴባሕ ፡ በቅድመ ፡ እግዚአ ብሔር ፡ ወይከውነኒ ፡ አምላኪየ ፡ ኃይልየ።	፩፤ አሁንም ፡ ያዕቆብን ፡ ወደሱ ፡ እመልስ ፡ ዘንድ ፡ እስራኤልንም ፡ እሰበስበው ፡ ዘንድ ፡ ባርያው ፡ ልሆን ፡ በእናቴ ፡ ማኅፀን ፡ የፈጠረኝ ፤ እግዚአ ብሔር ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ ከነሳቸው ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ እሆናለሁ ፤ በእግዚአብሔርም ፡ ፊት ፡ እከብ ራለሁ ፤ ፈጣሪዬም ፡ አጋዥ ፡ ይሆነኛል ፡ አለ።
፳፪፤ እስመ ፡አብሰ ፡ኢይኴንን ፡ወኢመነሂ ፡አላ ፡ ኵሎ ፡ኵነኔሁ ፡አወፈዮ ፡ለወልዱ።	፳፪፤ አብ ፡ በማንም ፡በማን ፡አይፈርድም ፤ ፍርዱን፡ ሁሉ ፡ለልጁ ፡ሰጠው ፡እንጂ።
፳፫፤ ከመ ፡ ኵሉ ፡ ሰብእ ፡ ያክብርዎ ፡ለወልድ ፡ በከመ ፡ያክብርዎ ፡ለአብ ፤ ወዘሰ ፡ኢያክብሮ ፡ ለወልድ ፡ ኢያክብሮ ፡ለአብ ፡ ዘፈነዎ።	፳፫፤ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ አብን ፡ እንደሚያከብሩት ፡ ወልድንም ፡ ያክብሩ ፡ዘንድ ፡ወልድን ፡ የማያክ ብረው ፡ግን ፡የላከው ፡አብን ፡ አያከብረውም።

Scanned by CamScanner

ዘዕለተ፡ሆሣዕና።

፳፬፤ አማን፡አማን፡እብለክሙ፡ዘይሰምዕ፡ቃልየ፡ወየአምን፡በዘፈነወኒ፡ይረክብ፡ሕይወተ፡ዘለዓለም፡ወኢየሐውር፡ውስተ፡ደይን፡አላ፡ዐደወ፡እሞት፡ውስተ፡ሕይወት።

፳፭፤ አማን፡አማን፡እብለክሙ፡ከመ፡ይበጽሕ፡ጊዜሁ፡ወይእዜ፡ውእቱ፡ከመ፡ምውታን፡ይሰምዕዎ፡ቃሎ፡ለወልደ፡እግዚአብሔር፡ወእለሰ፡ሰምዕዎ፡የሐይዉ።

፳፮፤ ወበከመ፡ለአብ፡ቦቱ፡ሕይወት፡ኀቤሁ፡ከማሁ፡ለወልድኒ፡ወሀቦ፡ከመ፡ይኩን፡ሕይወት፡ኀቤሁ።

፳፯፤ ወወሀቦ፡ሥልጣነ፡ከመ፡ይግበር፡ፍትሐ፡ወኮነኔ፡እስመ፡ወልደ፡እግዚአብሔር፡ወልደ፡ዕጓለ፡እመሕያው፡ውእቱ።

፳፰፤ ወበእንተ፡ዝንቱሰ፡ኢታንክሩ፡እስመ፡ትመጽእ፡ሰዓት፡በዘይሰምዕዎ፡ቃሎ፡ኵሎሙ፡እለ፡ውስተ፡መቃብር።

፳፱፤ ወይወፅኡ፡እለ፡ሠናየ፡ገብሩ፡ውስተ፡ትንሣኤ፡ዘለሕይወት፡ወእለሰ፡እኩየ፡ገብሩ፡ውስተ፡ትንሣኤ፡ዘለደይን።

፴፤ ኢይክል፡አንሰ፡ገቢረ፡ለልየ፡ዘእምኀቤየ፡ወኢምንተኒ፡አላ፡በከመ፡ሰማዕኩ፡እኴንን፤ ወኮነኔየኒ፡ጽድቅ፡ውእቱ፡እስመ፡ኢየኀሥሥ፡ፈቃደ፡ዚአየ፡ዘእንበለ፡ፈቃዱ፡ለዘፈነወኒ።

ይ፡ካ፡ዘየአምን፡በወልድ፡ቦ፡ሕይወት፡ዘለዓለም፡ይቤ፡እግዚእ፡ለአርዳኢሁ።

(ይሕ)፡ነአምን፡በቃለ፡ወንጌልከ፡ቅዱስ።

ክፍል፡፬።

ሃይማኖተ፡አበው።

ምዕ፲፯፡፩–፲፱።

፩፤ ይቤሉ፡፲ወ፪ቱ፡ሐዋርያት፡ወጳውሎስ፡ሐዋርያ፡ወያዕቆብ፡እኁሁ፡ለእግዚእነ፡ወሄ፡ዲያቆናት፡ሮወ፪ቱ፡አርድእት፡በዲድስ፡ቅልያ፡በእንተ፡ርትዕት፡ሃይማኖት፡ወቅድስት፡ሥላሴ።

ዘሰበኩ፡ለነ፡በጽድቅ፡ወንሕነኒ፡ደቂቀ፡እግዚአብሔር፡ወውሉደ፡ሰላም፡ንሰብከ፡ዘንተ፡ቃለ፡ቅዱሰ፡ለእለ፡ይትኤዘዙ፡በርትዕ።

የሆሣዕና፡ዕለት።

፳፬፤ እውነት፡እውነት፡እላችኋለሁ፤ ቃሌን፡የሚሰማ፡በላከኝም፡የሚያምን፡የዘላለም፡ሕይወትን፡ያገኛል፤ ወደ፡ደይንም፡አይሄድም፤ከሞት፡ወደ፡ሕይወት፡ተሻገረ፡እንጂ።

፳፭፤ ጊዜው፡እንዲደርስ፡እውነት፡እውነት፡እላችኋለሁ፤ ሙታን፡የእግዚአብሔርን፡ልጅ፡ቃል፡የሚሰሙበት፡ጊዜም፡ዛሬ፡ነው፤ የሰሙትም፡ይድናሉ።

፳፮፤ ለአብ፡ከርሱ፡ዘንድ፡ሕይወት፡እንዳለው፡ሕይወት፡ከእርሱ፡ይሆን፡ዘንድ፡ለወልድም፡ሰጠው።

፳፯፤ ይፈርድ፡ዘንድ፡ሥልጣን፡ሰጠው፤የእግዚአብሔር፡ልጅ፡የሰው፡ልጅ፡ነውና።

፳፰፤ ስለዚህስ፡አታድንቁ፤በመቃብር፡ያሉ፡ሁሉ፡ቃሉን፡የሚሰሙበት፡ሰዓት፡ትመጣለችና።

፳፱፤ መልካም፡የሠሩ፡ለሕይወት፡ትንሣኤ፡ክፉ፡የሠሩም፡ለፍርድ፡ትንሣኤ፡ይነሣሉና።

፴፤ እኔ፡ራሴ፡ከራሴ፡አንቅቼ፡ምንም፡አልሠራም፤እንደሰማሁ፡እፈርዳለሁ፡እንጂ፡ፍርዴም፡እውነት፡ነው። የላከኝን፡ፈቃድ፡እንጂ፡የኔን፡ፈቃድ፡አልሻምና።

ካህኑ፡በወልድ፡ያመነ፡የዘላለም፡ሕይወት፡አለው፡አለ፡ጌታ፡ለደቀ፡መዛሙርቱ፡ይበል።

ሕዝቡ፡በከበረ፡ወንጌል፡ቃል፡እናምናለን፡ይበሉ።

ክፍል፡፬።

የአባቶች፡ሃይማኖት።

ምዕ፲፯፡፩–፲፱።

፩፤ በእውነት፡ያስተማሩ፡አሥራ፡ሁለቱ፡ሐዋርያት፡እና፡ሐዋርያው፡ጳውሎስ፡የጌታ፡ወንድም፡ያዕቆብና፡፯ቱ፡ዲያቆናት፡ሮ፪ቱ፡አርድእት፡የምሥጢረ፡ሥጋዌን፡የምሥጢረ፡ሥላሴን፡ነገር፡በተናገሩበት፡በዲድስቅልያ፡እንዲህ፡አሉ፤

የእግዚአብሔር፡አገልጋዮች፡የሰላም፡ልጆች፡እኛም፡በእውነት፡ጸንተው፡ለሚታዘዙ፡ይህንን፡የከበረ፡ትምህርት፡እናስተምራለን።

Scanned by CamScanner

ዘዕለተ፡ሰሓፅና።

መዝ፡፷፪፡፮።ሮሜ፡፰፡፳፯።

፪፡ ነአምን ፡ በአሐዱ ፡ አምላክ ፡ ገባሬ ፡ ሁሉ ፡ ፍጥረት ፡ አብ ፡ ለእግዚእነ ፡ ወአምላክነ ፡ ወመድኃኒነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ። እስመ ፡ አልቦ ፡ ውስተ ፡ ህላዌሁ ፡ አመክንዮ።

ዮሐ፡፩፡፲፯–፲፰።፲፡፴፯።ማር፡፩፡፲፩።፪ቆሮ፡፩፡፫።

መዝ፡፹፱፡፪።

፫፡ በከመ ፡ አቅደምነ ፡ ነጊረ ፡ አላ ፡ ባሕቲቱ ፡ ህልው ፡ በሁሉ ፡ መዋዕል ፡ አልቦቱ ፡ ጥንት ፡ ወኢተፍ ፡ ጸሜት።

፬፡ ወቦቱ ፡ ብርሃን ፡ ዘኢይጠፍእ ፡ ወአልቦ ፡ ዘይክል ፡ ቀሪበ ፡ ኀቤሁ።

፭፡ ኢኮነ ፡ ፪ተ ፡ ወኢ፫ተ ፡ ወኢይትዌሰክ ፡ አላ ፡ አሐዱ ፡ ውእቱ ፡ ባሕቲቱ ፡ ዘይነብር ፡ ለዓለም።

ኤፌ፡፬–፮።

፮፡ እስመ ፡ ኢኮነ ፡ ሥውረ ፡ ዘኢይትአመር ፡ ጸዕሙ ፡ ጥዩቀ ፡ አእመርናሁ ፡ በአሪት ፡ ወበነቢያት።

፯፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ አኀዜ ፡ ኵሉ ፡ ወመ ልዕልተ ፡ ኵሉ ፡ ወሥሉጥ ፡ ላዕለ ፡ ኵሉ ፡ ፍጥረት።

ዘዳ፡፴፪፡፮።መዝ፡፵፫፡፭–፮።ዕብ፡፩፡፩።ራዕ፡ዮሐ፲፩፡፫–፭።

፰፡ እግዚአብሔር ፡ አብ ፡ ለእግዚእነ ፡ ወመድኃኒነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ዘተወልደ ፡ እምቅድመ ፡ ይትፈጥር ፡ ዓለም ፡ ወልድ ፡ ዋሕድ ፡ ዘዕሩይ ፡ ምስሌሁ።

፱፡ ገባሬ ፡ ኵሉ ፡ ሠራዊት ፡ ወሚመታት ፡ ወሥልጣናት ፡ ዘሠምረ ፡ ይኩን ፡ ሰብአ ፡ በደኀረ ፡ መዋዕል።

፲፡ ወነሥአ ፡ ሥጋ ፡ እምእግዝእትነ ፡ ማርያም ፡ ቅድስት ፡ ድንግል ፡ ዘእንበለ ፡ ዘርአ ፡ ብእሲ።

ገላ፡፬፡፬።ቈላ፡፩፡፲፭–፲፰።ዮሐ፡፩–፲፰።

፲፩፡ ወተሐፅነ ፡ ከመ ፡ ሰብእ ፡ ዘእንበለ ፡ ኃጢአት ፡ ወአበሳ ፡ ወአልቦ ፡ ጕሕሉት ፡ ውስተ ፡ አፉሁ።

ሉቃ፡፩፡፶፪።ኢሳ፡፶፫፡፱።ዮሐ፡፰፡፵፮።፩ጴጥ፡፪፡፳፪።

፲፪፡ ወእምገሠ ፡ ሐመ።

የሆሣዕና ፡ ዕለት።

መዝ፡፷፪፡፮።ሮሜ፡፰፡፳፯።

፪፡ ሁሉን ፡ በፈጠረ ፡ በአንዱ ፡ አምላክ ፡ በጌታችን ፡ በፈጣሪያችን ፡ በመድኃኒታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አባት ፡ በእግዚአብሔር ፡ አብ ፡ እናምናለን ። በባሕርዩ ፡ አስገኝ ፡ የለውምና።

ዮሐ፡፩፡፲፯–፲፰።፲፡፴፯።ማር፡፩፡፲፩።፪ቆሮ፡፩፡፫።

መዝ፡፹፱፡፪።

፫፡ አስቀድመን ፡ እንደተናገርን ፡ በዘመኑ ፡ ሁሉ ፡ በአስገኝነት ፡ ያለ ፡ እርሱ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ጥንት ፡ ፍጻሜ ፡ የለውም።

፬፡ የማይለወጥ ፡ ብርሃን ፡ አለው ። ወደርሱ ፡ መቅረብ ፡ የሚቻለው ፡ የለም።

፭፡ ሁለት ፡ አይደለም ፤ ሦስትም ፡ አይደለም ፡ ተጨማሪም ፡ የለበትም ፤ ለዘላለም ፡ ጸንቶ ፡ የሚኖር ፡ አንድ ፡ እሱ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ እንጂ።

ኤፌ፡፬–፮።

፮፡ የማይታወቅ ፡ የተሠወረ ፡ አይደለምና ፡ በአሪት ፡ በነቢያት ፡ ፈጽመን ፡ አውቀነዋል ፡ እንጂ።

፯፡ ሁሉን ፡ የፈጠረ ፡ ከሁሉ ፡ በላይ ፡ ያለ ፡ በፍጥረት ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ሥልጣን ፡ ያለው ፡ እንደሆነ።

ዘዳ፡፴፪፡፮።መዝ፡፵፫፡፭–፮።ዕብ፡፩፡፩።ራዕ፡ዮሐ፲፩፡፫–፭።

፰፡ ዓለም ፡ ሳይፈጠር ፡ የተወለደ ፡ የጌታችን ፡ የፈጣሪያችን ፡ የመድኃኒታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አባቱ ፡ እግዚአብሔር ፡ አብ ፡ አንድ ፡ ነው። ወልድ ፡ ዋሕድ ፡ ከእርሱ ፡ ጋራ ፡ ትክክል ፡ የሚሆን ፡ የባሕርይ ፡ አምላክ ፡ ነው።

፱፡ ሠራዊትን ፡ ሚመታትን ፡ ሥልጣናትን ፡ ሁሉ ፡ የፈጠረ ፡ በኋላ ፡ ዘመን ፡ ሰው ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ የወደደ።

፲፡ ያለ ፡ ዘርአ ፡ ብእሲ ፡ ንጽሕት ፡ ድንግል ፡ ከምትሆን ፡ ከእመቤታችን ፡ ማርያም ፡ ሥጋን ፡ የነሳ።

ገላ፡፬፡፬።ቈላ፡፩፡፲፭–፲፰።ዮሐ፡፩–፲፰።

፲፩፡ ኃጢአት ፡ ሳይሰራ ፡ እንደ ፡ ሰው ፡ በየጥቂቱ ፡ አደገ ፤ በአንደበቱም ፡ ሐሰት ፡ የለበትም።

ሉቃ፡፩፡፶፪።ኢሳ፡፶፫፡፱።ዮሐ፡፰፡፵፮።፩ጴጥ፡፪፡፳፪።

፲፪፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በሥጋ ፡ ታመመ።

Scanned by CamScanner

ዘዕለተ፡ሆሣዕና።

ክፍል፡፩።

ወሀየንተ፡ክብር፡ይእቲ፡ያንብቡ፡ዘንተ።
ዘኢሳይያስ፡ነቢይ፡በረከቱ፡ትኩን፡ምስሌነ፡
ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ምዕ፡፷፪፡፩-፲፩።

፩፤ ሑሩ ፡ ባኡ ፡ እንተ ፡ አንቀጽየ ፡ ወጺሁ ፡ ፍናትየ፡ ለሕዝብየ ፡ ወአእትቱ ፡ እም ፍናት ፡ እብነ ፡ ወንሥኡ ፡ ትእምርተ ፡ ለአ ሕዛብ።

፲፤ ናሁ፡እግዚአብሔር፡ ይገብር፡መንክረ፡እስከ፡ አጽናፈ፡ምድር፡በልዎ፡ለወለተ፡ጽዮን፡ነዋ፡ ንጉሥኪ ፡ በጽሐ ፡ ወምስሌሁ ፡ ዕሤቱ ፡ ወምግባሩ፡ቅድመ፡ገጹ።

፲፩፤ ወትሰመዩ፡ሕዝበ፡ቅዱሰ፡ዘአድኅነ፡እግዚአ ብሔር ፡ አንቲኒ ፡ ትሰመዪ ፡ ሀገረ ፡ ቅድስተ ፡ እንተ ፡ ይፈቅድዋ ፡ ወአኮ ፡ እንተ ፡ የኃድግዋ ። ተስእለ፡እምነቢይ፡ወተሰጥዎ፡እመልአክ።

ምዕ፡፷፫፡፩።

፩፤ መኑ ፡ ዝንቱ ፡ ዘወፅአ ፡ እምኤዶም ፡ ቀይሐ ፡ አልባስ ፡ እምባሶር ፡ መካሕ ፡ ብእሲ ፡ ጎያል ፡ ወግሩም ፡ በልብሰቱ ፡ አነ ፡ ዘእት ዋቀስ ፡ በእንተ፡ ጽድቅ ፡ ወእፈትሕ ፡ ለአድኅኖ።

የሆሣዕና፡ዕለት።

ክፍል፡፩።

በክብር፡ይእቲ፡ፈንታ፡ይህን፡ያንብቡ።
የነቢዩ ፡ ኢሳይያስ ፡ ትንቢት ፡ በረከቱ ፡ ከኛ ፡ ጋር፡ለዘላለሙ፡ትኑር፡አሜን።

ምዕ፡፷፪፡፩-፲፩።

፩፤ ሂዳችሁ፡ወደ፡አገሬ፡ወደ፡ኢየሩሳሌም፡ግቡ፤ለወ ገኖቼም ፡ ገሥዳናን ፡ ጥረጉ ፤ ከገሥዳናም ፡ ድንጋዮ ቹንም፡አስወግዱ፤ለአሕዛብም፡ሰንደቅ፡አላማን፡ ያዘ።

፲፤ እነሆ ፡እግዚአብሔር ፡ እስከ ፡ ምድር ፡ ዳርቻ ፡ ድረስ ፡ ድንቅ ፡ ተአምራትን ፡ ያደርጋል ። የጽዮን ፡ ልጅ ፡ እነሆ ፡ ንጉሥሽ ፡ ደረሰ ። ዋጋውም ፡ (ሚጠት) ፡ ከእርሱ ፡ ጋራ ፡ አለ ፡ ሥራውም፡በፊቱ፡ነው፡በሏት።

፲፩፤ እግዚአብሔር ፡ ያዳናቸው ፡ የከበሩ ፡ ወገኖች ፡ ትባላላችሁ ፤ አንቺም ፡ የሚጠሏት ፡ ያይደለ ፡ የሚወዷት፡የከበረች፡አገር፡ትባያለሽ።

ምዕ፡፷፫፡፩።

፩፤ ቀይ ፡ ልብስን ፡ ለብሶ ፡ ከባሶር ፡ ከኤዶም ፡ ያለ ፡ የወጣ ፡ የሚመካ ፡ ጎይለኛ ፡ ሰው ፡ በአለባ በሱም ፡ ግሩም ፡ የሆነ ፡ ይህ ፡ ማነው ፡ ሲል ፡ ከነቢዩ፡የተገኘ፡ጥያቄ፡ከመልአኩ፡የተሰጠ፡ መልስ፡ይህ፡ነው።

ዝማሬ፡ዘሆሣዕና፡ ግዕዝ፡ወዕዝል።እስመ፡ለዓለም፡ምሕረቱ፡ሑሩ፡በልዎ፡ለእገሌ፡ይቤለክ፡ሊቅ፡አይቱአ፡ጽርሑ፡ጎበ፡ እገብር፡ፋሲካ፡ምስለ፡አርዳእየ፡አይቱአ፡ጽርሑ፡ጎበ፡እገብር፡ፋሲካ፡ምስለ፡እሊአየ።አይቱአ፡ጽርሑ፡ጎበ፡እገብር፡ፋሲካ፡ ምስለ፡ሐዋርያትየ።ውእቱ፡ያርእየክሙ፡ጽርሐ፡ንጹሐ፡ርሱየ፡ወሥርግወ፡በሀየ፡እገብር፡ፋሲካ።ዘበልዐ፡ሥጋየ፡በሀየ፡ እገብር፡ፋሲካ።ወሰትየ፡ደምየ።በሀየ፡እገብር፡ፋሲካ።እስመ፡ዝንቱ፡ጎበስት፡ዘእሁበክሙ፡እነ፡ለሕይወት፡ውእቱ፡እስመ፡ ዝንቱ፡ጽዋዕ፡ዘአሚጥወክሙ፡እነ፡ለመድኃኒት፡ውእቱ።በክሙ፡ፈነወኒ፡አቡየ፡ከማሁ፡እነኒ፡እፌንዎክሙ።

ክፍል፡፪።

ወእምድኅረ ፡ ተፈጸመ ፡ ጸሎተ ፡ ቅዳሴ ፡ ዘቊርባን ፡ ይንበሩ ፡ ኵሉ ፡ ሕዝብ ፡ በመዓዝን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ቅድስት።
ወይቁሙ ፡ ሰብዓቱ ፡ ካህናት ፡ እለ ፡ ውስተ ፡ መሥዋዕት ፡ መንገለ ፡ ምሥራቅ ፡ ውስተ ፡ ቅኔ ፡ ማሕሌት።
(ይዲ)፡ ተንሥኡ ፡ ለጸሎት፤
(ይሕ)፡እግዚኦ፡ ተሣሃለን
(ይካ)፡ ሰላም ፡ ለኵልክሙ
(ይሕ)፡ ምስለ ፡ መንፈስከ።

ክፍል፡፫።

የቅዳሴው ፡ ጸሎት ፡ ከተፈጸመ ፡ በኋላ ፡ በከበረች፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በአራቱ ፡ ማእዘን፡ በዓውደ ፡ ምሕረቱ ፡ ይቀመጡ ። መሥዋዕት ፡ ያሳረጉ ፡ ሰባት ፡ ካህናት ፡ ከቅኔ ፡ ማሕሌቱ ፡ ወርደው ፡ ፊታቸውን ፡ ወደ ፡ ምሥራቅ ፡ መልሰው ፡ ይቁሙ።
(ዲያቆኑ)፡ ለጸሎት ፡ ተነሡ ፡ ይበል።
(ሕዝቡ)፡አቤቱ፡ ይቅር ፡ በለን ፡ ይበሉ፤
(ካህኑም)፡ ሰላም ፡ ለናንተ ፡ ይሁን ፡ ይበል።
(ሕዝቡ)፡ ከመንፈስህ ፡ ጋራ ፡ ይበሉ።

Scanned by CamScanner

ዘዕለተ፡ሆሣዕና።	የሆሣዕና፡ዕለት።
፩፤ ይላ፡ወካዕበ፡ናስተበቍዕ፡ዘሎሎ፡ይእኅዝ፡እግዚአብሔር፡አብ፡ለእግዚእ፡ወመድኀኒን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ።	፩፤ ካህኑ፡ሁሉን፡የሚይዝ የጌታችንና፡የመድኃኒታችን፡የኢየሱስ፡ክርስቶስ፡አባት፡እግዚአብሔርን፡ዳግመኛ፡እንማልደዋልን፡ይበል።
፪፤ እግዚእ ፡ ሕያዋን ፡ ወሕይወተ ፡ ሙታን ፡ ተስፋ፡ ቅቡጻን ፡ ረዳኤ ፡ ምንዱባን ፡ ወመንጽሔ ፡ ኀጥአን ። ዘሞተ ፡ አዕራዕከ ፡ ወማእሠረ ፡ ሰይጣን፡ በቲከከ ፡ ሕይወተ ፡ ለትዝምደ፡ሰብእ፡ጸንከ።	፪፤ የሕያዋን፡ጌታ፡የሙታን፡ሕይወት፡ተስፋ፡ለቆረጡት፡አለኝታ፡ለተቸገሩት፡የምትረዳ፡ኃጥአንን፡የምታነጻ፡ሞትን፡ያጠፋህ፡የሰይጣንን፡ወጥመድ፡ቆርጠህ፡ለሰው፡ትውልድ፡ሕይወትን፡የሰጠህ።
፫፤ ኀቢከ ፡ ንስእል ፡ ወናስተበቍዕ ፡ ዘኢት መውት፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ ዘመዝገበ ፡ ሕይወት፡ኀቢከ፡ውእቱ።	፫፤ የሕይወት ፡ መዝገብ ፡ በአንተ ፡ ያለ ፡ ለዘለዓለም፡የማትሞት፡አቤቱ፡ወደ፡አንተ፡እንለምናል ፤ እንማልዳለንም ። የሕይወት ፡ መዝገብ፡በአንተ፡ዘንድ፡ነው።
፬፤ በእንተ፡እለ፡ኖሙ፡ወበሃይማኖት፡አዕረፉ፡አበው ፡ ቀደምት ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፤ ጳጳሳት ፡ ወኤጲስቆጶሳት ፤ ቀሳውስት ፡ ወዲያቆናት ፡ አናጕንስጢስ፡ወመዘምራን	፬፤ በሃይማኖት፡ጸንተው፡ስለሞቱ፡ስለ፡ቀደሙ፡አባቶች፡ስለ፡ሊቃነ፡ጳጳሳት፡ጳጳሳትና፡ስለ፡ኤጲስቆጶሳት ፤ ስለቀሳውስትና ፡ ዲያቆናት ፡ ስለ፡አንባቢዎችና፡ስለ፡መዘምራን፤
፭፤ ደናግል፡ወመነኮሳት፡መዓስባት፡ወሕፃናት፡ዕቤራት፡ወዕጓለ፡ማውታ።	፭፤ ስለ ፡ ደናግልና ፡ ስለ ፡ መነኮሳት ፡ ስለ ፡ ሕፃናትና፡ስለ፡ባልቴቶች፡አባት፡እናት፡ስለ፡ሌላቸው።
፮፤ በእንተ ፡ ነፍሳተ ፡ ምእመናን ፡ ወበእንተ ፡ ኵሎሙ ፡ እለ ፡ ሀለዉ ፡ ዝየ ፡ ወውስተ ፡ ዝ ፡ መካን፡ዘአንተ፡ጸዋዕከ፡እምውስተ፡ሕዝብከ፡በጽድቅ ፡ ወበርትዕ ፡ አእርፍ ፡ ነፍሶሙ ፡ ውስተ፡መካን ፡ሥውር ፡ወኀበ ፡ማየ ፡ዕረፍት ፡ ውስተ ፡ ሕፅን ፡ አብርሃም ፡ ይስሐቅ ፡ ወያዕቆብ።	፮፤ ስለ ፡ ምዕመናን ፡ ነፍሳት ፡ ከወገኖችህ ፡ ለይተህ፡ በእውነት ፡ በሚገባ ፡ ስለ ፡ ጠራሀቸው፡ በዚህ ፡ ቦታ ፡ ስላሉ ፡ ሰዎችም ፡ ሁሉ ፡ በለመለመ ፡ ቦታ፡ በዕረፍት ፡ ውኃ ፡ ዘንድ፡በአብርሃምና፡በይስሐቅ፡በያዕቆብም፡አጠገብ፡ነፍሳቸውን፡አሳርፍ።
፯፤ በእንተ ፡ ነፍሰ ፡ ክርስቲያን ፡ ዘለ ዕረፍት ፡ ሥልጣን ፡ ብከ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክነ።	፯፤ ስለ ፡ ክርስቲያን ፡ ነፍስ ፡ ዕረፍትን ፡ ለመስጠት፡ሥልጣን፡ያለህ፡አምላካችን፡እግዚአብሔር፡አንተ፡ነህ።
፰፤ (ይ ፡ ዲ) ፡ ጸልዩ ፡ በእንተ ፡ እለ ፡ ኖሙ ፡ አበዊነ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ ወአበዊነ ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ወአበዊነ ፡ ቀሳውስት ፡ ወአኀዊነ ፡ ዲያቆናት ፡ ወአበዊነ ፡ መነኮሳት ፡ ወአኀዊነ ፡ ሕዝባውያን፡ ወአኀቲነ ፡ አንስት ፡ ከመ ፡ ያዕርፍ ፡ እግዚእ ፡ ነፍሳቲሆሙ ፡ በሰላም ፡ ወይስረይ ፡ ለነ ፡ ኃጣውኢነ።	፰፤ (ዲያቆኑ)፡ስለ፡ሞቱት፡አባቶቻችን፡የጳጳሳት፡አለቆችና፡ስለ፡አባቶቻችን፡ጳጳሳት፡ስለ፡አባቶቻችን ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ስለ፡ አባቶቻችን ፡ ቀሳውስት ፤ ስለ ፡ ወንድሞቻችን ፡ ዲያቆናት፡ስለ፡ አባቶቻችን ፡ መነኮሳት ፡ ወንድሞቻችን፡ስለሆኑ ፡ ሕዝብ ፡ እኅቶቻችን ፡ ስለ ፡ ሆኑ ፡ ስለ፡ሴቶች ፡ ጸልዩ ፤ እግዚአብሔር ፡ በመንግሥተ፡ሰማያት፡ነፍሳቸውን፡ያሳርፍ፡ዘንድ፡ኃጢአታችንንም፡ይቅር፡ይለን፡ዘንድ፡ይበል።
፱፤ (ይ፡ሕ)፡መሐራ፡እግዚእ፡ለነፍሰ፡ክርስቲያን፡	፱፤ ሕዝቡ፡አቤቱ፡የክርስቲያንን፡ነፍስ፡ማራት፡

Scanned by CamScanner

ዘዕለተ፡ሆሣዕና።	የሆሣዕና፡ዕለት።
ወመሐሮሙ ፡ ለኵሎሙ ፡ አግብርቲከ ወአእ ማቲከ።	የአገልጋዮችህን ፡ የሴቶችንና ፡ የወንዶችን፡ ነፍስ፡ሁሉ፡ማርልን፡ይበሉ።
፲፣ ይካ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘኵሎ ፡ ትእኅዝ ፡ ንስእለከ፡ ወናስተበቍዓከ ፡ ነፍሳተ ፡ አግብ ርቲከ፡ወአእማቲከ።	፲፣ ካህኑ፡ሁሉን፡የምትይዝ፡እግዘአብሔር፡ሆይ፡ ስለሞቱት፡ወንዶችና፡ሴቶች፡አገልጋዮችህ፡ እንለምንሃለን፡እንማልድሃለን፡ይበል።
፲፩፣ በእንተ ፡ ነፍሰ ፡ አግብርቲከ ፡ አኃዊነ ፡ ክርስ ቲያን፡ቮጊዜ።	፲፩፣ ስለ ፡ አገልጋዮችህ ፡ ወንድሞቻችን ፡ ክርስቲ ያኖች፡ነፍስ፡ማራት፡ይበል፡ሦስት፡ጊዜ።
፲፪፣ (ይ፡ሕ)፡መሐራ፡እግዚኦ፡ለነፍሰ፡አግብርቲከ፡ ወአእማቲከ፡ኵሎሙ፡ክርስቲያን፡ቮተ፡ጊዜ።	፲፪፣ ሕዝቡ ፡ የአገልጋዮችህን ፡ የክርስቲያኖችን ፡ ነፍስ፡ማራት፡ይበሉ፡ሦስት፡ጊዜ።
፲፫፣ ወበእንተ፡ነፍሳተ፡ክርስቲያን፣	፲፫፣ ስለ፡ክርስቲያን፡ነፍሳት፣
፲፬፣ መሐሮሙ ፡ ለኵሎሙ ፡ አግብርቲከ ፡ ወአእ ማቲከ።	፲፬፣ አገልጋዮችህን ፡ ሁሉ ፡ ማራቸው ፡ ይበሉ።
፲፭፣ (ይ፡ካ)፡ወበእንተ፡ኵሎሙ፡እለ፡ገየ፡ሀለዉ፡ ዘአንተ ፡ ጸዋዕከ ፡ እምውስተ ፡ ሕዝብከ ፡ በጽድቅ፡ወበርትዕ፡ሕፅን፡ነፍሶሙ፡ውስተ፡ መካን ፡ ሥውር ፡ ኅበ ፡ ማየ ፡ ዕረፍት ፡ ውስተ ፡ ሕፅነ ፡ አብርሃም ፡ ይስሐቅ ፡ ወያዕቆብ ፡ ውስተ፡ገነተ፡ትፍሥሕት።	፲፭፣ (ካህኑም) ፡ ከወገኖችህ ፡ አንተ ፡ በእውነት ፡ በሚገባ ፡ ጠርተሃቸው ፡ በዚህ ፡ ቦታ ፡ ስለ ፡ አሉትም ፡ ሰዎች ፡ እንለምንሃለን ፡ ነፍሳ ቸውን፡ በለመለመ ፡ ቦታ ፡ በዕረፍት ፡ ውኃ ፡ ዘንድ ፡ በአብርሃም ፡ በይስሐቅ ፡ በያዕቆብ ፡ አጠገብ፡በመንግሥተ፡ሰማያት፡አሳርፍ።
፲፮፣ በመራሕያነ፡ብርሃን፡መላእክቲከ፡ደምር፡ነፍ ሳቲሆሙ ፡ ምስለ ፡ ቅዱሳኒከ ፡ ውስተ ፡ ዘለዓለም፡ማኅደርከ።	፲፮፣ ወደ ፡ ብርሃን ፡ በሚመሩ ፡ በመላእክትህ ፡ መሪነት፡በዘለዓለማዊት፡ማደሪያህ፡ውስጥ፡ ነፍሳቸውን፡አሳድር።
፲፯፣ ወሥጋሆሙኒ ፡ አንሥእ ፡ በዕለት ፡ እንተ ፡ ባቲ ፡ ሠራዕከ ፡ በከመ ፡ ቅዱስ ፡ ወቡሩክ ፡ ዘኢይትሔሰው፡ተስፋከ፡ዘበሰማያት፡መንግ ሥትከ።	፲፯፣ ሥጋቸውንም ፡ ትንሣኤን ፡ በሠራህባት ፡ በቀጠሮህ ፡ ቀን ፡ አሥነሣ ፡ የማይታበል ፡ ተስፋህ ፡ ቅዱስ ፡ ቡሩክ፡ እንደመሆኑ ፡ መንግሥተ፡ሰማያትን፡አድላቸው።
፲፰፣ (ይሕ) ፡ መሐራ ፡ እግዚኦ ፡ ለነፍሰ ፡ ገብርከ ፡ ወመሐሮሙ ፡ ለኵሎሙ ፡ አግብርቲከ ፡ ወአእ ማቲከ፡ቮተ፡ጊዜ።	፲፰፣ (ሕዝቡ)፡አቤቱ፡የባለሟልህን፡ነፍስ፡ማራት፡ ባሮችህንም ፡ ሁሉ፡ ወንዶችንና ፡ ሴቶችን ፡ ሁሉን፡ማራቸው፡ይበሉ፡ሦስት፡ጊዜ።
፲፱ (ይካ)፡እስመ፡አልቦሙ፡ለአግብርቲከ፡ሞት፡ አላ፡ፍልሰት።	፲፱፣ (ካህኑ) ፡ ለአገልጋዮችህ ፡ ከዚህ ፡ መሄድ ፡ እንጂ፡ሞት፡የለባቸውምና።
፳፣ ወለእመ፡ቦ፡ዘአበሱ፡ወዘተሠወሮሙ፡ሕገ፡ ሰብእ፡አናሕሲ፡ሎሙ።	፳፣ በድለውም ፡ የተሠወራቸው ፡ ቢኖር ፡ ሰው ፡ እንደመሆናቸው፡መጠን፡ይቅር፡በላቸው።
፳፩፣ እስመ፡ኄር፡ወመፍቀሬ፡ሰብእ፡አንተ፡እግዚ አብሔር ፡ እስመ ፡ አልቦ ፡ ንጹሕ ፡ እምር ስሐት፡በቅድሜከ።	፳፩፣ እግዚአብሔር! ቸርና፡ሰውን፡ወዳጅ፡አንተ፡ ስለሆንክ፡በፊትህ፡ከኃጢአት፡ንጹሕ፡የሆነ፡ የለምና።
፳፪፣ ወለእመኒ ፡ አሐተ ፡ ሰዓተ ፡ ሐይዉ ፡ በዲበ ፡ ምድር ፡ ማኅለፍታተ ፡ ነፍሶሙ ፡ ግዑዘ ፡ ዘእንበለ ፡ ክልኦት ፡ ሀቦሙ ፡ ወዘእንበለ ፡ ሕመሚ፡አንተ፡ጸጉ።	፳፪፣ በዚህ ፡ ዓለምስ ፡ እንኳን ፡ አንዲት ፡ ሰዓት ፡ ቢኖሩ ፡ የነፍሳቸውን ፡ መንገድ ፡ ያለ ፡ መከልከልና ፡ ያለ ፡ ምቀኝነት ፡ አቅንተህ ፡ ስጥ።
፳፫፣ መንፈሰ ፡ ናዛዜ ፡ ወመናህየ ፡ ለሰብ አሙ፡ፈኑ።	፳፫፣ የሚያረጋጋና ፡ የሚያሳርፍ ፡ መንፈስን ፡ ለቤተ፡ሰዎቻቸው፡ላክ።
፳፬፣ ናዝዞሙ፡ወአስተፍሥሖሙ፡በክርስቶስ።	፳፬፣ አረጋግተህም ፡ ደስ ፡ አሰኛቸው ፡ በክርስቶስ ፡

Scanned by CamScanner

ዘዕለተ፡ሰሚዕና።	የሰሚዕና፡ዕለት።
ዘቡቱ ፡ ለከ ፡ ምስሌሁ ፡ ወምስለ ፡ ቅዱስ ፡ መንፈስ፡ ስብሐት ፡ ወእኒገ ፡ ይእዜኒ ፡ ወዘልፈኒ፡ወለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።	በርሱ፡ያለ፡ክብር፡ጽንዕ፡ለአንተም፡ይገባል፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ከመንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ ጋራ፡ ዛሬም፡ዘወትርም፡ለዘላለሙ፡አሜን።
(ይካ) ፡ ሰላመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ወፍቅረ ፡ እግዝእትነ ፡ ቅድስት ፡ ድንግል ፡ በክልኤ ፡ ማርያም ፡ ወላዲተ ፡ አምላክ፡ ወሞገሰ ፡ መስቀሉ ፡ ለእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ኢይርነቅ ፡ እማእ ከሌየ ፡ ወእማእከሌክሙ ፡ እስከ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም።	ካህኑ ፡ የአብ ፡ የወልድ ፡ የመንፈስ ፡ ቅዱስ፡ ፍቅር ፡ አንድነት ፡ በሁለት ፡ ወገን ፡ ድንግል፡ የሆነች፡የእመቤታችን፡አምላክን፡የወለደች፡ የቅድስት ፡ ማርያም ፡ ፍቅር ፡ የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ የመስቀሉ ፡ ግርማ ፡ ከእኔና ፡ ከእናንተ ፡ መካከል ፡ ለዘላለሙ ፡ አይራቅ፡ይበል፡
(ይሕ)፡አሜን።	(ሕዝቡ)፡አሜን፡ይበሉ።
(ይካ)፡እግዚአ፡መሐረነ፡ክርስቶስ።	(ካህኑ) ፡ አቤቱ ፡ ክርስቶስ ፡ ማረን ፡ ይበል ።
ሕዝብኒ ፡ ይሰጠዉ ፡ ዘንተ ፡ እስከ ፡ ይፈጽሙ ፡ አርብዓ፡ወአሐደ፡ጊዜ፡	ሕዝቡም ፡ አርባ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ እስከሚ ፈጽሙ፡ይህን፡ተሰጥዎ፡ይቀበሉ።
(ይዲ) ፡ አትሕቱ ፡ ርእሰክሙ ፡ ለእግዚአ ብሔር፡በፍርሃት።	(ዲያቆኑ) ፡ በፍርሃት ፡ ሁናችሁ ፡ ራሳችሁን ፡ ለእግዚአብሔር፡ዝቅ፡ዝቅ፡አድርጉ፡ይበል
ሕዝብኒ ፡ እለ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ኮሎሙ፡ያድንኑ፡ርእሶሙ።	በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ውስጥ ፡ ያሉት ፡ ሕዝብ፡ ሁሉም፡ራሳቸውን፡ዝቅ፡ዝቅ፡ያድርጉ።
፩፡ (ይካ) ፡ አንተ ፡ ውእቱ ፡ ዘአጽንከ ፡ ሰማያተ ፡ ወወረድከ ፡ ኀቤነ ፡ ወተሰባእከ ፡ በእንተ ፡ ውሉደ፡ሰብእ።	፩፡ (ካህኑ) ፡ አቤቱ ፡ ባሕርይህን ፡ ዝቅ ፡ አድርገህ፡ ከሰማያት ፡ ወደኛ ፡ የወረድህ ፡ ስለ ፡ ሰው ፡ ልጆችም፡ሰው፡የሆንኸ፡አንተ፡ነህ።
፪፡ አንተ ፡ ውእቱ ፡ ዘትነብር ፡ ዲበ ፡ ኪሩቤል ፡ ወሱራፌል፡ወትሬኢ ፡ትሕታኑ።	፪፡ በኪሩቤልና ፡ በሱራፌል ፡ ላይ ፡ ተቀምጠህ፡ ትሑታኑን፡ የምትመለከት ፡ የምትጠብቅ ፡ አንተ፡ነህ፡ይበል።
፫፡ ወይእዜኒ ፡ እግዚአ ፡ እስመ ፡ ናሴዕል ፡ አዕይንተ፡ አልባቢነ ፡ ኀቤከ ፡ ስረይ ፡ ለነ ፡ ኃጣውኢነ ፡ ወአድኅን ፡ ነፍሳተነ ፡ እሙስና።	፫፡ አሁንም ፡ አቤቱ ፡ ውስጣዊ ፡ ዓይናችንን ፡ ወደአንተ፡እናንጋጥጣለንና ፡ኃጢአታችንን፡ አስተሰርይልን ፡ ነፍሳችንንም ፡ ከጥፋት ፡ አድን።
፬፡ ንሰግድ ፡ ለኂሩትከ ፡ ማሕየዊት ፡ ወናስተ በቍዕ፡ኀቤከ ፡ከመ ፡ተሀበነ ፡ሰላመ ፡እስመ ፡ ኮሎ፡ወሀብከነ።	፬፡ አዳኝ ፡ ለሆነች ፡ ቸርነትህ ፡ እንሰግዳለን ፡ ሁሉን፡ ሰጥተህናልና ፡ ፍቅር ፡ አንድነትን ፡ ትሰጠን፡ዘንድ፡ወዳንተ፡እንማልዳለን።
፭፡ ወኢንአምር ፡ ባዕደ ፡ አምላክ ፡ ዘእንበለ ፡ ስምከ፡ቅዱስ።	፭፡ ከቅዱስ ፡ ስምህ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ አምላክ ፡ አናውቅም።
፮፡ ሚጠነ ፡ እግዚአ ፡ ኀበ ፡ ፍኖትከ ፡ ቅዱስ ፡ ወአእምሮ፡ዚአከ።	፮፡ አቤቱ ፡ ወደ ፡ ሕግህና ፡ አንተን ፡ ወደማወቅ ፡ መልሰን።
፯፡ ርድአነ ፡ንትቀነይ ፡ለከ ፡ በጽላሎተ ፡ክነፈከ ፡ ከድነነ ፡ ምስለ ፡ ኮሎሙ ፡ ቅዱሳኒከ ፡ እለ ፡ ተወከሉ፡ብከ።	፯፡ እናገለግልህ ፡ዘንድ ፡ርዳን ። ከሚታመኑብህ፡ ቅዱሳንህ ፡ ሁሉ ፡ ጋራ ፡ በክንፈ ፡ ረድኤትህ ፡ ሠውረን።
፰፡ ወእለ ፡ አትሕቱ ፡ እንከ ፡ አርእስቲሆሙ ፡ ቅድሜከ፡አልዕሎሙ፡በምሕረትከ።	፰፡ በፈትህም ፡ ራሳቸውን ፡ ዝቅ ፡ ዝቅ ፡ ያደረጉትን፡በቸርነትህ፡ከፍ፡ከፍ፡አድርጋቸው።
፱፡ ወአሠርግዎሙ ፡ በመናያቲከ ፡ ይረሱ ፡ መንግሥተ፡ሰማያት፡በሥምረቱ ለአቡከ፡	፱፡ የክብር ፡ ባለቤት ፡ በሆነ ፡ በአባትህ ፡ ፈቃድ፡ በክብር፡ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ለዘላለሙ ፡ ትክክል፡

Scanned by CamScanner

ዘዕለተ፡ሰሚዕና።	የሰሚዕና፡ዕለት።
ዘለሙ፡ ፡ ስብሐት ፡ ወበሥምረቱ ፡ ለመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ማሕየዊ ፡ ዘዕሩይ ፡ በአኰቴት ፡ ምስሌክ ፡ እስከ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም፡አሜን።	በሚሆን ፡ አዳኝ ፡ ሕይወት ፡ በሚሆን ፡ በመንፈስ፡ቅዱስም፡ ፈቃድ፡ሰማያዊ፡መንግሥትን ፡ ይወርሱ ፡ ዘንድ ፡ በምግባር ፡ በሃይማኖት፡አስጊጣቸው፡አሜን።
(ይዲ) ፡ ስግዱ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በፍርሐት።	(ዲያቆኑ) ፡ በፍርሐት ፡ ሁናችሁ ፡ ለእግዚአብሔር፡ስገዱ፡ይበል።
(ይሕ) ፡ ቅድሜክ ፡ እግዚኦ ፡ ንሰግድ ፡ ወንሴብሐክ።	(ሕዝቡ) ፡አቤቱ ፡ በፊትህ ፡ወድቀን ፡እናመሰግንሃለን ፡ይበሉ።
(ይካ) ፡ ቡሩክ ፡ ዘይመጽእ ፡ በስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሰሚዕና ፡ በአርያም ፡ ዝንቱ ፡ ውእቱ ፡ ንጉሥ ፡ እስራኤል ፡ ሰሚዕና ፡ በአርያም ፡ ለወልደ፡ዳዊት።	(ካህኑ) ፡በአርያም ፡ያለ ፡መድኃኒት ፡በእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ የሚመጣ ፡ የተባረከ ፡ ነው ፡ የእሥራኤል ፡ንጉሥ ፡ይህ ፡ነው። ለዳዊት ፡ልጅ ፡ በአርያም ፡ መድኃኒት ፡ መባል ፡ ይገባዋል ፡ ይበል።
፩፤ አ ፡ እግዚአብሔር ፡ እግዚአ ፡ መና ፍስት ፡ ወለኵሉ ፡ ዘሥጋ ፡ ዘኬድኮ ፡ ለሞት ፡ ወረገምኮ ፡ ለዲያብሎስ ፡ ሀባ ፡ እግዚአ ፡ ሕይወተ ፡ ዘለዓለም፡ ወአእርፋ ፡ ለነፍሰ ፡ ክርስቲያን ፡ በመካን ፡ ዘአልቦ ፡ ጸማ ፡ ወአልቦ ፡ ሐዘን።	፩፤ የረቂቃን ፡ መላእክት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሆይ ፡ ሥጋ ፡ ለለበሰውም ፡ ሁሉ ፡ ፈጣሪ ፡ ሞትን ፡ የረገጥከው ፡ ዲያብሎስን ፡ ረግመህ ፡ ያጠፋህ ፡ የክርስቲያንን ፡ ነፍስ ፡ የዘላለም ፡ ሕይወትን ፡ ሰጥተህ ፡ ድካምና ሐዘን ፡ በሌለበት ፡ ቦታ ፡ አሳርፋት።
፪፤ ለእመ ፡ አበሰት ፡ እግዚኦ ፡ እመሂ ፡ በቃላ ፡ ወእመሂ ፡ በምግባራ ፡ ወእመሂ ፡ በኀሊናሃ ፡ ጎድግ ፡ ላቲ ፡ እስመ ፡ ኄር ፡ አንተ ፡ ወመፍቀሬ ፡ ሰብእ።	፪፤ በቃልዋም ፡ በሥራዋም ፡ ቢሆን ፡ በሃሳቧም ፡ ቢሆን ፡ አቤቱ ፡ አንተን ፡ ብትበድል ፡ አንተ ፡ ቸር ፡ ሰውን ፡ ወዳጅ ፡ ነህና ፡ ይቅር ፡ በላት።
፫፤ አ ፡ እግዚኦ ፡ ሰንኮሪሶን ፡ እስመ ፡ አልቦ ፡ ሰብእ ፡ ዘእንበለ ፡ ኃጢአት ፡ አንተ ፡ ባሕቲትከ ፡ ዘአልብከ ፡ ኃጢአት።	፫፤ አቤቱ ፡ መሐሪ ፡ አምላክ ፡ ሆይ ፡ ሰው ፡ ሁኖ ፡ ያለ ፡ ኃጢአት ፡ የሚኖር ፡ የለምና ፡ ኃጢአት ፡ የሌለብህ ፡ ንጹሐ ፡ ባሕርይ ፡ አንተ ፡ ብቻ ፡ ነህ።
፬፤ ወጽድቅ ፡ ስምዕከ ፡ እስከ ፡ ለዓለም ፡ ወሥርዓትከ ፡ እሙን ፡ ውእቱ።	፬፤ ምስክርነትህ ፡ ለዘላለም ፡ እውነት ፡ ነው ፡ ሕግህም ፡ የታመነ ፡ ነው።
፭፤ እስመ ፡ አንተ ፡ ሕያው ፡ ዘታዐርፎሙ ፡ ለእለ ፡ ኖሙ ፡ አግብርቲከ።	፭፤ በሞት ፡ ያንቀላፉትን ፡ ባለሟሎችህን ፡ ዕረፍተ ፡ ነፍስ ፡ ሰጥተህ ፡ የምታሳርፋቸው ፡ አንተ ፡ ሕያው ፡ ባሕርይ ፡ ነህና።
፮ አ ፡ እግዚኦ ፡ ክርስቶስ ፡ አምላክነ ፡ ወለከ ፡ ናቄርብ ፡ ስብሐተ ፡ ወለአቡከ ፡ ኄር ፡ ሰማያዊ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ማሕየዊ።	፮፤ አቤቱ ፡ አምላካችን ፡ ክርስቶስ ፡ ሆይ ፡ ለአንተ ፡ ቸር ፡ ሰማያዊ ፡ አባትህ ፡ አዳኝ ፡ ሕይወትም ፡ ለሚሆን ፡ ለመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ክብር ፡ ምስጋና ፡ እናቀርባለን።
ይእዜኒ ፡ ወዘልፈኒ ፡ ወለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን።	ዛሬም ፡ ዘወትርም ፡ ለዘላለሙ ፡ አሜን።
ይካ ፡ እግዚኦ ፡ መሐረነ ፡ ክርስቶስ ፡ አርብዓ ፡ ወአሐደ ፡ ጊዜ ፡ ኪርያላይሶን ፡ ከማሁ ፡ ፵ወ፩ደ ፡ ጊዜ ። ክርስቶስ ፡ አምላክነ ፡ በስእለታ ፡ ለፍሥሕት ፡ እምከ ፡ አንብራ ፡ እግዚኦ ፡ ለነፍሰ ፡ ክርስቲያን ፡ ውስተ ፡ ሕፅነ ፡ አብርሃም ፡	ካህኑ ፡ አቤቱ ፡ ይቅር ፡ በለን ፡ አርባ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ኪርያላይሶንም ፡ እንዲሁ ፡ አርባ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ይበል ፡ ሕዝቡም ፡ ይበሉ ። አቤቱ ፡ አምላካችን ፡ ክርስቶስ ፡ የደስታ ፡ መገኛ ፡ በሆነች ፡ እናትህ ፡ የክርስቲያኖችን ፡ ነፍስ ፡ በአብርሃም ፡ በይስሐቅና ፡

Scanned by CamScanner

ዘዕለተ፡ሆሣዕና።	የሆሣዕና፡ዕለት።
ወኢትትሀከይ ፡ አቅልሎ ፡ ክበደ ፡ አበ ሳሃ ፡ አ ፡ ጸዋሪ ፡ ኢትትሀየይ ፡ ተግባረ ፡ እደዊከ።	አስወግድ፡የበደሏንም፡ክብደት፡ለማቃለል፡ ቸል ፡ አትበል ። ሁሉን ፡ የምትሸከም ፡ ሆይ ፡ የእጅህን፡ሥራ፡ቸል፡አትበል።
፩፡ አ ፡ ፈጣሪ ፡ ኢትትኀሠሥ ፡ አበሳ ፡ አመትከ ፡ አ ፡ ገባሪ ፡ አ ፡ እግዚአ ፡ ትኩን ፡ ፍትሕተ ፡ ወግዕዝተ፡ነፍሰ፡ክርስቲያን፡በአፈ፡ዚአከ።	፩፡ ፈጣሪ፡ሆይ፡ያባሪያህን፡በደል፡አትመራመር፡ አቤቱ፡ፈጣሪ፡ሆይ፡የክርስቲያን፡ነፍስ፡በአንደ በትህ፡ቃል፡የተረታች፡ነጻ፡የወጣች፡ትሁን።
፪፡ አ ፡ አብ ፡ ኄር ፡ ሰማያዊ ፡ ወበአፈ ፡ ወልድከ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ቃል ፡ ቀዳማዊ ፡ በርደቱ ፡ ወበምጽአቱ ፡ ለወልድከ ፡ በጥምቀቱ ፡ ወበስብከቱ ፡ ለፍቁርከ ፡ በሕማሙ ፡ ወበስቅለቱ ፡ ለበኵርከ ፡ በትንሣኤሁ ፡ ወበዕርገቱ ፡ ለዋህድከ፡ ወበነቢሮቱ ፡ በየማንከ ፡ በፀአቱ ፡ ወበበአቱ ፡ ኀበ ፡ ህላዌከ ፡ እንዘ ፡ ኢይትበተክ ፡ እም ትካት ፡ እምኔከ ፡ በዳግም ፡ ምጽአቱ ፡ ምስለ፡ኵለሙ፡ኀይላተ፡ሰማይ።	፪፡ ሰማያዊ ፡ ቸር ፡ አባት ፡ ሆይ ፡ አስቀድሞ ፡ በነበረ፡ አካላዊ ፡ ቃል ፡ ልጅህ ፡ በሆነ ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ፡ አፍ ፡ በልጅህ ፡ መውረዱና ፡ ሰው ፡ በመሆኑ ፡ በመጠመቁና ፡ በማስተማሩ ፡ በወዳጅህ፡ መከራ ፡ በመቀበሉና ፡ በመሰቀሉ ፡ በበኵርህ ፡ ከሙታን ፡ ተለይቶ ፡ በመነሣቱና ፡ በማረጉ፡በአንድ፡ልጅህ፡ በቀኝህ፡በ መቀመጡ፡ አስቀድሞ ፡ ካንተ ፡ ሳይለይ ፡ በመውጣቱና ፡ ወዳንተ ፡ ሕልውና ፡ በመግባቱ ፡ ዳግመኛም ፡ ከሰማይ፡ሠራዊት፡ሁሉ፡ጋራ፡በመምጣቱ።
፫፡ በሥጋሁ ፡ ወበደሙ ፡ ዘቅድስት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እንተ ፡ ረሰያ ፡ ማኅደረ ፡ ስሙ ፡ ወአጥረያ፡ በደሙ ፡ በቀራንዮ ፡ መካነ ፡ መስቀሉ ፡ ወበኅልኀታ ፡ መቃብሩ ፡ ወበኢየሩሳሌም ፡ ሀገሩ ፡ በደብረ ፡ ዘይት ፡ ማኅደሩ ፡ ወበደብረ ፡ ታቦር ፡ መካነ ፡ ምሥጢሩ ፡ ወበደብረ ፡ ሲና ፡ ምሥዋሩ ፡ ወኢየሩሳሌም ፡ እንተ ፡ ላዕሉ ፡ አእጋረ ፡ አንስርት ፡ በጸሐታ ፡ ኢይክሉ።	፫፡ በሥጋውና ፡ በደሙ ፡ የስሙ ፡ ማደሪያ ፡ ባደረጋትና በደሙ ፡ በዋጃት ፡ በክብርት ፡ ቤተክርስቲያን ፡ በመስቀሉ ፡ ቦታ ፡ በቀራንዮ ፡ በመቃብሩ፡በኅልኀታ፡በሀገሩ፡በኢየሩሳሌም፡ በማደሪያው ፡ በደብረ ፡ ዘይት ፡ የጌትነቱን ፡ ምሥጢር ፡ በገለጠበት ፡ በደብረ ፡ ታቦር ፡ በመሠወሪያው ፡ በደብረ ፡ ሲና ፡ አንስርት ፡ ሊደርሱባት፡ የማይችሉ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ሰማያዊት።
፬፡ አቡቱ ፡ ትኩን ፡ ፍትሕተ ፡ ወግዕዝተ ፡ ነፍሰ ፡ ክርስቲያን ፡ እማእሰረ ፡ ኃጢአት ፡ በአፉሃ ፡ ለእግዝእትነ ፡ ማርያም ፡ መንፈሳዊት ፡ ሐዳስ ፡ ምእናም ፡ ወበእንተ ፡ ስእለታ ፡ ግሩም ፡ ወበአፈ ፡ ዚአየ ፡ አነ ፡ ገብርከ ፡ ኀጥእ ፡ ወድኩም።	፬፡ አቤቱ ፡ የክርስቲያንን ፡ ነፍስ ፡ ኃጢአቷን ፡ አስተስርይላት ። በማወቅ ፡ ወይም ፡ ባለመዋቅ ፡ የሠራችውን ፡ በሥራዋም ፡ ቢሆን ፡ በሐሳብም ፡ ቢሆን ፡ በፈቃዷም ፡ ቢሆን ፡ በመገደድም ፡ ቢሆን ፡ በመድከምም ፡ ቢሆን ፡ ወይም ፡ በግፊት ፡ በግልጽም ፡ ቢሆን ፡ ወይም ፡ በመሠወር ፡ ብትሠራ።
፭፡ አምላክነ ፡ ሆይ ፡ የክርስቲያን ፡ ነፍስ ፡ ከኃጢአት ፡ ማሰሪያ ፡ የተፈታች ፡ ነጻ ፡ የወጣች ፡ ትሁን ፤ አዲስ ፡ መሣሪያ ፡ በምትሆን ፡ በእመቤታችን ፡ በማርያም ፡ አፍ ፡ ግሩም ፡ በሆነ ፡ ልመናዋም ፡ ኀጥእ ፡ ደኅማ ፡ በምሆን ፡ በእኔም ፡ በባሪያህ ፡ ቃል ፡ የተፈታች ፡ ነጻ ፡ የወጣች ፡ ትሁን።	፭፡ አምላካችን ፡ ሆይ ፡ የክርስቲያን ፡ ነፍስ ፡ ከኃጢአት ፡ ማሰሪያ ፡ የተፈታች ፡ ነጻ ፡ የወጣች ፡ ትሁን ፤ አዲስ ፡ መሣሪያ ፡ በምትሆን ፡ በእመቤታችን ፡ በማርያም ፡ አፍ ፡ ግሩም ፡ በሆነ ፡ ልመናዋም ፡ ኀጥእ ፡ ደኅማ ፡ በምሆን ፡ በእኔም ፡ በባሪያህ ፡ ቃል ፡ የተፈታች ፡ ነጻ ፡ የወጣች ፡ ትሁን።

Scanned by CamScanner

ዘዕለተ፡ሰሚዕና።	የሰሚዕና፡ዕለት።
ይስሐቅ፡ወያዕቆብ። ወለነኒ፡ደምር፡ነፍሰነ፡ወተማሃለነ፡በኵሉ፡ጊዜ። ይእዜኒ፡ወዘልፈኒ፡ወለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።	በያዕቆብ፡ዕቅፍ፡አኑራት። እኛንም፡አንድ፡አድርገን፡በየጊዜው፡ሁሉ፡ይቅር፡በለን። ዛሬም፡ዘወትርም፡ለዘላለሙ፡አሜን።
ጸሎተ፡ንስሓ፡ዓቢይ።	ታላቅ፡የንስሐ፡ጸሎት።
፩፡ እግዚእ፡እግዚኦ፡እግዚአብሔር፡አኀዜ፡ኵሉ፡ብሑተ፡ሥልጣን፡ወስም፡ቀዳማዊ፡ዘእንበለ፡ጥንት፡ወደኅራዊ፡ዘእንበለ፡ተፍጻሜት፡ዘትነብር፡ውስተ፡አርያም፡ወመንበረ፡ስብሐቲከ፡ዘኢይተረፍም፡ዘልብሰትከ፡አፍሐም፡ወመንጦላዕትከ፡እሳት፡ግሩም።	፩፡ አቤቱ፡ሁሉን፡የያዝኸ፡ጌታ፡እግዚአብሔር፡በሥልጣን፡በስም፡ብቸኛ፡የምትሆን፡ጥንት፡የሌለህ፡ቀዳማዊ፡ፍጻሜ፡የሌለህ፡ዘላለማዊ፡በአርያም፡የምትኖር፡የክብርህ፡የጌትነትህ፡ዙፋን፡የማይመረመር፡ልብስህ፡የእሳት፡ፍም፡መጋረጃህም፡ግሩም፡የሆነ፡እሳት።
፪፡ ዘፈታሕከ፡ኵሎ፡ማእሰረ፡ኃጣውኢነ፡በሕማሙ፡ለወልድከ፡ለአርዳኢሁ፡ዘይቤሎሙ፡በቃሉ፡ዘመንክር፡ጣዕሙ፡ለእለ፡ጎደግሙ፡ኃጢአት፡ይትጎደግ፡ሎሙ፡ወለእለ፡ኢጎደግሙ፡ኃጢአት፡ኢይትጎደግ፡ሎሙ።	፪፡ የኃጢአታችንን፡ማሰሪያ፡ሁሉ፡በልጅህ፡ሕማም፡የፈታሕ፡ጣዕሙ፡ድንቅ፡በሆነ፡ቃሉ፡ለደቀ፡መዛሙርቱ፡ይቅር፡ያላችኋቸው፡ኃጢአታቸው፡ይቀርላቸዋል፡ይቅርም፡ያላላችኋቸው፡ኃጢአታቸው፡አይቀርላቸውም፡ያላቸው።
፫፡ በእንተ፡ዝንቱ፡ንስእል፡ወናስተበቍዕ፡ወናን ቀዓዱ፡ኀቤከ፡በእንተ፡ነፍሰ፡ክርስቲያን፡አ፡መሐሪ፡ወመፍቀሬ፡ሰብእ። ወበእንተ፡ኵሎሙ፡አበዊነ፡ወአኃዊነ፡እለ፡ኖሙ፡ወፈለሱ፡እምዝንቱ፡ዓለም፡ኀላፊ፡ዘይበሊ፡ወይማስን።	፫፡ መሐሪ፡ይቅር፡ባይ፡ሰውን፡የምትወድ፡ሆይ፡ስለዚህ፡ስለ፡ክርስቲያን፡ነፍስ፡ወዳንተ፡በማንጋጠጥ፡እንለምናለን፡እንማልዳለንም። ከዚህ፡ከኀላፊውና፡ከሚጠፋው፡ዓለም፡በሞት፡ስለተሰደዱ፡አባቶቻችንና፡ወንድሞቻችን፡እንለምንሃለን፡እንማልድሃለን።
፬፡ ወበእንተ፡ካህናት፡እለ፡ይሴብሑከ፡በዜማ፡ጥዑም፡ከመ፡ቃለ፡አርጋኖን፡አንዛሪ፡ወተናጋሪ።	፬፡ ሲመቱት፡ድምፅ፡እንደሚሰጥ፡እንደ፡እንዚራ፡እንደ፡በገና፡ጣዕም፡ባለው፡ዜማ፡ስለሚአመሰግኑህ፡ካህናት።
፭፡ ወበእንተ፡ኵሎሙ፡ቅዱሳን፡ዲያቆናት፡እለ፡ተልእኩ፡ወተቀንዩ፡ለከ፡ወአቅለሉ፡ክነፊሆሙ፡ከመ፡ንስር፡ሰራሪ።	፭፡ ስለሚላኩና፡ስለሚያገለግሉህ፡እንደሚበር፡ንስር፡ለተልእኮ፡ስለሚፋጠኑ፡ቅዱሳን፡ዲያቆናት፡እንማልዳለን።
፮፡ ወበእንተ፡ኵሎሙ፡ሕዝብ፡ዕድ፡ወአንስት፡አእሩግ፡ወሕፃናት፡እለ፡ቆሙ፡ውስተ፡ቤተ፡ክርስቲያንከ፡ቅድስት፡ወምሥዋዒከ፡ኀጣውኦ፡ዘያስተሰሪ።	፮፡ ኃጢአትን፡በሚአስተሰርይ፡በመሠዊያህ፡ፊት፡ስለ፡ቆሙ፡ስለ፡ሕፃናቱና፡ስለ፡ሽማግሎቹ፡ስለ፡ወንዶችና፡ሴቶች፡ስለ፡ሕዝቡ፡ሁሉ፡እንማልዳለን።
፯፡ አ፡እግዚእ፡ፍትሐ፡ወአግዕዛ፡እምኵሉ፡ኃጣውኢሃ፡ዘአሥገራ፡አሥጋሪ።	፯፡ አቤቱ፡ጥማጅ፡ያጠመዳትን፡የክርስቲያን፡ነፍስ፡ከኃጢአት፡ሁሉ፡የተፈታች፡ነጻ፡የወጣች፡አድርጋት።
፰፡ ወብትከ፡እምኔሃ፡ማእሰረ፡ዘእስተዳለወ፡አሳሪ። ወአሰስል፡እምኔሃ፡መናሥግተ።	፰፡ አሳሪ፡ዲያብሎስ፡ያዘጋጀውንም፡ማሰሪያ፡ከእርስዋ፡ቁረጥ። ከእርሷም፡የኃጢአትን፡መቄለፊያ፡አስወግድ።
፱፡ አ፡ከሀሊ፡አሰስል፡ሕምዘ፡ዘከዐወ፡ቀታሊ፡	፱፡ ከሀሊ፡ሆይ፡ጠላት፡የፈሰሰውን፡መርዝ፡

Scanned by CamScanner

ዘዕለተ፡ሆሣዕና።	የሆሣዕና፡ዕለት።
፲፫፡ ወዓዲ፡በእንተ፡አዳም፡አበ፡ኵሉ፡ዓለም፡ በእንተ፡ሴት፡ወኄኖስ፡እለ፡አሥመሩከ፡ እምቅድም፡በእንተ፡ኖኅ፡ወሴም፡ስረይ፡ላቲ፡ ኃጢአታ፡ለአመትከ።	፲፫፡ ዳግመኛም፡ለዓለሙ፡ሁሉ፡አባት፡ስለሆነ፡ አዳም፡ከቀድሞ፡ጀምሮ፡ስለ፡አገለገለህ፡ስለ፡ ሴት፡ስለኄኖስ፡ስለ፡ኖኅና፡ስለ፡ሴም፡የባሪ ያህን፡ነፍስ፡ኀጢአቷን፡አስተስርይላት።
፲፬፡ አ፡ክርስቶስ፡ንጉሠ፡ዓለም፡በኵረ፡አብ፡ ወበኵረ፡ድንግል፡አናሕሲ፡አበሳሃ፡ ዘገብረት፡እስከ፡ዮም።	፲፬፡ የዓለም፡ንጉሥ፡ክርስቶስ፡ሆይ፡የአብ፡በኵር፡ ልጅ፡የድንግልም፡በኵር፡ልጅ፡እስከ፡ዛሬ፡የሠ ራችውን፡ኃጢአቷን፡በደሏን፡ይቅር፡በላት።
፲፭፡ በእንተ፡መልከ፡ጼዴቅ፡ወኢዮብ፡በእንተ፡ አብርሃም፡ይስሐቅ፡ወያዕቆብ፡በእንተ፡ ሙሴ፡ወአሮን፡በእንተ፡ዳዊት፡ወናታን።	፲፭፡ ስለ፡መልከ፡ጼዴቅና፡ስለ፡ኢዮብ፡ስለ፡ አብርሃም፡ስለ፡ይሥሐቅ፡ስለ፡ያዕቆብ፡ስለ፡ ሙሴና፡አሮን፡ስለ፡ዳዊትና፡ስለ፡ናታን።
፲፮፡ በእንተ፡ኤልያስ፡ቀናኢ፡ወኤልሳዕ፡ትእዛዘ፡ ሊቁ፡ሰማዒ፡ሥረይ፡ላቲ፡ኃጢአታ፡ ለአመትከ።	፲፮፡ ለአምልኮትህ፡ቀናተኛ፡ስለሆነ፡ስለ፡ኤልያስ፡ የመምህሩን፡ትእዛዝ፡ስለሚሰማ፡ስለ፡ ኤልሳዕ፡የባሪያህን፡ኀጢአቷን፡ይቅር፡በላት።
፲፱፡ አ፡ክርስቶስ፡በቋዒ፡በሥጋከ፡ወበደምከ፡ ቍስለ፡ዚአሃ፡አጥዒ፡ሣህለከ፡ወምሕረተከ፡ አርኢ።	፲፱፡ የምትጠቅም፡ክርስቶስ፡ሆይ፡በሥጋህና፡ በደምህ፡የኃጢአቷን፡ቍስል፡አድን፡ይቅር ታህንና፡ምሕረትህንም፡ግለጽ።
፳፡ በእንተ፡ኢሳይያስ፡ዘተመጠወ፡ቍርባነ፡ በእደ፡ሱራፌ፡ወዕዝራ፡ጸሐፊ።	፳፡ በሱራፌ፡እጅ፡ቍርባንን፡ስለተቀበለ፡ስለ፡ ኢሳይያስ፡ስለ፡ጸሐፊው፡ስለ፡ዕዝራ።
፳፩፡ በእንተ፡ኤርምያስ፡ዘሠናይ፡ራእዩ፡ወዘካ ርያስ፡ወልደ፡በራክዩ፡በእንተ፡ሕዝቅኤል፡ ዘአንሥአ፡አዕፅምተ፡እምድኅረ፡የብሳ፡ ወበእንተ፡ዕንባቆም፡ዘርእዮ፡ለወልድ፡ ማዕከለ፡ክልኤ፡እንስሳ፡ስረይ፡ላቲ፡ለነፍሰ፡ ክርስቲያን።	፳፩፡ ራእዩ፡መልካም፡ስለሆነ፡ስለ፡ኤርምያስና፡ ስለ፡በራክዩ፡ልጅ፡ዘካርያስ፡የደረቁ፡ ዓፅሞችን፡ሥጋ፡አልብሶ፡ስለ፡አስነሣ፡ስለ፡ ሕዝቅኤል፡በሁለት፡እንስሶች፡መካከል፡ ወልድን፡ስለ፡አየው፡ስለ፡ዕንባቆም፡ይቅር፡ በላት።
፳፪፡ አ፡ክርስቶስ፡ወልደ፡አንበሳ፡ዘትሜግብ፡ ሰብአ፡ወእንስሳ፡አናሕሲ፡ዘአመትከ፡ ኃጢአተ፡ወአበሳ።	፳፪፡ የአንበሳ፡ልጅ፡ክርስቶስ፡ሆይ፡ሰውና፡ እንስሳን፡የምትመግብ፡የባሪያህን፡ኃጢአቷን፡ አስተስርይላት፡በደልዋን፡አቃልላት።
፳፫፡ በእንተ፡ዐሠርቱ፡ወንጌላት፡ነቢያት፡ ላእካን፡ወዐሠርቱ፡ወክልኤቱ፡ሐዋርያት፡ ፍንዋን። በእንተ፡ዮሐንስ፡መጥምቅ፡ጸያሔ፡ ፍኖት፡ወእስጢፋኖስ፡ሊቀ፡ዲያቆናት፡ ወቀዳሜ፡ሰማዕት።	፳፫፡ አገልጋዮች፡ስለሚሆኑ፡ስለ፡አሥራ፡አምስቱ፡ ነቢያትና፡ለስብከት፡ስለ፡ተላኩ፡ስለዐሥራ፡ ሁለቱ፡ሐዋርያት፡ስለ፡መንገድ፡ጠራጊው፡ስለ፡ መጥምቁ፡ዮሐንስና፡የሰማዕታት፡መጀመሪያና፡ የዲያቆናት፡አለቃ፡ስለሆነው፡ስለእስጢፋኖስ።
፳፬፡ ወበአፈ፡ሰብዓ፡ወክልኤቱ፡አርድእት፡ ቅዱሳን፡ወበአፈ፡ኀምስቱ፡ምእት፡ቢጽ፡ ሥረይ፡ላቲ፡ለነፍሰ፡ክርስቲያን።	፳፬፡ በክበሩ፡በሰብዓ፡ሁለቱ፡አርድእት፡ቃል፡ በአምስት፡መቶ፡ወንድሞች፡ቃል፡የክርስቲ ያንን፡ነፍስ፡ኃጢአቷን፡አስተስርይላት።
፳፭፡ አ፡ቅዱስ፡አቡሁ፡ለእግዚእነ፡ኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ጎዕብ፡ርስሐታ፡በዝንቱ፡ማይ፡	፳፭፡ የጊታችን፡የኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ቅዱስ፡አባት፡ ሆይ፡ስሙ፡ናሎስ፡የሚባል፡ተከዜ፡በሚባል

Scanned by CamScanner

ዘስሙ ፡ ናሎስ ፡ ተከዚ ፡ ማየ ፡ ዮርዳኖስ ፡ ወአንጽሓ፡እምኵሉ፡ደነስ፡ወርኵስ።

፹፮፡ ወአድኅና፡እምኵሉ፡አበሳ፡ወሐሲ፡ወልደኪ፡ አመ ፡ ገጸ ፡ ይመይጥ ፡ ከመ ፡ ኢትትረከብ ፡ በኀሢሥ፡ወአሠርግዋ፡በመንፈስ፡ቅዱስ።

፹፯፡ በአፈ፡ሠለስቱ፡ምእት፡ዐሠርቱ፡ወሰመንቱ፡ ርቱዓን ፡ ሃይማኖት ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ እለ ፡ ተጋብኡ፡በኒቅያ፡ወበአፈ፡ምእት፡ውኅምሳ፡ እለ፡በቍስጥንጥንያ።

ወበአፈ፡ክልኤቱ፡ምእት፡እለ፡በኤፌሶን።

፹፰፡ ወበእንተ ፡ ነሊሙ ፡ ማኅበረ ፡ በዙር ፡ ቅዱሳን።

፹፱፡ አ ፡ ክርስቶስ ፡ ጸወን ፡ ዘትሰውቆሙ ፡ ለትን ቱናን፡ ወታኅሥአሙ ፡ ለምውታን ፡ ዘእን ግእኮ፡ ለወልደ ፡ መበለት ፡ በሀገረ ፡ ናይን ፡ ከማሁ ፡ አንሥአ ፡ ለንፍሰ ፡ ነሊሙ ፡ ክርስ ቲያን፡በዕለተ፡ደይን።

፺፡ በአፈ ፡ ጴጥሮስ ፡ ሊቀ ፡ ሐዋርያት ፡ ወበአፈ ፡ ጴጥሮስ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ወተፍጻሜተ ፡ ሰማዕት።

፺፩፡ በአፈ ፡ ጎርጎርዮስ ፡ ወባስልዮስ ፡ በአፈ ፡ አትና ቴዎስ ፡ ወቴዎፍሎስ ፡ በአፈ ፡ ቄርሎስ ፡ ወሳዊሮስ ፡ በአፈ ፡ ዮሐንስ ፡ ልሳነ ፡ ወርቅ ፡ ወዲዮስቆሮስ ፡ ቀናኢ ፡ ለጽድቅ ፡ ስሪይ ፡ ላቲ ፡ ለነፍሰ ፡ ክርስቲያን።

፺፪፡ አ ፡ ክርስቶስ ፡ ሊቅ ፡ ዘትሰውቆ ፡ ለጥውቅ ፡ ወታኅሥአ ፡ ለውዱቅ ፡ ናስተበ ቍዓክ ፡ በጽሒቅ ፡ ከመ ፡ ታድኅና ፡ እምሲኦል ፡ ዕሙቅ።

፺፫፡ በእንተ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ኮከበ ፡ ክብር ፡ ብሩህ ፡ ወመርቆሬዎስ ፡ ዘተአምሪሁ ፡ ብዙኀ ፡ በጸሎተ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ዘአጕየየ ፡ ረሲ አነ ፡ ሥዕሉ ፡ ሶበ ፡ ይጸርሕ ፡ ወገላው ዴዎስ ፡ ድንግል ፡ ወንጹሕ ፡ ስረይ ፡ ላቲ ፡ ለነፍሰ፡ክርስቲያን።

፺፬፡ አ ፡ ክርስቶስ ፡ መሲሕ ፡ እመኒ ፡ ኀጢአታ ፡ ብዙኀ ፡ ከመ ፡ ለይ ፡ ዘያቅየሐይሕ ፡ አጸዕድዋ ፡ ከመ ፡ በረድ ፡ ወከመ ፡ ዕምር ፡ ንጹሕ ፡ ወአሠ ርግዋ ፡ በልብሰ ፡ መርዓ ፡ ብሩህ።

፺፭፡ በእንተ ፡ ሚናስ ፡ ዘሰማይ ፡ ሐራ ፡ ወፈቅጦር ፡ ወልደ ፡ ማርታ ፡ ለጥበብ ፡ ማኅደራ ፡ ስረይ ፡ ላቲ ፡

በዚህ ፡ በዮርዳኖስ ፡ ውኃ ፡ አምላል ፡ በሆነው ፡ አንጻት።

፹፯፡ ከበደልና ፡ ከነቀፋም ፡ አድናት ፡ ልጅህ ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ በመመርመር ፡ በደለኛ ፡ ሁና ፡ እንዳትገኝ፡በመንፈስ፡ቅዱስ፡አስጊጣት።

፹፰፡ በኒቅያ ፡ በተሰበሰቡ ፡ ሃይማኖታቸው ፡ የቀና ፡ ስለ ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ዐሥራ ፡ ስምንት ፡ ጳጳሳት ፡ ቃል ፡ በቍስጥንጥንያም ፡ በተሰበሰቡ ፡ በመቶ ፡ ኀምሣው ፡ ጳጳሳት ፡ ቃል ፡ በኤፌሶን ፡ በተሰበሰቡ ፡ በሁለት ፡ መቶ ፡ ጳጳሳት ፡ ቃል።

፹፱፡ ቅዱሳን ፡ ስለሚሆኑ ፡ ማኅበረ ፡ በዙር ፡ ሁሉ።

፺፡ አምባ ፡ መጠጊያ ፡ ክርስቶስ ፡ ሆይ ፡ የተፍገመገ ሙትን ፡ የምትደግፋቸው ፡ ሙታንን ፡ የምታስ ነሣቸው ፡ በሀገረ ፡ ናይን ፡ የመበለቲቱን ፡ ልጅ ፡ ያስነሣህ ፡ እንዲሁ ፡ በቀርድ ፡ ቀን ፡ የክርስቲያ ኖችን ፡ ነፍስ ፡ ወደ ፡ ክብር ፡ አስነሣ።

፺፡ በሐዋርያት ፡ አለቃ ፡ በጴጥሮስ ፡ ቃል ፡ የሰማዕ ትነት ፡ መደምደሚያና ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ በሆነውም ፡ በጴጥሮስ ፡ ቃል።

፺፩፡ በጎርጎርዮስና ፡ በባስልዮስ ፡ ቃል ፡ በአትናቴ ዎስና ፡ በቴዎፍሎስ ፡ ቃል ፡ በቄርሎስና ፡ በሳዊሮስ ፡ ቃል ፡ ልሳነ ፡ ወርቅ ፡ በተባለ ፡ ዮሐንስና ፡ ለእውነት ፡ ቀናተኛ ፡ በሚሆን ፡ በዲ ዮስቆሮስ ፡ ቃል ፡ ለክርስቲያን ፡ ነፍስ ፡ ኀጢአቷን ፡ አስተስርይላት።

፺፪፡ የተጨነቀውን ፡ የምትረዳ ፡ የወደቀውንም ፡ የምታነሣ ፡ መምህር ፡ ክርስቶስ ፡ ሆይ ፡ ጥልቅ ፡ ከሆነች ፡ ሲኦል ፡ ታድናት ፡ ዘንድ ፡ በትጋት ፡ እንማልድሃለን።

፺፫፡ የሚአበራ ፡ የክብር ፡ ኮከብ ፡ ስለተባለ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ተአምራቱም ፡ ብዙ ፡ ስለ ፡ ሆነው ፡ መርቆሬዎስ ፡ ሥዕሉ ፡ በጮኸ ፡ ጊዜ ፡ ገዝነዎችን ፡ ስለ ፡ አሳደደ ፡ ስለ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ጸሎት ፡ ንጹሕ ፡ ድንግል ፡ ስለሚሆን ፡ ስለ ፡ ገላውዴዎስ ፡ ጸሎት ፡ የክርስቲ ያንን ፡ ነፍስ ፡ ኀጢአቷን ፡ አስተስርይላት።

፺፬፡ መሲሕ ፡ ክርስቶስ ፡ ሆይ ፡ ኀጢአት ፡ እንደ ፡ ግምጃ ፡ ቅላቱ ፡ የበዛ ፡ ቢሆን ፡ እንደ ፡ በረዶ ፡ አንጻው ፡ እንደ ፡ ንጹሕ ፡ ባዙቶም ፡ አድርገህ ፡ በሙሽርነት ፡ ልብስ ፡ አስጊጣት።

፺፭፡ የሰማይ ፡ ጭፍራ ፡ ስለተባለ ፡ ሚናስ ፡ የጥበብ ፡ ማደሪያ ፡ ስለሆነ ፡ ስለ ፡ ማርታ ፡ ልጅ ፡ ፈቅጦር ፡

Scanned by CamScanner

ዘዕለተ፡ሆሣዕና።	የሆሣዕና፡ዕለት።
ጎጢአታ፡ለነፍሰ፡ክርስቲያን።	ኃጢአቷን፡ይቅር፡በላት።
፴፮፤ አ፡ክርስቶስ፡ለድንግል፡በኵራ፡አድኅና፡እም ዘሲኦል፡ወእምዲያብሎስ፡መከራ፤ በእንተ፡ ቂርቆስ፡ሰማዕት፡ለመንግሥተ፡ሰማይ፡ በደሙ፡ዘተሣየጣ፡ወእሙ፡ኢየሉጣ፤ስረይ፡ ላቲ፡ለነፍሰ፡ክርስቲያን።	፴፮፤ የድንግል፡በኵር፡ክርስቶስ፡ከሲኦልና፡ከዲያ ብሎስ፡መከራ፡የክርስቲያንን፡ነፍስ፡ አድኅና፤ ኃጢአቷንም፡አስተስርይላት፡ መንግሥተ፡ሰማይን፡በደሙ፡ስለዋጀች፡ስለ ሰማዕቱ፡ቂርቆስና፡ስለእናቱ፡ኢየሉጣ፡የክር ስቲያንን፡ነፍስ፡ኃጢአቷን፡አስተስርይላት።
፴፯፤ አ፡ክርስቶስ፡አልፋ፡ወቢጣ፡ አናሕሲ፡ አበሳሃ፡በእንተ፡ስምከ፡የውጣ።	፴፯፤ አልፋ፡ቤጣ፡ክርስቶስ፡ሆይ፡የውጣ፡ስለሚ ባለው፡ስምህ፡በደሏን፡አቅልል።
፴፰፤ በእንተ፡መርምህናም፡ጽኑዕ፡ወአንቂጦስ፡ ጥቡዕ፡ስረይ፡ላቲ፡ለነፍሰ፡ክርስቲያን።	፴፰፤ ጽኑዕ፡ስለሚሆን፡መርምህናምና፡ብርቱ፡ ስለሆነ፡አንቂጦስ፡የክርስቲያንን፡ነፍስ፡ ኃጢአቷን፡አስተስርይላት።
፴፱፤ አ፡ክርስቶስ፡መፍቀሬ፡ሰብእ፡አናሕሲ፡ አበሳሃ፡በእንተ፡ስምከ፡ኅቡእ።	፴፱፤ ሰውን፡ወዳጅ፡ክርስቶስ፡ሆይ፡ስለ፡ኅቡእ፡ ስምህ፡በደሏን፡አቅልል።
፵፡ በአፈ፡አባ፡እንጦንስ፡ወአባ፡መቃርስ፡ በአፈ፡መክሲሞስ፡ወዱማቴዎስ። በአፈ፡ አባ፡ሲኖዳ፡ወአባ፡ብስኑዳ፡ስረይ፡ላቲ፡ ለነፍሰ፡ክርስቲያን።	፵፡ በአባ፡እንጦንስና፡በአባ፡መቃርስ፡ቃል፡ በመክሲሞስና፡በዱማቴዎስ፡ቃል። በአባ፡ ሲኖዳና፡በአባ፡ብስኑዳ፡ቃል፡የክርስቲያንን፡ ነፍስ፡ኃጢአቷን፡አስተስርይላት።
፵፩፤ አ፡ክርስቶስ፡ለድንግል፡ወልዳ፡አመ፡ዕለተ፡ ደይን፡ወፍዳ፡ወአመ፡ይትነበብ፡መጽሐፈ፡ ዕዳ፡አድኅና፡ለባህረ፡ሲኦል፡እሞገዳ፡ወኢታ ርእያ፡ለነበልባል፡ነዳ። ሥረይ፡ላቲ፡ለነፍሰ፡ ክርስቲያን።	፵፩፤ የድንግል፡ልጅዋ፡ክርስቶስ፡ሆይ፡የዕዳ፡ ደብዳቤ፡በሚነበብበት፡ጊዜ፡በፍርድ፡ቀን፡ ከሲኦል፡የእሳት፡ባሕር፡ሞገድ፡አድኅነት፡የሚ ነደውንም፡የእሳት፡ነበልባል፡አታሳያት፡የክር ስቲያንን፡ነፍስ፡ኃጢአቷን፡አስተስርይላት።
፵፪፤ በአፈ፡አባ፡ብሶይ፡ወአባ፡አሞይ፤ አ፡ ክርስቶስ፡አዶናይ፤ ንጉሠ፡ምድር፡ወሰማይ፤ ንጉሠ፡ባሕር፡ወቀላይ፤ አድኅና፡እምኵሉ፤ አበሳ፡ወጌጋይ።	፵፪፤ በአፈ፡አባ፡ብሶይና፡በአባ፡አሞይ፡ የምድርና፡የሰማይ፡የባሕርና፡የቀላይ፡ ንጉሥ፡አዶናይ፡የምትባል፡ክርስቶስ፡ሆይ፡ ከፍጹም፡በደልዋ፡ሁሉ፡አድኅናት።
፵፫፤ በአፈ፡አባ፡ዮሐንስ፡ከማ፡ወአባ፡በርሱማ፡ ወበአፈ፡አባ፡ገሪማ፡ወበአፈ፡አባ፡ሰላማ፡ ሥረይ፡ላቲ፡ለነፍሰ፡ክርስቲያን	፵፫፤ በአባ፡ዮሐንስ፡ከማና፡በአባ፡በርሱማ፡አፍ፡ በአባ፡ገሪማና፡በአባ፡ሰላማ፡አፍ፡የክርስቲ ያንን፡ነፍስ፡ኃጢአቷን፡አስተስርይላት።
፵፬፤ አ፡ክርስቶስ፡ንጉሠ፡ራማ፡አድኅና፡እምዘ ሲኦል፡ጸማ።	፵፬፤ የራማ፡ንጉሥ፡ክርስቶስ፡ሆይ፡ከሲኦል፡ ድካመ፡ነፍስ፡አድኅናት።
፵፭፤ በአፈ፡አባ፡አረጋዊ፡ካህን፡ወአባ፡ጸንጠ ሌዎን፡ወበአፈ፡ኵሎሙ፡ቅዱሳን፡ሥረይ፡ ላቲ፡ኃጢአታ፡ለነፍሰ፡ክርስቲያን።	፵፭፤ በካህኑ፡በአባ፡አረጋዊና፡በአባ፡ጸንጠሌዎን፡ አፍ፡በቅዱሳኑም፡ሁሉ፡አፍ፡የክርስቲያን፡ ነፍስ፡ኃጢአቷን፡አስተስርይላት።
፵፮፤ አ፡ክርስቶስ፡ዘትፈትሖሙ፡ለሙቁሐን፡ ፍትሓ፡ወአግዕዛ፡ለነፍሰ፡ኵሎሙ፡ክርስ ቲያን፡እምኵሉ፡ሐዘን፡ወአንብራ፡ኅበ፡ ተጋብኡ፡ቅዱሳን።	፵፮፤ እስረኞችን፡የምትፈታቸው፡ክርስቶስ፡ሆይ፡ የክርስቲያንን፡ሁሉ፡ነፍስ፡ከኃጢአት፡ ፈትተህ፡ከሐዘንዋ፡ነጻ፡አውጥተህ፡ቅዱሳን፡ በሚሰበሰቡበት፡ቦታ፡አኑራት።

Scanned by CamScanner

ዘዕለተ፡ሠሣዕና።

፵፯፤ በእንተ፡ሚካኤል፡ቃለ፡አብ፡ሰማዒ፡ወገብርኤል፡መዋኢ፡ወሩፋኤል፡እሳት፡በላዒ፡ወኡራኤል፡ማኅፈድ፡ጽኑዕ፡ቅድመ፡ገጸ፡ጸላኢ፡ሥረይ፡ላቲ፡ኀጢአታ፡ለነፍሰ፡ክርስቲያን።

፵፰፤ አ፡ክርስቶስ፡ጸሎተ፡ኵሉ፡ሰማዒ፡ለምውታን፡መንሥኢ፡ዘትጸብአ፡ለጸባኢ፡ወትገፍአ፡ለገፋዒ፡ኢትመጥዋ፡ለነፍሰ፡ክርስቲያን፡ለዲያብሎስ፡ቀናኢ፡ርድአ፡ረዳኢ፡በመለኮትከ፡መዋኢ፡ወአድኅና፡እምእሳት፡በላዒ።

፵፱፤ በእንተ፡ሱራፌል፡ወኪሩቤል፡እለ፡ብዙኃት፡አዕይንቲሆሙ፡ወአርባዕቱ፡እንስሳ፡ሰብአ፡ቤት፡ጸዋርያነ፡መንበር፡ወሠረገላ፡ዘእሳት።

፶፤ በእንተ፡ዕሥራ፡ወአርባዕቱ፡ካህናተ፡ሰማይ፡እለ፡ንቡራን፡ዲበ፡መናብርት፡ወእለ፡የዐውዱ፡መንበረ፡ጸባኦት፡በስብሐት፡ወበጸሎት፡ሥረይ፡ላቲ፡ኀጢአታ፡ለነፍሰ፡ኵሎሙ፡ክርስቲያን።

፶፩፤ አ፡ክርስቶስ፡አምላከ፡ምሕረት፡ሥረይ፡ላቲ፡ዘገብረት፡ኵሎ፡ምግባረ፡ኀጢአት፡በእንተ፡ኵሎሙ፡ትጉሐን፡መላእክት፡ወመዋዕያን፡ሰማዕት።

፶፪፤ በአፈ፡ኵሎሙ፡ጸጸላት፡ርቱዓን፡ሃይማኖት፡በአፈ፡ኅሩያን፡ወክቡራን፡ካህናት፡በአፈ፡ደናግል፡ንጹሐን፡ወመስተዓግሣን፡ወኵሉመ፡ማኅበረ፡በኵር፡ፍሡሐን፡ሥረይ፡ላቲ፡ለነፍሰ፡ክርስቲያን፡አመ፡ዕለተ፡ፍዳ፡ወደይን።

፶፫፤ ወአንብራ፡በየማን፡ምስለ፡አባግዒከ፡ቡሩካን።

፶፬፤ በአፈ፡አባ፡ኖብ፡ሰማዕት፡ዕዉቅ፡ወበጸሎተ፡ሠለስቱ፡ደቂቅ፡ወበጸሎተ፡ኵሎሙ፡ዕድ፡ወአንስት፡ማኅበረ፡አብ፡ወወልድ፡ወመንፈስ፡ቅዱስ፡ሠለስቱ፡አስማት።እለ፡ዘከርነ፡ስሞሙ፡ወእለ፡ኢዘከርነ፡አስማቲሆሙ፡አንተ፡ዘክሮሙ።

፶፭፤ እወ፡እግዚኦ፡ፍትሐ፡ወአግዕዛ፡አንጽሖ፡ወአሠንያ፡ወአሰዕርያ፡እምኵሉ፡አበሳ፡ወመርገም።

የሠሣዕና፡ዕለት።

፵፯፤ የአብን፡ቃል፡ስለሚሰማ፡ሚካኤልና፡ድል፡አድራጊ፡ስለሚሆን፡ገብርኤል፡እሳታዊ፡ስለሚሆንም፡ሩፋኤል፡በጠላት፡ፊት፡እንደጽኑ፡ግንብ፡ስለሚሆን፡ኡራኤል፡የክርስቲያንን፡ነፍስ፡ኀጢአቷን፡አስተስርይላት።

፵፰፤ የሰውን፡ሁሉ፡ጸሎት፡የምትሰማ፡ሙታንንም፡የምታስነሣ፡ሰልፈኛውን፡የምትወጋ፡ገፊውን፡የምትገፋ፡ክርስቶስ፡ሆይ፡የክርስቲያንን፡ነፍስ፡ለቀናተኛ፡ዲያብሎስ፡አሳልፈህ፡አትስጣት፤በመለኮትህ፡የምትረዳ፡ሆይ፡እርዳት፤ከሚበላ፡እሳትም፡አድናት።

፵፱፤ ዐይኖቻቸው፡ብዙ፡ስለሚሆኑ፡ሱራፌልና፡ኪሩቤል፡ቤተ፡ሰቦች፡የሆኑ፡የእሳት፡መንኰራኵሮች፡ስለሚባሉ፡ጸወርተ፡መንበር፡አርባዕቱ፡እንስሳ።

፶፤ በምስጋናና፡በጸሎት፡ተወስነው፡በሠራዊት፡ጌታ፡መንበር፡ዙሪያ፡በወንበሮች፡የሚቀመጡ፡ስለ፡ሃያ፡አራቱ፡ካህናት፡ሰማይ፡የክርስቲያንን፡ነፍስ፡ሁሉ፡ኀጢአቷን፡አሥተሥርይላት።

፶፩፤ የምሕረት፡ባለቤት፡ክርስቶስ፡ሆይ፡ስለ፡ትጉሐን፡መላእክት፡ሁሉና፡ስለ፡ድል፡አድራጊዎች፡ሰማዕታት፡ብለህ፡የሠራችውን፡የኃጢአት፡ሥራ፡ሁሉ፡ይቅር፡በላት።

፶፪፤ ሃይማኖታቸው፡በቀና፡ጸጸላት፡ሁሉ፡አፍ፡በተመረጡና፡በከበሩ፡ካህናትም፡አፍ፡በሚታገሡ፡በንጹሐን፡ደናግል፡አፍ፡ደስ፡ብሏቸው፡በሚኖሩ፡ሁሉ፡በማኅበረ፡በኵር፡አማላጅነት፡የክርስቲያንን፡ነፍስ፡ይቅር፡በላት፤ከፍርድ፡ቀንም፡ፍዳ፡አድናት።

፶፫፤ ከቡሩካን፡ጻድቃንም፡ጋራ፡በቀኝ፡አቁማት።

፶፬፤ በታወቀው፡ሰማዕት፡በአባ፡ኖብ፡አፍ፡በሠለስቱ፡ደቂቅም፡ጸሎት፡የሦስቱ፡ስሞች፡የአብ፡የወልድ፡የመንፈስ፡ቅዱስ፡ማኅበር፡በሆኑ፡በሴቶችና፡በወንዶች፡ጸሎት፡ስማቸውን፡የጠራናቸውንና፡ያልጠራናቸውን፡አቤቱ፡አንተ፡አስባቸው።

፶፭፤ አዎን፡አቤቱ፡ከርግማንና፡ከበደል፡ሁሉ፡የተፈታች፡ነጻ፡የወጣች፡ያማረች፡የተስተካከለች፡አድርጋት።

Scanned by CamScanner

ዘዕለተ፡ሆሣዕና።

፻፲፩ እመሂ፡በሐሰት፡መሐለት፡አው፡በቁመት፡ደፈረት፡እመሂ፡በቃል፡አበሰት፡ወእመሂ፡በምግባሩ፡ረኵሰት፡እመሂ፡በኅቡእ፡ኀሠሠት፡ወእመሂ፡በክሡት፡ደኃሰት፡ሥረይ፡ላቲ፡ወአናሕሲ፡ነሲሎ፡አበሳሃ፡ወኀጣውኢሃ፡ለነፍሰ፡ክርስቲያን።

፻፲፪ እስመ፡አልቦ፡ሰብእ፡ዘእንበለ፡ኀጢአት፡አንተ፡ባሕቲትከ፡ዘልዑል፡እምሰማያት፡ወንጹሕ፡እምኀጢአት።

፻፲፫ ወለከ፡ይደሉ፡ክብር፡ወስብሐት፡ወአኰቴት፡ወስግደት፡እስከ፡ነፍስ፡ደኃሪት።
ወላዕሌነ፡ይኩን፡ሣህል፡ወምሕረት።

፻፲፬ አ፡ሥሉስ፡ቅዱስ፡አብ፡ወወልድ፡ወመንፈስ፡ቅዱስ፡ይእዜኒ፡ወዘልፈኒ፡ወለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።
በገዩ፡ተፈጸመ፡ሥርዓተ፡ሆሣዕና።

ምዕራፍ፡፬።

ትእዛዝ።

ወይትጋብኡ፡ካህናት፡ውስተ፡ቤተ፡ክርስቲያን፡ቅድስት፡በሠርክ፡ሆሣዕና፡ወያንብቡ፡ምዕተ፡ወሃምሳ፡መዝሙረ፡ዳዊት።
(ይ፡ካ፡) በዜማ፡ግዕዝ፡ቅዱስ፡ (ይ፡ሕ፡) ይትልዉ፡ዘንተ፡እንዘ፡ይብሉ፡እግዚአብሔር፡አስከ፡ተፍጸሜቱ።
ዋዜማ፡በኵር፡ሃሌ፡ሉያ፡እግዚአብሔር፡ውእቱ፡ዖማኑኤል፡ስመ፡ዘይፈኑ፡ዐሐየ፡ውስተ፡ምዕራቢሁ፡ወወርኀኒ፡ገብአ፡በዕድሜሁ፡ከያኒ፡ሰማያተ፡ስኑ፡ወመልአ፡ምድረ፡ስብሐቲሁ።

(ይ፡ካ፡)መስተብቊዕ።
ሀየንተ፡ለእግዚአብሔር፡ምድር፡በምልኣ።
ሰብሕዎ፡ለእግዚአብሔር፡እምሰማያት፡
ሀየንተ፡እግዚአብሔር፡ነግሠ፡ሰብሕዎ፡ለእግዚአብሔር፡ስብሐተ፡ሐዲስ፡ሀየንተ፡እግዚአ፡
ጸራሕኩ፡ሰብሕዎ፡ለእግዚአብሔር፡
በቅዱሳኑ፡ወኢትጎድግ፡መስተብቊዐ፡
አልቦ፡ይትባረክ።

የሆሣዕና፡ዕለት።

፻፲፩ በሐሰት፡ብትምል፡ወይም፡በመቆም፡ብትደፍር፡ወይም፡በቃል፡ብትበድል፡ምንም፡በሥራዋ፡ብትረክስ፡በሥውር፡ኀጢአት፡ብትሰራ፡ወይም፡በግልጥ፡ብትሰስን፡የክርስቲያንን፡ነፍስ፡ኀጢአቷን፡አስተስርይላት፡የበደለችውንም፡ሁሉ፡አቅልልላት።

፻፲፪ ያለ፡ኀጢአት፡ንጹሕ፡ሰው፡የለምና፡አንተ፡ብቻህን፡ልዑለ፡ባሕርይ፡ንጹሐ፡ባሕርይ፡ነህ።

፻፲፫ ለአንተ፡ክብር፡ጌትነት፡ምሥጋና፡ስግደትም፡እስከ፡መጨረሻይቱ፡ሕቅታ፡ድረስ፡ከዚያም፡በኋላ፡ይገባል፡ለእኛም፡ይቅርታና፡ቸርነት፡ይደረግልን።

፻፲፬ ልዩ፡ሦስት፡የምትሆን፡አብ፡ወልድ፡መንፈስ፡ቅዱስ፡ሆይ፡ዛሬም፡ዘወትርም፡ለዘላለሙ፡አሜን።
በዚህ፡የሆሣዕና፡ሥርዓት፡ተፈጸመ።

ምዕራፍ፡፬።

ትእዛዝ።

በሆሣዕና፡ምሽት፡በቅድስት፡ቤተ፡ክርስቲያን፡ካህናት፡ይሰብሰቡ፡መዶ፡ኀምሳውን፡የዳዊት፡መዝሙር፡ይድገሙ።
ካህን፡በግዕዝ፡ዜማ፡ቅዱስ፡ይበል፡ሕዝቡም፡እግዚአብሔር፡ብለው፡ተቀብለው፡እስከ፡መጨረሻው፡ይበሉ።
በአንድ፡ሃሌታ፡ዋዜማ፡ስሙ፡ዖማኑኤል፡የሚባል፡እርሱ፡እግዚአብሔር፡ዐሐይን፡ወደ መግቢያው፡የሚአሰናብት፡ጨረቃም፡በጊዜው፡ጊዜ፡ይመለሳል፡የጌትነቱ፡መወደድ፡ላህይ፡ሰማያትን፡ሸፈነ፡ምሥጋናውም፡ምድርን፡መላ።
ካህን፡መስተብቊዕ፡ይበል።
ለእግዚአብሔር፡ምድር፡በምልዓ፡ፈንታ፡ሰብሕዎ፡ለእግዚአብሔር፡እምሰማያት፡በል፡በእግዚአብሔር፡ነግሠ፡ፈንታ፡ሰብሕዎ፡ለእግዚአብሔር፡ስብሐተ፡ሐዲስ፡በል፡በእግዚአ፡ጸራሕኩ፡ፈንታ።ሰብሕዎ፡ለእግዚአብሔር፡በቅዱሳኑ፡በል፡መስተብቊዕን፡

ክፍል፡፩።

ዘኢሳይያስ፡ነቢይ፡በረከቱ፡ትኩን፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ምዕ፡፶፰፡፲፪–፳፫።

፲፪፡ ስምዓኒ ፡ ያዕቆብ ፡ ወእስራኤልኒ ፡ ዘአነ ፡ ጸዋዕኩከ ፡ አነ ፡ ቀዳማዊ ፡ ወአነ ፡ ድኅራዊ ፡ ለዓለም። ዘዳ፡፴፪፡፴፱።

፲፫፡ እዴየ ፡ ሣረረታ ፡ ለምድር ፡ ወየማንየ ፡ አጽንዓት፡ለሰማይ፡እጼውዖሙ፡ወይመጽኡ፡ኅቡየ፡ኅቡረ።

፲፬፡ ወይትጋብኡ ፡ ኵሎሙ ፡ ወይሰምዑ ፡ መኑ ፡ ነገረከ ፡ ዘንተ ፡ እኮኑ ፡ በአፍቅሮ ፡ ዚአከ ፡ ገበርኩ፡ ፈቃደከ ፡ ላዕለ ፡ ባቢሎን ፡ ከመ ፡ አእትት፡ዘርኦሙ፡ለከላውዴዎን።

፲፭፡ አነ ፡ ነበብኩ ፡ ወአነ ፡ ጸዋዕኩ ፡ ወአምጻእኩክሙ፡ወረዳእኩክሙ፡እንዘ፡እብል፡ንዑ፡ኅቡየ፡ወስምዑኒ፡ዘንተ።

፲፮፡ አኮኑ ፡ እምትካት ፡ ኢተናገርኩ ፡ ጽሚተ ፡ እመኒ፡ኮነ ፡ ህየ ፡ ከመ ፡ ሀለውኩ ፡ ወይእዜኒ ፡ እግዚአብሔር ፡ እግዚእ ፡ ፈነወኒ ፡ ወመንፈሱ። ኢሳ፡፵፰፡፲፮።

፲፯፡ ከመ ፡ ዝ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘአድነነከ ፡ ወዘባልሐከ ፡ ቅዱስ ፡ እስራኤል ፡ አነኬ ፡ ውእቱ፡ አምላክከ ፡ ወአርአይኩከ ፡ ፍኖተ ፡ ኅበ፡ ትረክብ፡እንተ ፡ ባቲ ፡ ተሐውር። መዝ፡ ፸፮፡፳።

፲፰፡ ሶበሰ ፡ ሰማዕከ ፡ ትእዛዝየ ፡ እምኮነ ፡ ከመ ፡ ውኂዝ፡ሰላምከ፡ወጽድቅከኒ፡ከመ፡ማዕበለ፡ባሕር።

፲፱፡ ወእምኮነ፡ከመ፡ኖኅ፡ባሕር፡ዘርእከ፡ወከመ፡ጸበለ፡ምድር፡ትውልደ፡ከርሥከ።

፳፡ ወይእዜኒ፡ከመ፡ኢትጥፍኡ፡ወከመ፡ኢትትኃሥሉ፡ዓዐ፡እምባቢሎን፡እንዘ፡ትጮይዩ፡እምከላውዴዎን ፡ ወዜንዎ ፡ ቃለ ፡ ትፍሥሕት። ዘፍ፡፳፪፡፲፯። ኢዮ፡፭፡፳፩።

፳፩፡ ወዮሰማዕ ፡ ዝንቱ ፡ ነገር ፡ ወንግሩ ፡ እስከ ፡ አጽናፈ ፡ ምድር ፡ ወበሉ ፡ አድኅኖ ፡ እግዚአብሔር፡ለያዕቆብ፡ገብሩ።

የሠሣዕና፡ዕለት።

ክፍል፡፩።

የኢሳይያስ ፡ ትንቢት ፡ በረከቱ ፡ ከኛ ፡ ጋራ ፡ ለዘላለሙ፡ትኑር፡አሜን።

ምዕ፡፶፰፡፲፪–፳፫።

፲፪፡ እኔ ፡ እስራኤል ፡ ብየ ፡ የጠራሁህ ፡ ያዕቆብ ፡ ስማኝ ፡ ቀዳማዊ ፡ ድኅራዊ ፡ ፈጣሪ ፡ ለዘለዓለሙ፡እኔ፡ነኝ። ዘዳ፡፴፪፡፴፱።

፲፫፡ እጄ ፡ (ሥልጣኔ) ፡ ምድርን ፡ ፈጠረችት ፡ ሥልጣኔም፡(ቀኜ)፡ሰማይን፡አጸናችው፡እጠራችዋለሁ፡በአንድነት፡ወደእኔ፡ይመጣሉ።

፲፬፡ ሁሉም፡ተሰብስበው፡ይሰማሉ፡ይህን፡ማን፡ነገረህ? አንተን፡በመውደድ፡የከለዳውያንን፡ልጅች ፡ አጠፋ ፡ ዘንድ ፡ በባቢሎን ፡ ላይ ፡ ፈቃድህን፡ያደረግሁ፡አይደለምን?

፲፭፡ እኔ፡ተናገርሁ፡እኔም፡ጠራሁ፡ከባቢሎንም፡አመጣኋችሁ ፡ ወደእኔ ፡ ኑ ፡ ይሸንንም ፡ ስሙኝ፡እያልኩ፡ረዳኋችሁ።

፲፮፡ ከጥንት፡ጀምሮ፡በቆይታ፡አልተናገርኩምና፡መከራውም ፡ ቢደረግባችሁ ፡ እኔ ፡ በዚያ ፡ እንዳለሁ ፡ ዕወቁ ፡ አሁንም ፡ ጌታ ፡ የሚሆን ፡ እግዚአብሔር ፡ ላከኝ ፡ ሕይወቱ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስም፡ላከኝ። ኢሳ፡፵፰፡፲፮።

፲፯፡ ያዳነህ ፡ የተቤዠህ ፡ እስራኤልን ፡ የሚአጸና ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ ፈጣሪህ ፡ እኔ ፡ ነኝ፡ ዕረፍት ፡ ወደምታገኝባት ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ የምትሄድባትን ፡ ጐዳናም ፡ አሳየሁህ ፡ መገ፡ ፴፪፡፫።

፲፰፡ ትእዛዜንስ ፡ ብትሰማ ፡ ሰላምህ ፡ እንደ ፡ ፈሳሽ ፡ ጽድቅህም ፡ እንደ ፡ ባሕር ፡ ማዕበል ፡ በሆነ ፡ ነበር።

፲፱፡ ዘርህ ፡ እንደ ፡ ባሕር ፡ አሸዋ ፡ እንደ ፡ ትቢያም ፡ በበዛ ፡ ነበር።

፳፡ አሁንም ፡ ፈጽማችሁ ፡ እንዳትጠፉ ፡ ከከላውያስ ፡ እየሸሻችሁ ፡ ከባቢሎን ፡ ውጡ ። የተድላ ፡ የደስታን ፡ ቃል ፡ ተናገሩ። ዘፍ፡፳፪፡፲፯። ኢዮ፡፭፡፳፩።

፳፩፡ ይህ ፡ ነገር ፡ ይሰማ ፡ እግዚአብሔር ፡ ባርያው ፡ ያዕቆብን ፡ አዳነው ፡ ብላችሁ ፡ እስከ ፡ ምድር ፡ ዳርቻም ፡ ድረስ ፡ ተናገሩ።

Scanned by CamScanner

ዘዕለተ፡ሠሣዕና።

፳፱፡ ወእመኒ ፡ጸምኡ ፡ማየ ፡በበድው ፡ያወፅእ ፡ለሙ ፡ማየ ፡እምከሠሐ ፡ወትነቅዕ ፡ለሙ ፡ከሠሐ ፡ወይውኅዝ ፡ማይ ፡ወይሰትዩ ፡ሕዝበየ።

፳፫፡ ወይትፈሥሑ ፡ነዳያን ፡እንከ ፡ይቤ ፡እግዚአ ብሔር።ኢሳ፡፶፭፡፩።

ዘናሆም ፡ነቢይ ፡በረከቱ ፡ትኩን ፡ምስሌነ ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ምዕ፡፩፡፪-፳።

፪፡ እግዚአብሔር ፡ቀናኢ ፡ወመስተበቅል ፡ወይ ትቤቀሎሙ ፡እግዚአብሔር ፡በመዓቱ ፡ለፀሩ ፡ወያጠፍአሙ ፡ለጸላእቱ።

፫፡ እግዚአብሔርሰ ፡መስተዐግሥ ፡ወዐቢይ ፡ኀይሉ ፡ወንጹሕኒ ፡አልቦ ፡በኀቤሁ ፡ለእግዚአ ብሔር ፡በፍጽም ፡ወበድኅር ፡ፍኖቱ ፡ወይከውኑ ፡ከመ ፡ጸበል ፡ወይሬስዮሙ ፡ከመ ፡ደመና ፡በታሕተ ፡እገሪሁ።

፬፡ ወያጠፍአ ፡ለባሕር ፡ወያየብሳ ፡ወያነጽፎሙ ፡ለኵሉሙ ፡አፍላግ ፡ኀልቁ ፡ባሳን ፡ወቀር ሜሎስ ፡ወጠፍአ ፡ኵሉ ፡ፍሬ ፡ሊባኖስ ፡መዝ፡፻፮፡፴።

፭፡ ወአድለቅለቁ ፡አድባር ፡እምኔሁ ፡ወአንቀ ልቀሉ ፡አውግር ፡ወደንገፀት ፡ኵላ ፡ምድር ፡እምቅድመ ፡ገጹ ፡ወአልቦ ፡ዘይትቃወም ፡ቅድመ ፡ገጹ ፡እምኵሉሙ ፡እለ ፡ይነብሩ ፡ውስቴታ።

፮፡ ወመኑ ፡ይትቃወማ ፡ለመቅሠፍተ ፡መዐቱ ፡ወመዐቱኒ ፡ይመስዎሙ ፡ለአድባር ፡አርእስ ቲሆ ፡ኑ ፡ወይትቀጠቀጥ ፡ከሠሐ ፡እምኔሁ ፡ሚል፡፫፡፪።

፯፡ ጎር ፡እግዚአብሔር ፡ለእለ ፡ይትዔገሥዎ ፡በዕለተ ፡ምንዳቤሆሙ ፡ወየእምሮሙ ፡ለእለ ፡ይፈርህዎ።መሳ፡፯፡፳፯።

፰፡ ወይሬስዮሙ ፡ለእለ ፡ይትነሥኡ ፡በእከይ ፡ከመ፡ይጎልቁ ፡በፍኖተ ፡አይኅ ፡ወይዴ ግኖሙ፡ጽልመት፡ለፀሩ።

የሠሣዕና፡ዕለት።

፳፱፡ በምድረ ፡በዳም ፡ውኃን ፡ቢጠሙ ፡ውኃ ከአለት ፡ደንጊያ ፡ያመነጭላቸዋል ፡ድንጋይ ውኃን ፡ታስገኝላቸዋለች ፡ፈሳሽም ፡ይፈሳል ወገኖቼም ፡ውኃን ፡ይጠጣሉ።

፳፫፡ እግዚአብሔርም ፡እንግዲህ ፡ወዲህ ፡ድኖች ደስ ፡ይላቸዋል ፡አለ።ኢሳ፡፶፭፡፩።

የናሆም ፡ትንቢት ፡በረከቱ ፡ከኛ ፡ጋራ ለዘላለሙ ፡ትኑር ፡አሜን።

ምዕ፡፩፡፪-፳።

፪፡ እግዚአብሔር ፡ለአምላክነቱ ፡ቀናኢ ፡ነው ጠላቶቹንም ፡እግዚአብሔር ፡ተቈጥዶ ፡ይበቀ ላቸዋል ፡ጠላቶቹንም ፡ያጠፋቸዋል።

፫፡ እግዚአብሔርስ ፡ኀይሉ ፡ገናና ፡ሲሆን ፡ዕጉሥ ነው ፡በእግዚአብሔር ፡ዘንድ ፡ንጹሕ ፡የለም ሥራው ፡በፈትም ፡በኋላም ፡ነው ፡እነሱም እንደ ፡ትቢያ ፡ይሆናሉ ፡እሱም ፡ከእግሩ በታች ፡እንዳሰ ፡ደመና ፡ያደርጋቸዋል።

፬፡ ባሕሪቱንም ፡ፈጽሞ ፡ያደርቃታል ፡ያጠፋታል ፈሳሾችንም ፡ሁሉ ፡ያደርቃቸዋል ፡(መኳ ንቱን) ፡ቀርሜሎስ ፡ባሳን ፡(ሠራዊቱ) ፡ጠፋ የደጋውም ፡ዛፍ ፡ፍሬ ፡ሁሉ ፡ጠፋ ፡(የንጉሡ ተድላ ፡ደስታ)።መዝ፡፻፮፡፴።

፭፡ ከእርሱም ፡የተነሣ ፡ተራሮች ፡ተነዋወጡ (ነገሥታቱ) ፡ኮረብታዎችም ፡ተነዋወጡ (መኳንንቱ) ፡ከገጸ ፡መዓቱም ፡የተነሣ ምድር ፡ሁሉ ፡ደነገጡች ፡(ትሑታኑ) በሱዋም ፡ከሚኖሩ ፡ሰዎች ፡ሁሉ ፡በፊቱ ሁኖ ፡የሚቃወመው ፡የለም።

፮፡ ተቈጥዶ ፡ያመጣት ፡መቅሰፍትን ፡የሚቃ ወማት ፡የለም ፡ቁጣውም ፡የነገሥታቱ ፡ራሶች ቸውን ፡እንደሰም ፡ያቀልጣቸዋል ፡ከሱም የተነሣ ፡አለቱ ፡ይሰነጠቃል ፡(ብልጣሶር ሰናክሬም)፡ሚል፡፫፡፪።

፯፡ መከራ ፡በመጣባቸው ፡ቀን ፡መከራውን ለሚታገሱ ፡ሰዎች ፡እግዚአብሔር ፡ቸር ፡ነው የሚፈሩትንም ፡ይወዳቸዋል።መሳ፡፯፡፳።

፰፡ በክፉ ፡ነገር ፡የሚነሡትንም ፡ሰዎች ፡እጅ ማየ ፡አይኅ ፡ባለ ፡መቅሰፍት ፡እንዲጠፉ ፡ያ ርጋቸዋል ፡ጠላቶቹንም ፡መከራ ፡እየተከተለ ያጠፋቸዋል።

Scanned by CamScanner

ክፍል፡፪።

(ይዲ)፡ቅድመ፡ወንጌል።

መዝ፤፰፡፪።

እምአፈ ፡ ደቂቅ ፡ ወሕፃናት ፡ አስተዳሎከ ፡ ስብሐተ ። በእንተ ፡ ጸላዒ ። ከመ ፡ ትንሥዖ ፡ ለጸላዒ፡ወለገፋዒ።

ወንጌል፡ዘማቴዎስ።

ምዕ፤፳፡፳–፳፰።

፳፤ ወእምዝ ፡ መጽአት ፡ ኀቤሁ ፡ እሞሙ ፡ ለደቂቀ፡ ዘብዴዎስ ፡ ምስለ ፡ ደቂቃ ፡ ወሰገደት፡ሎቱ፡እንዘ፡ትስእል፡እምኀቤሁ።

፳፩፤ ወይቤላ ፡ ምንተ ፡ ትፈቅዲ ፡ እግበር ፡ ለኪ ፡ ወትቤሎ ፡ ረሲ ፡ ሊተ ፡ ከመ ፡ ይንበሩ ፡ እሉ ፡ ደቂቅየ ፡ ክልኤሆሙ ፡ አሐዱ ፡ በየማንከ ፡ ወአሐዱ፡በፀጋምከ፡በመንግሥትከ።

፳፪፤ ወአውሥአ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡ወይቤሎሙ፡ ኢተአምሩ ፡ ዘትስእሉ ፡ ትክሉኑ ፡ ሰትየ ፡ ጽዋዕ፡ዘአነ ፡ ሀሎኩ ፡ እስተይ ፡ ወጥምቀተኒ ፡ ዘአነ ፡ እጠመቅ ፡ ትጠመቁኑ ፡ ወይቤልዎ ፡ እወ፡ንክል።

፳፫፤ ወይቤሎሙ ፡ ጽዋዕየሰ ፡ ትሰትዩ ፡ ወጥምቀተኒ፡ ትጠመቁ ፡ ወነቢረሰ ፡ በየማንየ ፡ ወበፀጋምየ ፡ አኮ ፡ አነ ፡ ዘእሁብ ፡ ዘእንበለ ፡ ለአለ ፡ አስተዳለወ፡ሎሙ አቡየ።

፳፬፤ ወሰሚያሙ ፡ ዐሠርቱ ፡ ሐዘኑ ፡ በእንተ ፡ ክልኤሆሙ፡አኀው።

፳፭፤ ወጸውዖሙ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡ወይቤሎሙ፡ ተአምሩኑ፡ከመ፡መኳንንቲሆሙ፡ለአሕዛብ፡ ይኤዝዝዎሙ ፡ ወዐበይቶሙ ፡ ይሜለጡ ፡ ላዕሌሆሙ።

፳፮፤ አኮኬ ፡ ከመ ፡ ዝ ፡ ዘይከውን ፡ በኀቤክሙሰ ፡ ባሕቱ ፡ ዘይፈቅድ ፡ እምውስቴትክሙ ፡ ይኩን፡ዐቢየ፡ይኩንክሙ፡ላእከ።

፳፯፤ ወዘሂ ፡ ይፈቅድ ፡ እምኔክሙ ፡ ይኩን ፡ ሊቀ ፡ ይኩንክሙ፡ገብረ።

፳፰፤ በከመ፡ኢመጽአ፡ወልደ፡ዕጓለ፡እመሕያው፡ ይትለአከዎ ፡ ዘእንበለ ፡ ከመ ፡ ይትለአክ ፡ ወየሀብ፡ነፍሰ፡ቤዛ፡ብዙኃን።

ክፍል፡፪።

ዲያቆን፡ከወንጌል፡አስቀድሞ።

መዝ፤፰፡፪።

ከሕፃናት ፡ አንደበት ፡ ምስጋናን ፡ አዘጋጀህ ፤ ስለጠላት፡ደስ፡አይበለው፤ጠላትና፡ገፊውን፡ ታጠፋው፡ዘንድ።

የማቴዎስ፡ወንጌል።

ምዕ፤፳፡፳–፳፰።

፳፤ ከዚህም፡በኋላ፡የዘብዴዎስ፡ልጆች፡እናት፡ ከልጆቿ ፡ ጋር ፡ መጥታ ፡ እየማለደች ፡ ሰገደችለት።

፳፩፤ ምን፡ላደርግልሽ፡ትወጂለሽ፡አላት፤እነዚህ፡ ልጆቼ ፡ በመንግሥትህ ፡ አንዱ ፡ በቀኝህ ፡ አንዱ፡በግራህ፡እንዲቀመጡ፡አድርግልኝ፡ አለችው።

፳፪፤ ጌታ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስም፡መልሶ፡የምትለምኑትን ፡ አታውቁም ፤ እኔ ፡ የምጠጣውን ፡ ጽዋ፡መጠጣት፡ትችላላችሁን?እኔ፡የምጠመቃትን፡ ጥምቀትስ ፡ ትጠመቃላችሁን? አላቸው።አዎን፡እንችላለን፡አሉት።

፳፫፤ እሱም ፡ ጽዋዬንስ ፡ ትጠጣላችሁ ፤ ጥምቀቴንም፡ ትጠመቃላችሁ ፤ በቀኜና ፡ በግራዬ ፡ መቀመጥን ፡ ግን ፡ በሰማይ ፡ ያለው፡አባቴ፡ካዘጋጀላቸው፡በቀር፡እኔ፡የምሰጥ፡አይደለሁም፡ አላቸው።

፳፬፤ ዐሥሩም ፡ ሰምተው ፡ በሁለቱ ፡ ወንድማማቾች፡ላይ፡አንጐራጐሩ።

፳፭፤ ጌታ፡ኢየሱስም፡ጠርቶ፡አሕዛብን፡መኳንንቶቻቸው፡እንዲገዙአቸው፡ታላላቆቹም፡እንዲሠለጥኑባቸው፡አታውቁምን?አላቸው።

፳፮፤ ለእናንተ፡ግን፡እንዲህ፡አይደለም፤ከእናንተ፡ የበላይ ፡ ሊሆን ፡ የሚወድ ፡ አገልጋይ ፡ ይሁናችሁ።

፳፯፤ ከእናንተም፡አለቃ፡ሊሆን፡የሚወድ፡ሎሌ፡ ይሁናችሁ።

፳፰፤ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሊአገለግል ፡ ሰውነቱንም ፡ ለብዙዎች፡ቤዛ፡አድርጎ፡ሊሰጥ፡እንጂ፡ሊአገለግሉት፡አልመጣምና።

Scanned by CamScanner

በ፭፡ሰዓተ፡ሌሊት፡ዘሠኑይ።

፲፪፤ ንሰብሖ፡ወንወድሶ፡ወናልዕል፡ስሞ፡ኀቡረ፡
እስመ፡ውእቱ፡ገብረ፡ለነ፡ምሕረተ፡በከመ፡
ዕበየ፡ሣህሉ።



ሠኞ፡ሌሊት፡በ፭፡ሰዓት።

፲፪፤ ፈጽሞ፡እናመስግነው፤ስሙንም፡በአንድነት፡
ከፍ፡ከፍ፡እናድርግ፤አርሱ፡እንደ፡ይቅርታው፡
ገናናነት፡ምሕረትን፡አድርጎልናልና።



Scanned by CamScanner

ዘዕለተ፡ሰሚዕና።

ድኅረ፡ወንጌል።

፩፤ ወበይእቲ ፡ ሰዓት ፡ እምእሑደ ፡ ሰሚዕና ፡ ስብሐተ ፡ አዳም ፡ ትሕዝብተ ፡ ዘተሐዘቡ ፡ ኪያሃ ፡ አይሁድ ፡ ዐላውያን ፡ በእንተ ፡ መድኀኒነ፡ወንጦሥነ፡ክርስቶስ።

፪፤ ከመ ፡ ውእቱ ፡ አምላለ ፡ ነገሥተ ፡ ምድር ፤ እስመ፡ ጉቡአን ፡ ብዙኃን ፡ ዘየዐውድዎ ፡ ሐራ ፡ ወተዓይን ፡ ወኮያንው ፡ በአምላለ ፡ ነገሥት።

፫፤ ወከመ ፡ ዝ ፡ ትትሔዘብ ፡ እሞሙ ፡ ለዮሐንስ ፡ ወለያዕቆብ ፡ እኁሁ ፡ ደቂቀ ፡ ዘብዴዎስ ፡ ወተሐዘበት ፡ ከመዝ ፡ ወመጽአት ፡ ኀበ ፡ መድኀኒነ ፡ ቅድመ ፡ ሕዝብ ፡ ወአርዳኢሁ።

፬፤ ወሰገደት ፡ ሎቱ ፡ ምስለ ፡ ደቂቃ።

፭፤ ወሰአለት ፡ እምኔሁ ፡ እንዘ ፡ ትብል ፡ ከመዝ ፡ በል ፡ ስማዕ ፡ ስእለትየ ፡ ክልኤቱ ፡ ደቂቅየ ፡ ከመ ፡ ይንበሩ ፡ ምስሌከ ፡ በውስተ ፡ መንግሥትከ ፡ አሐዱ ፡ በየማንከ ፡ ወአሐዱ ፡ በፀጋምከ።

፮፤ አጽምዑ ፡ ኀበ ፡ መስተሣህል ፡ ዘምሕረቱ ፡ ብዙኅ ፡ ዘይፈቅድ ፡ ሕይወተ ፡ ኵሉ ፡ ዓለም።

፯፤ ይቤ ፡ ትክሉኑ ፡ ከመ ፡ ትስተዩ ፡ ጽዋዐ ፡ ዘመጻእኩ ፡ በእንቲአሁ ፡ ከመ ፡ እስተዮ።

፰፤ ወለጥምቀትየኒ ፡ ካልእት ፡ ዘእጠመቃ ፡ ትጠመቅዋኑ ፡ ይቤልዎ ፡ እወ ፡ ንክል።

፱፤ ወይቤሎሙ ፡ ጽዋዕየሰ ፡ ትሰትዩ ፡ ወጥምቀትየኒ ፡ ትጠመቁ ፡ ወነቢሮትክሙሰ ፡ በየማንየ ፡ ወበፀጋምየ ፡ አኮ ፡ ውእቱ ፡ ሊተ ፡ አላ ፡ ለእለ ፡ አስተዳለወ ፡ ለሙ ፡ አቡየ ፡ ሰማያዊ ፡ ዘይመልእ ፡ ኵሎ ፡ መካነ ፡ ውእቱ ፡ ይሁቦሙ ፡ ለኅሩያኒሁ ፡ ገባርያነ ፡ ፈቃዱ።

፲፤ ወሶበ ፡ ሰምዑ ፡ ዘንተ ፡ ክልኤቱ ፡ አኀው ፡ አርመሙ ፡ ወሐሩ።

፲፩፤ በእንተ ፡ ብዝኅ ፡ ምሕረቱ ፡ ክርስቶስ ፡ መድኀኒነ ፡ መጽአ ፡ ወሐመ ፡ ወበእንተ ፡ ሕማማቲሁ ፡ አድኀነነ።

የሰሚዕና፡ዕለት።

ከወንጌል፡በኋላ

፩፤ የአዳም ፡ ክብር ፡ ከምትሆን ፡ ከዚያች ፡ ከሰሚዕና፡ እሑድ ፡ ወዲህ ፡ ስለ ፡ መድኃኒታችንና ፡ ስለ ፡ ንጉሣችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ፡ ወንጀለኞች ፡ አይሁድ ፡ የተጠራጠርዋት ፡ መጠራጠር፡እርሷ፡ይች፡ናት።

፪፤ እርሱ ፡ ጌታችን ፡ እንደ ፡ ምድራውያን ፡ አምሳል፡በነገሥታት፡ብዙ፡ሕዝብ፡የሚአጅበውና፡እንዲሁም ፡ ብዙ ፡ የጦር ፡ ሠራዊት፡ የጦር፡መሣሪያ፡በመያዝ፡በቀኝ፡በግራ፡የሚከተለው፡ይመስላቸው፡ነበርና።

፫፤ እንዲሁም፡የዘብዴዎስ፡ልጆች፡የዮሐንስና፡ የወንድሙ ፡ የያዕቆብ ፡ እናት ፡ ትጠራጠር፡ ነበር ። ተጠራጥራም ፡ በሕዝቡና ፡ በደቀ፡ መዛሙርቱ ፡ ፊት ፡ ወደ ፡ መድኃኒታችን ፡ መጣች።

፬፤ ከልጆቿ፡ጋርም፡ሰገደችለት።

፭፤ ከእርሱም፡ዘንድ፡እንዲህ፡ስትል፡ለመነች፡ አቤቱ፡ልመናዬን፡ሰምተህ፡እነዚህ፡ሁለቱ፡ ልጆቼ ፡ በመንግሥትህ ፡ ውስጥ ፡ አንዱ፡ በቀኝህ፡አንዱ፡በግራህ፡እንዲቀመጡ፡አድርግልኝ፡አለች።

፮፤ ምሕረቱ ፡ ብዙ ፡ ወደሚሆንና ፡ የዓለሙን ፡ ሁሉ፡ ድኅነት ፡ ወደሚወድ ፡ ይቅር ፡ ባይ ፡ ወደሆነ፡ጌታ፡አድምጡ።

፯፤ እኔ ፡ እጠጣው ፡ ዘንድ ፡ ስለእርሱ ፡ የመጣሁለትን፡ጽዋ፡ትጠጡ፡ዘንድ፡ትችላላችሁን?አለ።

፰፤ የምጠመቃትንስ ፡ ሁለተኛዋን ፡ ጥምቀቴን፡ ትጠመቋታላችሁን?አለ። አዎን ፡ እንችላለን፡ አሉት።

፱፤ ጽዋዬንስ ፡ ትጠጣላችሁ ፤ ጥምቀቴንም ፡ ትጠመቃላችሁ ፤ በቀኜና ፡ በግራዬ ፡ መቀመጣችሁን ፡ ግን ፡ የምፈቅድ ፡ እኔ ፡ ብቻ ፡ አይደለሁም ፤ በሁሉ ፡ ቦታ ፡ ምሉዕ ፡ የሆነ ፡ ሰማያዊ፡ አባቴም ፡ ፈቃዱን ፡ ለሚፈጽሙ ፡ ለመረጣቸው፡ ያዘጋጀውን ፡ የሚሰጥ ፡ እርሱ ፡ ነው፡ እንጂ ፡ አላቸው።

፲፤ ሁለቱም ፡ ወንድማማቾች ፡ ይኸን ፡ በሰሙ፡ ጊዜ፡ዝም፡ብለው፡ሄዱ።

፲፩፤ በቸርነቱ ፡ ብዛት ፡ መድኃኒታችን ፡ ክርስቶስ፡ ሰው ፡ ሆኖ ፡ መከራ ፡ ተቀበለ ። በመከራውም፡ አዳነን።

Scanned by CamScanner